

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

አካባቢ ሳይንስ

የመምህር መምሪያ

፫ኛ ክፍል



ሦስተኛ ክፍል

አካባቢ ሳይንስ
፫ኛ ክፍል
የመምህር መምሪያ

አዘጋጆች

መለሰ ተካልኝ
በላይ አይዳኙህም
ብሩክ ለማ
አንዋር አወል
ዘሪቱ አባተ

አርታኢና ገምጋሚዎች፡

ሠለሞን ወንድሙ
በላይ በለጠ
ሙሉነህ ተክለብርሃን
ጌታሁን ጌታቸው
አሊ ከማል
ፍቅርተ ቶለሳ
ምህረቱ ዋሌ

አስተባባሪ፡-

ጌታቸው ታለማ

ሥዕላዊ መግለጫ እና ገጽ ቅንብር፡-

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ (ብስራት እውነቱ)

2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀምንባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን።

ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል።

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል።

በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን።

ማውጫ ገፅ

ምዕራፍ አንድ 1

የክፍለ ከተማችን መገኛ 2

1.1. አንጻራዊ መገኛ ምንነት 2

1.2. የፍጹማዊ መገኛ ምንነት 4

1.3. የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ 6

1.4 የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ 9

1.5 የክፍለ ከተማችን አዋሳኝ ክፍለ ከተማዎች መገኛና ስማቸው 11

ምዕራፍ ሁለት 15

ሳይንስን መገንዘብ 15

2.1. ምግብና ጤና 16

2.2 የምግብ ጠቀሜታ 19

2.3. የግል ንፅህና አጠባበቅ 24

2.4. የቁስ አካል ሁኔታዊ ለውጥ (ጠጣር ፣ ፈሳሽና ጋዝ) 36

2.5. የብርሃን ጥቅም 40

ምዕራፍ ሦስት 44

ተፈጥሮአዊ አካባቢ 44

3.1. የክፍለ ከተማችን አየር ንብረት 45

3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች 49

3.3. የተፈጥሮ ሀብቶች ለክፍለ ከተማችሁ ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ 59

3.4. በትምህርት ቤትና በወረዳችን የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች 67

3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች 71

ምዕራፍ አራት 75
ማኅበራዊ አካባቢ 75
4.1 የባህል ብዝኀነት 76
4.2. በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች 84

ምዕራፍ አምስት 102
ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች 102
5.1 የመንገድ ደኅንነት 103
5.2 ኤች. አይ. ቪ / ኤድስ 112

መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር እድገት ዋና መሣሪያ ነው፡፡ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት በአካባቢያችን የሚገኙ ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮችን የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ነው የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ማንኛውንም ነገር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማለትም በሙከራ፣ በመመልከት ፣ በመመራመር፣ በተግባር በማየት በአካባቢያችን ስለሚገኙ ተፈጥሮአዊና ስው ሠራሽ ክስተቶች የሚያጠና ትምህርት ነው፡፡

አካባቢ ሳይንስ ትምህርት በአካባቢ ላይ ያተኮረ እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት አዳብሮ አካባቢን ከዚያም አልፎ ዓለምን ለማየት የሚያስችል የተቀናጀ የትምህርት ዘርፍ ነው፡ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የሰው ልጅ በሽታን ለመከላከል፣ በአካባቢው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ለመጠቀም ፣ የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ፣ የአኗኗር ዘይቤውን ዘመናዊ ለማድረግ አጠቃላይ መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ይጠቅመዋል፡፡ ስለዚህ ለአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ይህ የ3ኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ መፅሐፍ ተማሪዎች ጠያቂነትን፣ መፍትሄ መፈለግን፣ተመራማሪነትን፣ በተግባር ማሳየትን እንዲያዳብሩ ተደርጎ የተዘጋጀ መፅሐፍ ነው፡፡ መፅሐፉ ሲዘጋጅ የተለዩ የማስተማር ስነ-ዘዴዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህም፡- የቡድን ውይይት፣ ጥያቄና መልስ፣ ገለፃ፣ ፅብረቃ፣ የመስክ ጉብኝት (ምልከታ)፣ የተግባር ሥራ (ተግባራዊ ክንውን)፣ የሚና ጨዋታ፣ ድራማ፣ ጭውውት፣ ሰርቶ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

መፅሐፉ በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን እነሱም፡- የክፍለ ከተማችን መገኛ፣ ሳይንስን መገንዘብ፣ ተፈጥሮአዊ አካባቢ፣ ማኅበራዊ አካባቢና ተዕዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች የሚሉ ርዕሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የምዕራፉ ዋና ርዕሶች በውስጣቸው የተለያዩ ንዑስ ርዕሶችን ይዘዋል፡፡ እያንዳንዱ ምዕራፍ መግቢያን፣ የተለያዩ የመማር ብቃቶችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ የተግባር ሥራዎችን፣ የግል ሥራዎችን፣ ጭውውቶችን፣ ድራማዎችን ፣ የመልመጃ ጥያቄዎችን እና የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ይህ መፅሐፍ ብዙ ሥዕሎችን የያዘ ሲሆን በዋናነት በቡድን ውይይትና በተግባር ሥራዎች ላይ የተመሠረተ፤ በአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ላይ ያተኮረ እና አጠር ባሉ ዐረፍተ ነገሮች የተዘጋጀ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በእድሜያቸው ህፃን ስለሆኑ ብዙ ንግግር ከማዳመጥ ይልቅ ሥዕሎችን እየተመለከቱ፤ በተግባር እየሠሩ፣ በጋራ እየተወያዩ መማርን ይመርጣሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪዎች ከፅንሰ ሐሳብ ይልቅ በሥዕል የተደገፈ ትምህርት በቀላሉ መረዳት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ይህ መፅሐፍ ሲዘጋጅ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ የተከተለ ነው፡፡ ለምሳሌ፦ የቡድን ውይይት መኖሩ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚያዩዋቸው ነገሮች በመነሳት የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያንፀባርቁ ዕድል ይሰጣቸዋል፤ የመናገር ችሎታቸውን ያዳብራሉ ፣ከሌሎች ተማሪዎችና ሰዎች ጋር የመግባባት አቅም ይጨምርላቸዋል፤ ፍርሃትን ለማስወገድ ይጠቅማቸዋል፡፡ የመምህሩ/ዋ ኃላፊነትም የመማር ማስተማሩን ሥራ የበላይ ሆኖ በመቆጣጠርና በመምራት እንዲሁም በማገዝ ተማሪዎች የራሳቸውን ሐሳብ እንዲገልፁና ሪፖርት እንዲያደርጉ ማስተባበር ነው፡፡ በእያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ ስር የተቀመጡት የመወያያ ጥያቄዎችና የተግባር ሥራዎች የእለቱ ትምህርት መንደርደሪያ ሐሳቦች ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችና ተግባራት በእለቱ ትምህርት በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ሀሳቦች በመሆናቸው ተማሪዎቹ በውይይቱ ወቅት ስለ ንዑስ ርዕሱ ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ሐሳብ በየቡድናቸው በአንድ ተወካይ ተማሪ አማካኝነት እንዲያቀርቡ በማድረግ በሚያቀርቡሩት ሐሳብ ላይ መምህሩ/ዋ ማበረታቻና ማስተካከያ በመስጠት ተማሪዎቹ መያዝ የሚጠበቅባቸውን ዕውቀት እንዲይዙ ይጠቅማል፡፡በውይይቱና ተግባራት በሚሠሩበት ወቅት የሚጠበቀውን ውጤት ያላስመዘገቡ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ እገዛ ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹን ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር አጣምሮ ማስቀመጥ፣ የምክር አገልግሎት መስጠት፣ ከወላጆቻቸው ጋር በመወያየት ድጋፍና ክትትል እንዲያደርጉላቸው ማድረግና ልዩ ፍላጎታቸውን በመረዳት የተለያዩ የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎችን በመጠቀም መፍትሄ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፡፡

ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ናሙና

የትምህርት ቤቱ ስም_____የመምህሩ ስም_____

የትምህርት ዓይነት- አካባቢ ሳይንስ ትምህርቱ የሚሰጥበት ቀን ከ_____እስከ_____

የክፍል ደረጃ - 3ኛ የክፍለ ጊዜ ርዝመት፦ 45 ደቂቃ

የትምህርቱ ዋና ርዕስ - የተፈጥሮ ሀብቶች

የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎች፦ ጥያቄና መልስ፣ የቡድን ውይይት እና ገለፃ

የትምህርቱ ንዑስ ርዕስ - አፈር

የትምህርቱ ዓላማ፦ ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማሩ በኃላ፦

- **የአፈር ምንነትን ይገልፃሉ፡፡**
- **የአፈርን ጥቅም ይዘረዝራሉ፡፡**

ቀን	ይዘት	ጊዜ	የመምህሩ ተግባር	የተማሪው ተግባር	መርጃ መሳሪያዎች	አስተያየት
	አፈር	6 ደቂቃ	መግቢያ፦ አፈር ማለት ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅ	• ስለአፈር ያላቸውን ቅድመ ዕውቀት መናገር	• የአፈር ሥዕልና ፖስተር • የአፈር ጥቅምን የሚያሳዩ ሥዕሎች ፣ ፖስተሮችና ፎቶግራፎች	
		25ደቂቃ	አቀራረብ"፦ በርዕሱ ስር የሚገኘውን የመወያያ ጥያቄ በየቡድኑ እንዲወያዩ ማድረግ • የተወያዩበትን ሐሳብ በተወካያቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ማድረግ • ካቀረቡበት ሀሳብ በመነሳት ስለ አፈር ምንነትና ጥቅም ገለፃ መስጠት • አጭር ማስታወሻ መስጠት	• በቡድን መወያየት • የተወያዩበትን ሀሳብ ማቅረብ • ማዳመጥ • ማስታወሻ መውሰድ		
		4 ደቂቃ	ማጠቃለያ፦ስለ አፈር የተማሩትን ማጠቃለያ መስጠት	•ያልገባቸውን ይዘት መጠየቅ		
		5ደቂቃ	ምዘና፦.አፈር ምንድን ነው? አፈር ምን ጥቅም ይሰጣል?	• ለጥያቄዎች መልስ መስጠት		

የአዘጋጅ መ/ር ስም_____

የአዘጋጅ መ/ር ስም_____የት/ክፍል ተጠሪ መ/ር ስም_____የሥርዓተ ት/ት ም/ር መ/ር ስም_____

ፊርማ_____ ፊርማ_____ ፊርማ_____

ቀን_____ ቀን_____ ቀን_____

ምዕራፍ አንድ

የክፍለ ከተማችን መገኛ

የክፍለ ጊዜ ብዛት-34

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ለሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን በዝርዝር ለተማሪዎች የሚያቀርብና የሚያስተምር ነው።

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለአንጻራዊ መገኛ ምንነት፣ ስለፍጹማዊ መገኛ ምንነት፣ስለክፍለ ከተሞች አንጻራዊ መገኛ፣ ስለክፍለ ከተሞች ፍጹማዊ መገኛ፣ በክፍለ ከተሞች ስለሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛና የክፍለ ከተሞች አዋሳኝ ከፍለ ከተሞች መገኛና ስማቸው ይማራሉ። መምህር! ለተማሪዎች ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠርና ተማሪዎችን በመምራት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ማጠቃለያ ሀሳቦችን በመስጠት የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ጥረት ያድርጉ።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፡-

- አቅጣጫን የመለየት ክህሎት ያዳብራሉ።
- ሥዕላትንና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎችጋር ለመግባባት ፈቃደኝነታችሁን ያሳያሉ::
- የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን ይገልጻሉ።
- የፍጹማዊ መገኛን ምንነት ይገልጻሉ።
- የክፍለ ከተማቸውን አንጻራዊ መገኛ ያመለክታሉ።
- በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የክፍለ ከተማቸውን መገኛ ያመለክታሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ለማመልከት ኬክሮስና ኬንትሮስን ይጠቀማሉ
- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ በመጠቀም በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ቦታዎችን ያመለክታሉ።

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

1.1. **የአንጻራዊ መገኛ ምንነት**

1.2. **የፍጹማዊ መገኛ ምንነት**

1.3. **የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ**

1.4. **የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ**

1.5. **በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ**

1.6. **የክፍለ ከተማችን አዋሳኝ ክፍለ ከተሞች መገኛና ስማቸው**

1.1. አንጻራዊ መገኛ ምንነት

ክፍለ ጊዜ--4

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-

- **የአንጻራዊ መገኛ ምንነትን ይገልጻሉ፡፡**

- **የትምህርቱ ጭብጥ**

ማንኛውም ሰው አንጻራዊ መገኛን በመጠቀም በቀላሉ አንድ ቦታ የት እንደሚገኝ ማወቅና ማሳየት ይችላል፡፡ አንጻራዊ መገኛ አቅጣጫን በመጠቀም የአንድ ቦታን መገኛ ከአካባቢው ካሉ ነገሮች በማነጻጸር የት እንደሚገኝ የምናመለክትበት ዘዴ ነው፡፡

- **የትምህርት መርጃ መሣሪያ፡-**
  - **ዐራቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎችን በቻርት በማዘጋጀት መጠቀም**
- **የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች፡-**
  - **የተግባር ሥራ**
  - **ገለጻ**
  - **ጥያቄና መልስ**
  - **ዕብረቃ**
- **ቅድመ ዝግጅት**
  - **መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡**
  - **ዐራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሚያሳይ ቻርት ያዘጋጁ፡፡**
- **የመማር ማስተማር ሂደት**

መግቢያ

የአንጻራዊ መገኛ ምንነትን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

የአንባራዊ መገኛ ምንነትን

- ከገለጻው በፊት ስለዐራቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች ይጠይቋቸውና የቀረበውን የተግባር ስራ ያሰሯቸው፡፡
- የተግባር 1. ጥያቄን ተማሪዎች እንዲሰሩና መልሱን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
- አንጻራዊ መገኛ አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ብቻ አይጠቀምም፡፡ ሌሎችንም የአቅጣጫ ክፍሎች ማለትም ሰሜን ምሥራቅ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ የመሣሰሉትን ይጠቀማል፡፡ አንጻራዊ መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም አንድ ቦታ የት እንደሚገኝ አካባቢው ካሉ ታዋቂ ነገሮች በመነሳት በማነጻጸር የምንገልጽበት ዘዴ ነው፡፡
- አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በተግባር ያሳዩዋቸው፡፡

ተማሪዎች አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች ተጠቅመው በስራቸው ያሉትን ነገሮች መገኛ እንደያሳዩ ያድርጉ፡፡

ተግባር 1. መልስ

➢ ተማሪዎች በጥያቄው መሰረት መልሳቸውን በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም እርስዎ የአካል ክፍልዎትን በመጠቀም አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በተግባር ለተማሪዎች ያሳዩዋቸው፡፡

ተግባር 2. መልስ

1. በስተምሥራቅ
2. በስተ ደቡብ
3. በስተምዕራብ

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- አራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
- አንጻራዊ መገኛ ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅ፡፡
- ተማሪዎች አንጻራዊ መገኛን በመጠቀም ቦታዎችን እንዲያሳዩ መጠየቅ፡፡

ማጠቃለያ

አራቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች የሚባሉት ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ አቅጣጫዎች የአንድን ቦታ አንጻራዊ መገኛ ለማመልከት ይጠቅማሉ፡፡

አንጻራዊ መገኛ ማለት አቅጣጫን በመጠቀም የአንድን ቦታ መገኛ በአካባቢው ካሉ ታዋቂ ቦታዎች በማነጻጸር የምንገልጽበት ዘዴ ነው፡፡

1.2. የፍጹማዊ መገኛ ምንነት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተመሩ በኋላ፡-

- **የፍፁማዊ መገኛ ምንነትን ይገልጻሉ፡፡**
    - **የትምህርቱ ጭብጥ**

ፍጹማዊ መገኛ ማለት ኬክሮስና ኬንትሮስ ልኬትን በመጠቀም የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ የሚያመለክት ነው፡፡

ኬክሮስ ማለት ከምድር ወገብ ተነስቶ ወደ ሰሜን 90 ዲግሪ እና ወደ ደቡብ 90 ዲግሪ የሚለኩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 180 ዲግሪ ይለካሉ፡፡

የምድር ወገብ መሬትን እኩል ቦታ ሰሜንና ደቡብ በማለት የሚከፍል መነሻ ቦታ ነው፡፡

ተጓዳኝ መስመር ከምድር ወገብ በመነሳት ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር ነው፡፡

ኬንትሮስ ማለት ከመነሻ ዋልታ 180 ዲግሪ ወደ ምሥራቅና 180 ዲግሪ ወደ ምዕራብ የሚለኩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 360 ዲግሪ ይለካሉ፡፡

መነሻ ዋልታ መሬትን እኩል ቦታ ምሥራቅና ምዕራብ በማለት የሚከፍል መነሻ ቦታ ነው፡

- **የትምህርት መርጃ መሣሪያ፤-**
    - **ሉልና ካርታ ይጠቀሙ፡፡**
        - **የማስተማር ስነ- ዘዴ**
    - **የቡድን ውይይት**
    - **ጥያቄና መልስ**
    - **ገለጻ**
    - **ዕብረቃ**
- **ቅድመ ዝግጅት**
    - **መምህር የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡**
    - **ሉልና ካርታ ያዘጋጁ፡፡**

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የፍጹማዊ መገኛ ምንነትን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርት አቀራረብ
  - የፍጹማዊ መገኛ ምንነት
  - ከገለጻው በፊት የመወያያ ጥያቄውን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን እዲያንፀባርቁ ያድርጉ፡፡
  - ካርታ ወይም ሉልን በመጠቀም ኬክሮስን፣ ኬንትሮስን፣የምድር ወገብን፣መነሻ ዋልታን፣ተጓዳኝ መስመሮችንና ቋሚ መስመሮችን ያሳዩ፡፡

ስለርዕሱ ማስታወሻ በማዘጋጀት ለተማሪዎች ይስጡ፡፡ ተማሪዎች የተዘጋጀውን ማስታወሻ እንዲዕፉ ያድርጉ፡፡

ውይይት 1. መልስ

1. ፍጹማዊ መገኛ ማለት ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ የሚያመለክት ነው፡፡
2. ኬክሮስ ማለት ከምድር ወገብ ተነስቶ ወደ ሰሜን 90 ዲግሪ እና ወደ ደቡብ 90 ዲግሪ የሚለካ ነው፡፡
3. ኬንትሮስ ማለት ከመነሻ ዋልታ 180 ዲግሪ ወደ ምሥራቅና 180 ዲግሪ ወደ ምዕራብ የሚለካ ነው፡፡

ውይይት 2 መልስ

1. ቋሚ መስመር
2. መነሻ ዋልታ(ፕራይም ሜሪዲያን)
3. የምድር ወገብ
4. ተጓዳኝ መስመር

- ምዘናና ግምገማ
    - ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡
    - ፍጹማዊ መገኛ ማለት ምን ማለት ነው?
    - የአንድን ቦታ ፍጹማዊ መገኛ ለማመልከት የሚያስፈልጉትን ተናገሩ፡፡
    - መሬትን ሰሜናዊና ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍለው ማን ነው?
    - መሬትን ምሥራቃዊና ምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ በማለት እኩል ቦታ የሚከፍለው ማን ነው?
    - ቋሚ መስመርና ተጓዳኝ መስመር ልዩነታቸውን አብራሩ፡፡

ማጠቃለያ

- ፍጹማዊ መገኛ ማለት ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ የሚያመለክት ነው፡፡
- ኬክሮስና ኬንትሮስ
- የምድር ወገብ
- መነሻ ዋልታ
- ተጓዳኝ መስመር ከምድር ወገብ በመነሳት ተመሳሳይ ኬክሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር ነው፡፡
- ቋሚ መስመር ከመነሻ ዋልታ በመነሳት ተመሳሳይ ኬንትሮስ ያላቸውን ቦታዎች የሚያገናኝ የሀሳብ መስመር ነው፡፡

መልመጃ 1. መልስ

ሀ. 1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት

ለ. 1. ለ 2. መ 3. ሀ 4. ሐ

ሐ. 1. የምድር ወገብ

2. መነሻ ዋልታ/ ግሪኒውች ሜሪዲያን/ ዜሮ ዲግሪ ኬንትሮስ

መ. 1. ከመነሻ ዋልታ ወደ ምሥራቅ 180 ዲግሪ እና ወደ ምዕራብ 180 ዲግሪ ይለካሉ፡፡ በአጠቃላይ 360 ዲግሪ ይለካሉ፡፡

2. ከምድር ወገብ ወደ ሰሜን 90 ዲግሪ እና ወደ ደቡብ 90 ዲግሪ ይለካሉ፡፡ በአጠቃላይ 180 ዲግሪ ይለካሉ፡፡

1.3. የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ

ክፍለ ጊዜ--6

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-

- የክፍለ ከተማቸውን አንጻራዊ መገኛ ይገልጻሉ፡፡
- የትምህርቱ ጭብጥ

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ዐስራ አንድ ክፍለ ከተሞች አሉ፡፡እነርሱም፡- ለሚ ኩራ፣ልደታ ፣ ቂርቆስ፣ ቦሌ፣ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣አራዳ፣አቃቂ ቃሊቲ፣ አዲስ ከተማ ፣ ኮልፌቀራንዮ ፣የካ እናጉለሌ ክፍለ ከተማ ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ አንጻራዊ መገኛ አላቸው፡፡አንጻራዊ መገኛቸውን ለመናገርና ለማሳየት አቅጣጫን መጠቀም ይኖርብናል፡፡ ከዚህ በመነሳት

- ጉለሌና የካ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ሰሜናዊ ክፍሎች ናቸው፡፡

- አራዳ፣ ልደታና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች መሀል የአዲስ አበባ ክፍሎች ናቸው፡፡

- ንፋስ ስልክ ላፍቶና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ደቡባዊ ክፍሎች ናቸው::

- ኮልፌ ቀራኒዮ እና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ምዕራባዊ ክፍል ናቸው፡፡

- ቦሌና ለሚ ኩራ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ምስራቃዊ ክፍሎች ናቸው፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያ፡-
  - ዐራቱ መሰረታዊ አቅጣጫዎች
  - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካርታ
- የማስተማር ስነ-ዘዴ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - ፅብረቃ
  - ጥያቄና መልስ
- ቅድመ ዝግጅት
  - መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡
  - መምህር! ዐራቱን መሰረታዊ አቅጣጫዎች በግራፍ ወረቀት ላይ ያዘጋጁ፡፡
  - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካርታ ያዘጋጁ፡፡
- መማር ማስተማር ሂደት
  - መግቢያ
  - የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ ንዑስ ርዕስ በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት

መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

- የትምህርቱ አቀራረብ
- የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ
- መምህር! ማብራሪያ ከመስጠትዎ በፊት በቀረቡት የተግባር 3 ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች መልሳቸውን እንዲያብራሩ ያድርጉ።
- መምህር! የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ካርታን ክፍል ውስጥ ይዞ በመገኘት በተግባር 3 ጥያቄዎች ላይ ገለጻ ያድጉላቸው።
- ተማሪዎች የራሳቸውን ክፍለ ከተማ በካርታ ላይ እንዲያመለክቱ ያድርጉ።

መምህር ስለክፍለ ከተሞች አንጻራዊ መገኛ ለተማሪዎች ማስታወሻና ማብራሪያ ይስጧቸው።

ውይይት 3. መልስ

ተማሪዎች የሚናገሩት የክፍለ ከተማቸው ስምና ትምህርት ቤታቸው የሚገኝበት ክፍለ ከተማ አንጻራዊ መገኛ እንደሚኖሩበት ክፍለ ከተማ የተለያየ ስለሚሆን ሲያመለክቱና ሲናገሩ ስህተት ከሰሩ ድጋፍና ማስተካከያ ያድርጉላቸው።

ተግባር 3. መልስ

1. ተማሪዎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንድፍ ካርታ እነዲያዘጋጁ ያድርጉ። ከዚያም

   የሰሩትን ንድፍ ካርታ ይረከቧቸው።

2. - ጉለሌና የካ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ሰሜናዊ ክፍሎች ናቸው።

   - አራዳ፣ ልደታ፣ ቂርቆስና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች መሀል የአዲስ አበባ ክፍሎች

     ናቸው።

- ንፋስ ስልክ ላፍቶና አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች የአዲስ አበባ ደቡባዊ ክፍሎች ናቸው።
- ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ምዕራባዊ ክፍል ነው።

3. ተማሪዎች የሚኖሩበትን ክፍለ ከተማ ስምና አንጻራዊ መገኛውን በካርታ ላይ እንዲያመለክቱ ያድርጉ። ተማሪዎች በካርታ ላይ ሲያመለክቱ ስህተት ካልባቸው ስህተታቸውን ያስተካክሉ።

- ምዘናና ግምገማ
  - ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የክፍለ ከተማቸውን አንጻራዊ መገኛ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
- መልመጃዎችን መስጠት

ማጠቃለያ

መምህር! የተማሪዎች የሚኖሩበትን ክፍለ ከተማ አንጻራዊ መገኛ በካርታ ላይ ያሳዩዋቸው:: የሁሉም ክፍለ ከተሞች አንጻራዊ መገኛ የተለያየ መሆኑን ለተማሪዎች ይንገሯቸው፡፡

መልመጃ 2. መልስ

ሀ. 1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. ሐሰት

ለ. 1. ሰሜን፣ ደቡብ፣ መሥራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡

2. የተማሪዎች መልስ እንደሚኖሩበት ክፍለ ከተማ ይለያያል፡፡

3. ለሚ ኩራና ቦሌ ናቸው፡፡

1.4 የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ

ክፍለ ጊዜ--6

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማሩ በኋላ፡-

- የክፍለ ከተሞችን ፍጹማዊ መገኛ ይገልጻሉ፡፡
- የትምህርቱ ጭብጥ

ከላይ በ1.3 ንዑስ ርዕስ ስር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ስለሚገኙ ክፍለ ከተሞች ስምና አንጻራዊ መገኛ ማየት ችለናል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ ስለክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም ማመልከት ይቻላል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያ
  - ኬክሮስና ኬንተሮስ ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካርታ ይጠቀሙ፡፡
- የማስተማር ስነ-ዘዴ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - ዕብረቃ
  - ጥያቄና መልስ
- ቅድመ ዝግጅት
  - መምህር የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡
  - ኬክሮስና ኬንተሮስ ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካርታ ያዘጋጁ፡፡

- መማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ ንዑስ ርዕስ በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርት አቀራረብ

የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ

መምህር! ማብራሪያ ከመስጠትዎ በፊት በቀረቡት የተግበር ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

መምህር! ኬክሮስና ኬንትሮስ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተደደር ካርታን ክፍል ውስጥ ይዞ በመገኘት ገለጻ ያድጉላቸው፡፡

ተማሪዎች የራሳቸውን ክፍለ ከተማ ፍጹማዊ መገኛ በካርታ ላይ እንዲያመለክቱ ያድርጉ::

መምህር! ስለክፍለ ከተሞች ፍጹማዊ መገኛ ለተማሪዎች ማስታወሻና ማብራሪያ ይስጧቸው::

ተግባር 4. መልስ

ተማሪዎች የሚያሳዩት የክፍለ ከተሞች ፍጹማዊ መገኛ እንደሚኖሩበት አካባቢ የተለያየ ስለሚሆን ሲያመለክቱ ስህተት ከሰሩ ድጋፍና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የክፍለ ከተማችሁን ፍጹማዊ መገኛ ለማመልከት ምን ትጠቀማላችሁ?
- የክፍለ ከተማችሁን ፍጹማዊ መገኛ አሳዩ፡፡

- ማጠቃለያ

መምህር! የተማሪዎች የሚኖሩበትን ክፍለ ከተማ ፍጹማዊ መገኛ በካርታ ላይ ያሳዩዋቸው::

የክፍለ ከተሞች ፍጹማዊ መገኛ ለመናግር ኬክሮስና ኬንትሮስን መጠቀም ይኖርብናል::

የሁሉም ክፍለ ከተሞች ፍጹማዊ መገኛ የተለያየ መሆኑን ለተማሪዎች በካርታ ላይ ያሳዩዋቸው፡፡

1.5 በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ

ክፍለ ጊዜ--6

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ

- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም ያመለክታሉ፡፡
    - የትምህርቱ ጭብጥ
- በእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ውስጥ ዋና ዋና ቦታዎች አሉ፡፡እነርሱም፤-አደባባዮች፣ ሐውልቶች፣ ቤተ-እምነቶች፣መንገዶች፣ተቋማት(ት/ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ወረዳዎች)ና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የእነዚህን ዋና ዋና ቦታዎች ፍጹማዊ መገኛ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም ማሳየትና መናገር ይቻላል፡፡
    - የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች
    - ኬክሮስና ኬንትሮስ ያሉት ዋና ዋና ቦታዎች ንድፍ ካርታ
    - ዋና ዋና ቦታዎችን የያዘ ፖስተር፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት
    - የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች
    - የቡድን ውይይት
    - ገለጻ
    - ፅብረቃ
    - የመስክ ጉብኝት
        - ቅድመ ዝግጅት
    - መምህር! የንዑስርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡
    - ኬክሮስና ኬንትሮስ ያሉት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች ካርታ ያዘጋጁ፡፡
    - ዋና ዋና ቦታዎችን የሚያሳይ ፖስተር፣ ፎቶ ግራፍና ቻርት ያዘጋጁ፡፡
        - የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

- በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ ንዑስ ርዕስ በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡
- የትምህርት አቀራረብ
- በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች
- መምህር! ማብራሪያ ከመስጠትዎ በፊት በቀረቡት የግል ስራ ጥያቄዎች ላይ

ተማሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጉ።የተለያዩ ዋና ዋና ቦታዎችን የሚያሳይ ፖስተር፣ ፎቶ ግራፍ፣ቻርት፣ንድፍ ካርታ በመጠቀም ገለጻ ያድርጉላቸው።

- ኬክሮስና ኬንትሮስ ያለው ዋና ዋና ቦታዎችን የያዘን ንድፍ ካርታ በመጠቀም ለተማሪዎች ፍጹማዊ መገኛቸውን ያሳዩ። ስለ ዋና ዋና ቦታዎች ፍጹማዊ መገኛ ለተማሪዎች ማስታወሻ ይስጧቸው።
-

ተግባር 5. መልስ

- ተማሪዎች በተሰጣቸው የግል ሥራ መሰረት በክፍለ ከተማቸው የሚገኙትን ዋና ዋና ቦታዎች ፍጹማዊ መገኛ እንዲያመለክቱ ያድርጉ። ሲያሳዩ ስህተት ካለባቸው ድጋፍና ማስተካከያ ይስጧቸው።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል።

- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች ተናገሩ።
- በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የዋና ዋናዎቹን ፍጹማዊ መገኛ አመልክቱ።
- ማጠቃለያ
- በክፍለ ከተማዎች የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን ለምሳሌ ት/ቤት፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ወረዳ የመሳሰሉትን ለአብነት ይንገሯቸው። በክፍለ ከተማዎች የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን ፍጹማዊ መገኛ በተግባር ያሳዩዋቸው።

1.6 የክፍለ ከተማችን አዋሳኝ ክፍለ ከተማዎች መገኛና ስማቸው

ክፍለ ጊዜ--6

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያን በመጠቀም በክፍለ ከተማችው የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን ያመለክታሉ።

- የትምህርቱ ጭብጥ

የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ማለት ሰዎች ማግኘት የሚፈልጉትን ቦታ የጎግል ድህረ-ገፅ ተጠቅመው በመፈለግ ቦታው በቀላሉ የት እንደሚገኝ የሚያመለክት መተግበሪያ ነው።የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ በመጠቀም በክፍለ ከተሞች የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎችን በቀላሉ የት እንደሚገኙ ማወቅ ይቻላል።

የጎግል ካረታ መፈለጊያ መተግበሪያ ጥቅም

- የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ ይነግረናል፡፡
- ተጠቃሚዎች ጓደኛዊነት ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡
- ለምንጠይቀው ጥያቄ በፍጥነት መልስ ይሰጠናል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያ
  - ጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ
  - ዋና ዋና ቦታዎችን የሚያሰይ ፖስተር፣ ፎቶ ግራፍና ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- የማስተማር ስነ-ዘዴ
  - ገለጻ
  - ፅብረቃ
  - ሰርቶ ማሳየት
  - ጥያቄና መልስ
- የትምህርት ቅድመ ዝግጅት
  - መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡
  - የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያን ያዘጋጁ፡፡
  - በክፍለ ከተሞች የሚገኙትን ዋና ዋና ቦታዎች ቀድመው ይወቁ፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

  - የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ ንዑስ ርዕስ በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡
- የትምህርቱ አቀራረብ

- የክፍለ ከተማችን አዋሳኝ ክፍለ ከተማዎች መገኛና ስማቸው
- መምህር! ማብራሪያ ከመስጠትዎ በፊት በቀረቡት የተግበር ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች የጎግል ካርታ መተግበሪያ እንዲጠቀሙ አጠቃቀሙን ያሳዩዋቸው፡፡
- ተመሪዎች የጎግል ካርታ መተግበሪያ ተጠቅመው ዋና ዋና ቦተዎችን እንዲያሳዩ የድርጉ:: ስለ ጎግል ካርታ መተግበሪያ ምንነትና ጥቅም ማስታወሻ ይስጡዋቸው፡፡

ተግባር 6. መልስ

በተግባር ጥያቄው መሰረት ተማሪዎች የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያን ተጠቅመው ቁልፍ ቦታዎችን መገኛ እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ስህተት ካላቸው ድጋፍና ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

- ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡
  - ጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ማለት ምን ማለት ነው?
  - ጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ለምን ይጠቅማል?

- ማጠቃለያ

- የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ማለት ሰዎች ማግኘት የሚፈልጉትን ቦታ የጎግል ድህረ-ገፅ ተጠቅመው በመፈለግ ቦታው በቀላሉ የት እንደሚገኝ የሚያመለክት መተግበሪያ ነው፡፡

የጎግል ካረታ መፈለጊያ መተግበሪያ ጥቅም

- የአንድን ቦታ ትክክለኛ መገኛ ይነግረናል፡፡
- ተጠቃሚዎች ግንኙነታቸው እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡
- ለምንጠይቀው ጥያቄ በፍጥነት መልስ ይሰጠናል፡፡

የማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

ሀ. 1. እውነት ለ. 1. ሐ
2. ሐሰት 2. መ
3. እውነት 3. መ
4. እውነት 4. መ
5. እውነት

ሐ. 1. የምድር ወገብ
2. ተጓዳኝ መስመር

መ. 1. በጥያቄው መሰረት የተማሪዎችን መልስ በማየት ማስተካከያ ካለው ይስጡ፡፡
2. - የማናውቀውን ቦታ በአጭር ጊዜ የት እንደሚገኝ ለማወቅ ይረዳል፡፡
- ቦታውን ለማግኘት የምናወጣውን ጉልበትና ሀብት ይቀንሳል፡፡
- መረጃን በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል፡፡
- ተጠቃሚዎች ግንኙነታቸው እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ሳይንስን መገንዘብ

የተመደበው ክፍለ ጊዜ ብዛት ፦ 42

መግቢያ

ተማሪዎች በሁለተኛ ክፍል ትምህርት ስለምግብ ምንነትና ጥቅሞች፣ ስለብርሃን ምንነት፣ስለ ብርሃን ምንጮችና ስለ ቁስ አካል ባህሪያት ተምረዋል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ምግብና ጤና፣ የምግብ ምድቦች፣ የተበከለ ምግብ መንስኤና መከላከያ መንገድ፣ ስለግል ንጽህና ጠቀሜታ፣ የግል ንጽህና ባንጠብቅ በሌላ ሰው ላይ ያለውን ተጽዕኖ ፣ በህመምተኛና በጤነኛ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት፣ ስለአካላዊ ሁነቶች ባህሪያትን ፍቺዎች፣ ስለብርሃን ምንጮችና ጥቅሞቻቸው ይማራሉ።

እባክዎ መምህር! ተማሪዎቹን በውይይቱ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው። ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ እስኪያጠናቅቁ ድረስ የእያንዳንዱን አጥጋቢ የመማር ብቃት በተከታታይ ጊዜ ይገምግሙ። በግምገማው ውጤት መሰረት ከሚጠበቀው አጥጋቢ የመማር ብቃት በላይ የሚሰሩ ተማሪዎችን በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ለምሳሌ በማመስገን፣ በመሸለም የበለጠ እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ነገር ግን ከአጥጋቢ የመማር ብቃት መለኪያ በታች ለሚያመጡ ተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍና ርዳታ ያድርጉላቸው። በክፍል ውስጥ የተለየ ትኩረት ይስጧቸው።

በእረፍት ሰዓትና ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪም ተጨማሪ የመማሪያ ጊዜ ሊሰጧቸው ይገባል።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን ይለያሉ።
- ምግቦችን በአራት መሠረታዊ ምድቦች ይከፍላሉ።
- የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅሕና አጠባበቅ መንገዶችን ይለያሉ።
- የንጽህና መጠበቂያ መንገዶችን ይገልጻሉ።
- የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች ባሕሪያትን በመስጠት የቁስ አካላትን(የጠጣር፣ ፈሳሽና የጋዞች) የሁነታ ለውጥ ይገልፃሉ።
- የብርሃንን ጥቅሞች ይዘረዝራሉ።

የምዕራፉ ይዘቶች፦

2.1. ምግብና ጤና

2.2. የምግብ ጠቀሜታ

2.3. የግል ንፅሕና አጠባበቅ

2.4. የቁስ አካል ሁነታዊ ለውጥ

2.5. የብርሃን ጥቅም

2.1. ምግብና ጤና

የተመደበው ክፍለጊዜ፦ 8

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- **ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን ይለያሉ።**
- **የትምህርቱ ጭብጥ፦**

ጤናማ የሆነ ምግብ ማለት ከበሽታ አምጪ ተህዋስያንና ከሌሎች ጎጂ ነገሮች የፀዳ ምግብ ነው። ጤናማ የሆነ ምግብ ያልተለመደ ጠረንና ጣዕም እንዲሁም ለዕይታ የተለየ መልክ የለውም። ምሳሌ፦ ያልተበላሸ ወጥ፣ ያልሻገተ እንጀራ፣ ንፁህ እንቁላል፣ ንፁህ ፍራፍሬ፣ የፈላ ወተት፣ የበሰለ ሥጋ እና የመሳሰሉት ናቸው።

ጤናማ ያልሆነ ምግብ ማለት በበሽታ አምጪ ተህዋስያንና በሌሎች ጎጂ ነገሮች የተበከለ ምግብ ነው። ጤናማ ያልሆነ ምግብ ያልተለመደ ጠረንና ጣዕም እንዲሁም ለእይታ የተለየ መልክ ሊፈጥር ይችላል። ለምሳሌ የገማ እንቁላል፣ የተበላሸ የምስር ወጥ፣ የሻገተ እንጀራ፣ የተበላሸ ሙዝና የመሳሰሉት ናቸው። የምንመገበው ምግብ በጥንቃቄ ካልተያዘ በዐይን በማይታዩ ጥቃቅን ተህዋስያን ሊበከል ይችላል። በመሆኑም ምግብ ሲዘጋጅም ሆነ ሲቀመጥ በጥንቃቄ መሆን አለበት።

- **የትምህርት መርጃ መሣሪያ**

- ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ የምግብ አይነቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ይጠቀሙ።

- **የመማር ማስተማር ዘዴዎች፦**
  - **- የቡድን ውይይት**
  - **- ገለፃ**
  - **- ጥያቄና መልስ**
  - **- አጭር ጭውውት**
  - **- ምልከታ**
- **ቅድመ ዝግጅት**

- መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- ስለጤናማ ምግቦችና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መፃሕፍትን በማንበብና ሰዎችን በመጠየቅ ይዘጋጁ፡፡

-ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ የምግብ አይነቶችን የሚያሳዩ ስዕላዊ መግለጫዎችና ፎቶግራፎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

-ተማሪዎቹ የጤናማ ምግቦችና መጠጦችን አዘገጃጀት፣ አቀማመጥና አመጋገብ የሚያሳይ አጭር ጭውውት አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ይስጧቸው፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ምግብና ጤና ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

ጤናማ የሆኑ ምግቦች ና መጠጦች ማለት ምን ማለት ነዉ?

ጤናማ የሆኑ ምግቦችና መጠጦችን መመገብ ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ተማሪዎቹን በቡድን ውስጥ በመመደብ ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችንና መጠጦችን በተመለከተ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከትና በመወያየት እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

መምህር!ተማሪዎቹ በቡድን በመሆን የጤናማ ምግቦችና መጠጦችን አዘገጃጀት፣ አቀማመጥና አመጋገብ የሚያሳይ አጭር ጭውውት አዘጋጅተው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ እድል ይስጧቸው፡፡

በመጨረሻም ጤናማ ምግቦችን የሚያሳዩ ፎቶ ግራፎች ፣ ፖስተሮችና ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ገለፃና ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡

ተግባር 1 መልስ

1. አራት ተማሪዎች ሆነው ቡድን በመመስረት ሁለቱ ተማሪዎች እንደ እናትና አባት በመሆን ሁለቱ ተማሪዎች ደግሞ እንደ ወንድና ሴት ልጆች በመሆን ጭውውቱን በሚከተለው መሰረት ያቅርቡ:: ሁለቱ ልጆች እጃቸውን በሳሙና ታጥበው ንፅሕናው የተጠበቀ እቃ በመጠቀምና ንፁህ ቦታ ላይ ምግብ እንደሚያዘጋጁ አስመስለው ያቅርቡ፡፡ ያዘጋጁትንም ምግብ ከድነውን ንፁህ ቦታ ሲያስቀምጡ ያሳዩ፡፡ እናትና አባታቸውም ከስራ ሲመለሱ እጃቸውን በማስታጠብ እነሱም እጃቸው በደንብ በመታጠብ ምግቡን አቅርበው በጋራ ሲመገቡ የሚያሳይ ጭውውት ያቅርቡ፡፡ የጭውውቱ ዓላማ ምግብን ስናዘጋጅና ስንመገብ እንዳይበከል በማድረግ ጤናማ ምግብ መመገብ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡ ለማድረግ ነው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

  ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

  - ጤናማ ምግብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መጠየቅ
  - ጤናማ ምግቦችንና ጤናማ ያልሆኑምግቦችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡

- ማጠቃለያ

ጤናማ ምግብ ማለት ከበሽታ አምጪ ተህዋስያንና ከሌሎች ጎጂ ነገሮች ነፃ የሆነ ምግብ ነው፡፡ያልተበላሸ ወጥ ፣ ያልሻገተ እንጀራ ፣ ንፁህ እንቁላል ፣ ንጹህ ፍራፍሬ ፣ የፈላ ወተት ፣ የበሰለ ሥጋ እና የመሳሰሉት ጤናማ ምግቦች ናቸው፡፡ የገማ እንቁላል ፣ የተበላሸ የምስር ወጥ ፣ የሻገተ እንጀራ ፣ የተበላሸ ሙዝና የመሳሰሉት ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ናቸው፡፡ምግብ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡ስለዚህ የምንመገበው ምግብ ጤናማ ምግብ መሆን አለበት፡፡

የመልመጃ 2.1. መልሶች

ሀ) 1. እውነት 2.እውነት 3.እውነት 4.እውነት 5.ሐሰት

ለ) 1. ጤናማ የሆነ ምግብ ማለት ያልተለመደ ጠረንና ጣዕም እንዲሁም ለዕይታ የተለየ መልክ የሌለው ምግብ ነው።

2. ጤናማ ያልሆነ ምግብ ማለት በሽታ አምጪ ተህዋስያንና በሌሎች ጎጂ ነገሮች የተበከለ ምግብ ነው።

3. ለተለያዩ በሽታዎች ይዳርጋል።

4. ምግብን በማቀዝቀዣ ውስጥ ማቆየት፣ማድረቅ ፣ጨው መነስነስና የመሳሰሉት ናቸው።

ሐ.

ባህርያት	ልዩነታቸው	
	ጤናማ ምግቦች	ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች
ያልተለመደ ሽታ	የላቸውም	አላቸው
ያልተለመደ ጣዕም	የላቸውም	አላቸው
ለእይታ የተለየ መልክ	የላቸውም	አላቸው

2.1. የምግብ ጠቀሜታ

የተመደበው ክፍለጊዜ፦ 9

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- **ምግቦችን በአራት መሠረታዊ ምድቦች ይከፍላሉ።**
- **የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንፅሕና አጠባበቅ መንገዶችን ይለያሉ።**

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች፦

- **አራቱ የምግብ ምድቦች**
- **የምግብ ብክለት**

ሀ. አራቱ የምግብ ምድቦች፦

- የትምህርቱ ጭብጥ

አራቱ የምግብ ምድቦች ለሰውነታችን የተለዩ ጥቅሞችን ይሰጣሉ።አትክልትና ፍራፍሬዎች ሰውነትን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማሉ። ለምሳሌ፦ ብርቱካን ፣ ሎሚ ፣ ፓፓያ ፣ ሙዝ ፣ አናናስ ፣ ጥቅል ጎመን ፣ ካሮት ፣ ቲማቲም ፣ ቃሪያ ፣ ድንች ፣ ቆስጣ እና የመሳሰሉትን የተመገበ ልጅ እድገቱ ፈጣንና ሰውነቱም ጤናማ ይሆናል።

እህልና ጥራጥሬዎች ጉልበትና ሙቀት ይሰጡናል። ሥራ ለመሥራት ጉልበት ያስፈልገናል። ጉልበትና ኃይል የሚሰጡ ምግቦች እንደ በቆሎ ፣ ስንዴ ፣ ጤፍ ፣ ፓስታ ፣ ገብስ ፣ አተር ፣ መኮረኒ ፣ ባቄላ ፣ ማሽላና የመሳሰሉት ናቸው።

ሥጋ ሰውነታችን ለመገንባትና ለመጠገን ይረዳል። ከዶሮ ሥጋ ፣ ከበግ ሥጋ ፣ ከዓሣና ከመሳሰሉት ሥጋን እናገኛለን።

ወተት ለሰውነት ጉልበት ይሰጣል፣ ከበሽታ ይከላከላል ፣ ጤናማ ዕድገት እንዲኖር ይረዳል። ወተትና የወተት ውጤቶች የምንላቸው ወተት ፣ እርጎ ፣ ቅቤ ፣ አሬራ ፣ አይብ እና አጓት ናቸው።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦

- የምግብ አይነቶችንና ምድቦቻቸውን የሚያሳዩ ስዕሎች ፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮችን ይጠቀሙ

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች፦
  - የቡድን ውይይት
  - ገለፃ
  - ጥያቄና መልስ
  - ምልከታ
- ቅድመ ዝግጅት፡

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

ይህንን ንዑስ ርዕስ ከማስተማርዎ አስቀድመው የምግብ አይነቶችና ምድቦቻቸውን የሚያሳዩ ቻርቶችን፣ስዕላዊ መግለጫዎችና ፎቶግራፎችን በቅድሚያ ማዘጋጀት ወይም ማሰባሰብ ያስፈልጋል።

የንዑስ ርዕሱ ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎችን ከግምት በማስገባት የተመደቡትን ክፍለ ጊዜያት በአግባቡ ሸንሽኖ ማቀድ ያስፈልጋል። አጠር ያለ ኖት ያዘጋጁ።

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ዐራቱ የምግብ ምድቦች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

የምንመገባቸው ምግቦች በስንት ይመደባሉ? ዘርዝሯቸው፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

አራቱ የምግብ ምድቦች፡-

ከገለፃው በፊት ተማሪዎቹን በትናንሽ ቡድኖች በመመደብ በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ በሥዕል 3 ላይ ያሉትን የምግብ ዓይነቶች ተመልክተው በቡድን ውይይት በመሳተፍ የምግብ ዓይነቶቹን በየምድቦቻቸው እንዲለዩ ያድርጉ፡፡

የቀረቡትንም የመወያያ ጥያቄዎች ተወያይተው እንዲመልሱ ያድርጓቸው፡፡በውይይቱ ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው፡፡ ሲጨርሱም በክፍል ውስጥ ወጥተው የተወያዩባቸውን ነጥቦች እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡

በማጠቃለያ ስለ ምግብ አይነቶችና ምድቦቻቸው ማስታወሻ በመስጠት በፖስተሮች ወይም በስዕሎች አስደግፈው ያስረዷቸው፡፡

ውይይት 1 መልስ
1. ተማሪዎች የሚመልሱት መልስ እንደ አካባቢያቸው ይለያያል፡፡ የሚመልሱት መልስ ማስተካከያ ካስፈለገው ያስተካክሉ፡፡
2. በአንደኛው ጥያቄ መልስ መሰረት በምግብ ምድቦች እንዲያስቀምጡ ያድርጉ፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የምግብ አይነቶችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡

- የዘረዘሯቸውን የምግብ አይነቶች በየምድባቸው እንዲመድቡ ማድረግ፡፡

- የምግብ ጥቅሞችንና ምሣሌዎችን እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው፡፡

ማጠቃለያ

የምንመገባቸው ምግቦች በአራት ምድቦች ይከፈላሉ። እነርሱም፡-

አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬዎች፣ ሥጋ፣ወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው።አትክልትና ፍራፍሬዎች ሰውነትን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማሉ። እህልና ጥራጥሬዎች ጉልበትና ሙቀት ይሰጣሉ።ሥጋ ሰውነታችንን ለመገንባትና ለመጠገን ይረዳል። ወተትና የወተት ውጤቶች ጉልበት መስጠት ፣ በሽታን መከላከልና ለዕድገት ይጠቅማሉ።

የመልመጃ 2.2 መልስ

ሀ. 1.እውነት 2.ሐሰት 3.እውነት

ለ. 1. በሽታን ለመከላከል
2. ሰውነትን ለመገንባትና ለመጠገን
3. አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬዎች ፣ሥጋ ወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው።
4. ገብስ፣ማሽላ፣በቆሎ አተር ጤፍ፣ ስንዴና የመሳሰሉት ናቸው።

ለ. የምግብ ብክለት

- የትምህርቱ ጭብጥ

የምግብ ብክለት ማለት ምግብ በዓይን በማይታዩ ጥቃቅን ነፍሳት (ጀርሞች) መመረዝ ማለት ነው ።ምግብን በደንብ ያለማብሰል፣ በደንብ ያለመክደን፣ በንፁህ ስፍራ አለማስቀመጥ፣ ንጽህና የጎደለው የምግብ ዝግጅት፣ አካባቢን አለማፅዳት፣ምግብን ንፁህ ባልሆነ ውሃ ማዘጋጀትና የመሳሰሉት የምግብ ብክለት መንስኤዎች ናቸው። እጅን በሳሙና በመታጠብ፣ምግብን በመክደን፣ የምግብ ማዘጋጃ ቦታን በማፅዳት፣ የምግብ ዕቃዎችን በአግባቡ በማጠብ፣ንፁህ ውሃን በመጠቀም፣ ጥፍርን በመቁረጥ፣ ፀጉርን በመሸፈን፣ አትክልቶችና ፍራፍሬዎችን በደንብበ ማጠብና በመሳሰሉት ዘዴዎች የምግብ ብክለትን መከላከል ይቻላል።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦

- የምግብ ብክለትን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች
  - - የቡድን ውይይት
  - - ገለፃ
  - - ጥያቄና መልስ
  - - ምልከታ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

የምግብብክለት መከላከያ ዘዴዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ማዘጋጀት፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት፦

መግቢያ

የምግብ ብክለት ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የምግብ መበከል ማለት ምን ማለት ነው?

- በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን በምግብ መበከል የሚመጡ በሽታዎችን ዘርዝሩ፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ገለጻ ከመስጠትዎ በፊት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎች በቻርት እንዲፅፉ ያበረታቷቸው፡፡ የፃፉትንም በግልፅ ቦታ በየክፍላቸው ውስጥ እንዲለጥፉ ያድርጉዋቸው፡፡

ውይይቱን በሚሰሩበት ጊዜ ከውይይቱ ተነስተው ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎችን እንዲፅፉ ያድርጉዋቸው፡፡

የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎችን በመጠቀም ተማሪዎቹ ምን እንደተረዱ ይጠይቁዋቸው፡፡በመጨረሻም የምግብ ብክለት መንስኤዎችን እና መከላከያ መንገዶችን በደንብ ማስታወሻ በመስጠት ያስረዷቸው፡፡

ውይይት 2 መልስ

1. ምግብን ክፍት መተው፣ ምግብ ሲዘጋጅ የንጽህና ጉድለት ካለ ፣ምግብ በዝንብና በነፍሳት ሲወረር፣ ምግብ የሚዘጋጅበት ውሃ ንፁህ አለመሆንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
2. ምግብን መክደን፣ አካባቢውን ማፅዳት፣ ሲዘጋጅ እጅን በሳሙና መታጠብ፣ ምግቡ የሚቀመጥበትን ቦታ ማፅዳት፣ ምግብን በንፁህ ውሃ ማዘጋጀትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ተማሪዎችን ጎጂ ጥቃቅን ተህዋስያን እንዴት ምግባችንን በመበከል ለበሽታ እንደሚዳርጉን ማብራርያ እንዲሰጡ መጠየቅ

- ተማሪዎችን የምግብ መበከል መከላከያ መንገዶችን እንዲዘረዝሩ ይጠይቋቸው፡፡

ማጠቃለያ

የበሽታ አምጪ ጎጂ ተህዋስያን ወደ ሰውነታችን የሚገቡት በልዩ ልዩ መንገዶች ነው፡፡ከነዚህም ውስጥ አንዱ በምንመገበው ምግብ አማካኝነት ነው፡፡ምግብ በተለያዩ ጥቃቅን ተህዋስያን ሊበከል ስለሚችል የምግብ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን በመተግበር የምግብ ብክለትን መከላከል ይቻላል፡፡

የመልመጃ 2.3 መልስ

ሀ. 1.እውነት	ለ.1. ለ
2. እውነት	2. መ
3. ሐሰት	3. ሀ
4. እውነት	4. ሐ
5. ሐሠት	

2.3 የግል ንፅህና አጠባበቅ

የተመደበው ክፍለ ጊዜ፦ 10

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የንጽህና መጠበቂያ መንገዶችን ይገልጻሉ፡፡

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች፦

- ንፅህና ለምን እንጠብቃለን?
- ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ ምን ጉዳት ይደርሳል?
- በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች
- ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር
- ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤ
- የትምህርቱ ጭብጥ

የግል ንፅህና ሲባል ዘወትር የሰውነታችንንና የልብሳችንን ንፅህና መጠበቅ ማለት ነው። ጤንነት እንዲኖረን ንፅህናችንን መጠበቅ ይኖርብናል። ንፁህ ባልሆነ እጅ፣ ዕቃዎችና ሥፍራ ምግብን ማዘጋጀት የበሽታ መንስኤ ሊሆን ይችላል።

የግል ንፅህናን መጠበቅ ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል፣ ንቁ፣ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘትና ሥራችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በትጋት ለማከናወን ያስችላል።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የግል ንፅሕና አጠባበቅን የሚያሳዩ ፖስተሮች፣ ስዕላዊ መግለጫዎች፣ ፎቶግራፍ፣ ቻርቶች ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች
  - - ውይይት
  - - ጥያቄና መልስ
  - - ገለፃ

    - ምልከታ

- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንፁህ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- በቅድሚያ ንፅህናን እንዴት መጠበቅ እንዳለብን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫዎችን ፣ ቻርቶችን ፣ ፖስተሮችን ማዘጋጀት ወይም ማሰባሰብ ያስፈልጋል።

- በትምህርት ቤቱ የጤና ክበብ ካለ የክበቡን ተጠሪዎች ለመጋበዝና በንጽህና ጉድለት ስለሚመጡ በሽታዎች ለተማሪዎች እንዲያስረዱ ከእነርሱ ጋር በቅድሚያ ፕሮግራም ይያዙ።

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የግል ንፅህና አጠባበቅ ንፁህ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

ተማሪዎች እንዴት የግል ንፅህናቸውን እንደሚጠብቁ እንዲያብራሩ ያድርጉ።

- የትምህርቱ አቀራረብ

በተማሪ ሱራፌልና በሲስተር ሐያት መካከል የተደረገውን ቃለ መጠይቅና መልስ ሁለት ተማሪዎችን መርጠው እንዲያነቡ ያድርጓቸው። ካነበቡ በኋላ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው። ከጥያቄና መልሱ የተገኙትን ጠቃሚ ምክሮች በደንብ ያስረዷቸው። በቡድን በቡድን ሆነው

የተሰጣቸውን የቡድን ውይይት እንዲወያዩ ያድርጓቸው።

በመጨረሻም ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመስጠት ያብራሩላቸው።

ውይይት 3 መልስ፡-

1. **የግል ንጽሕናችንን የምንጠብቀው ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንንና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና በመጠበቅ ፣ጥርሳችንን በመፋቅና ጥፍራችንን በመቁረጥነው።**
2. **እጃችንን ከመፀዳጃ ቤት ስንመለስ፣ ሕፃናትን ከመመገባችን በፊት፣ ምግብ ከመመገባችን በፊትና ከተመገብን በኋላ፣ ምግብ ከማዘገጃታችን በፊት፣ ከጨዋታ ስንመለስ፣ ማንኛውንም ሥራ ካጠናቀቅን በኋላ፣ እንስሳትን ከነካን ወይም ካሻሸን በኋላ በውሃና በሳሙና በሚገባ መታጠብ አለብን። ዘወትር ጠዋት ከመኝታችን ስንነሳ ፊታችን እና እጃችንን በውሃና በሳሙና በሚገባ መታጠብ አለብን።**
3. **የግል ንጽሕናቸውን ሲጠብቁ ያሳያል።**

- **ምዘናና ግምገማ**

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።

- የግል ንፅህናን መጠበቂያ መንገዶችን ዘርዝሩ።

ማጠቃለያ

የግል ንጽሕናችንን የምንጠብቀው ዘወትር የሰውነታችንን፣ የፀጉራችንንና የምንለብሳቸውን ልብሶች ንጽሕና በመጠበቅ ፣ጥርሳችንን በመፋቅና ጥፍራችንን በመቁረጥ ነው።ዘወትር ጠዋት ከመኝታችን ስንነሳ ፊታችን እና እጃችንን በውሃና በሳሙና በሚገባ መታጠብ አለብን።

ሀ. ንፅህና ለምን እንጠብቃለን?

- **የትምህርቱ ጭብጥ**

የግል ንፅሕናን መጠበቅ ለበሽታ የመጋለጥ ዕድልን ይቀንሳል።የግል ንፅሕናን አለመጠበቅ ሰውነት መጥፎ ጠረን እንዲኖረው ያደርጋል።ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታ ይቀንሳል።ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል።የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና በልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስኤ ይሆናል።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦

- የግል ንፅሕናን መጠበቅና አለመጠበቅ ያሏቸውን ልዩነቶችን የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ቻርት ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች፦
    - - የቡድን ውይይት
    - - ገለፃ
    - - ጥያቄና መልስ
    - - ምልከታ
    -
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- የግል ንፅሕናን መጠበቅና አለመጠበቅ ያሏቸውን ልዩነቶችን የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ቻርት ያዘጋጁ።

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ንፅህና ለምን እንጠብቃለን ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

- ንፅህና ለምን እንጠብቃለን?

- የትምህርቱ አቀራረብ

ገለጻ ከመሰጠቱ በፊት ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው በተሰጠው የቡድን ሥራ እንዲወያዩ ያድርጓቸው። በክፍል ውስጥ እየዞሩ የቡድኑን ውይይቶች ይመልከቱ። ተማሪዎች በውይይቱ እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው። ሲጨርሱም በክፍል ውስጥ ወጥተው የተወያዩባቸውን ነጥቦች እንዲያቀርቡ ዕድል ይስጧቸው።

በመጨረሻም የግል ንፅሕናን(የእጅ አስተጣጠብን፣ የጥርስ ንፅህና አጠባበቅና የልብስ አስተጣጠብን) የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ቻርት በመጠቀምና ማስታወሻ በመስጠት የትምህርቱን ፍሬ ሐሳብ በመግለፅ ያጠቃሉ።

የቡድን ውይይት 4. መልስ

1. የግል ንፅሕና መጠበቅ ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል። ንቁ፣ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት ያስችላል። ሥራችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በትጋት ለማከናወን ያስችላል።
2. የግል ንፅሕናን አለመጠበቅ ሰውነት መጥፎ ጠረን እንዲኖረው ያደርጋል። ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታ ይቀንሳል። ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል። የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና በልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስዔ ይሆናል።
3. ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት፡- የቤተሰብ ስራ መፍታት። ለተጨማሪ ወጭ ይዳርጋል። ለበሽታ መተላለፍ ምክንያት ይሆናል።ንፅሕናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ። ለምሣሌ ደስተኛ ሆነው ሊቀርቡን አይችሉም፣ አብረውን መቆየት አይችሉም፣ አብረዉን መጫወት፣ መማር፣ እና መመገብ አይፈልጉም።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።

የግል ንፅሕና መጠበቅ ለምን ያስፈልጋል?

ማጠቃለያ

የግል ንፅሕና መጠበቅ ራሳችንን ከበሽታ ለመከላከል ይጠቅማል። ንቁ፣ ደስተኛና ጤነኛ ሆኖ ለመገኘት ያስችላል። ሥራችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በትጋት ለማከናወን ያስችላል። የግል ንፅሕናን አለመጠበቅ ሰውነት መጥፎ ጠረን እንዲኖረው ያደርጋል። ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ የመሥራት ሁኔታ ይቀንሳል። ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል። የተለያዩ ተባዮች በፀጉራችንና በልብሳችን ውስጥ እንዲፈጠሩ መንስዔ ይሆናል።

ለ. ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ ምን ጉዳት ይደርሳል?

- የትምህርቱ ጭብጥ

ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት፡- የቤተሰብ ስራ መፍታት። ለተጨማሪ ወጭ ይዳርጋል። ለበሽታ መተላለፍ ምክንያት ይንሆናል። ንፅሕናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ። ለምሣሌ ደስተኛ ሆነው ሊቀርቡን አይችሉም፣ አብረውን መቆየት አይችሉም፣ አብረውን መጫወት፣ መማር፣ እና መመገብ አይፈልጉም።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦
  - - ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት(ንፅህናውን ያልጠበቀ ልጅ ዝንቦች ሲወሩትና ንፅህናውን የጠበቀ ልጅ ጋር ምግብ ሲበላና አይኑ ላይ ዝንቦቹ ሲያርፉ ከዚያም ሲታመም) የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕልና ፖስተር ይጠቀሙ።
- የመማር ማስተማር ዘዴዎች፦
  - -የቡድን ውይይት
  - -ገለፃ
  - -ጥያቄና መልስ
  - -ምልከታ
- ቅድመ ዝግጅት፡-

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት የሚያሳዩ ስዕሎች ፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ያዘጋጁ።

- የመማር ማስተማር ሂደት፦

መግቢያ

ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

ተማሪዎቹን ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት የሚያውቁትን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።

- የትምህርቱ አቀራረብ

ገለጻ ከመስጠትዎ በፊት ተማሪዎቹን በትናንሽ ቡድኖች ይከፋፍሉአቸው። ሥዕል 11ን እንዲመለከቱና ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው። እንዲሁም እያንዳንዱን ቡድን በተማሪው መፅሐፍ በተሰጡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ። ቡድኑ ከውይይቱ ያገኙትን ጠቃሚ ነገሮች ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው። ከእነሱ ሐሳብ ተነስተው ዋና ዋና ነጥቦችን ያብራሩላቸው። ተጨማሪም ማሰታወሻ ይስጧቸው።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።

- ንፅህናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳቶች እንዲዘርዝሩ መጠየቅ።

ተግባር 2
ተማሪዎች ከጤና ክበብ ስለግል ንጽህና ጠይቀው የሚያመጡትን መረጃ በመቀበል የተማሪዎች መልስ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። በተጨማሪም ተማሪዎቹን ያበረታቷቸው፣ ማስተካከያ ካስፈለገው ያስተካክሉ። የተግባሩ ዓላማ ተማሪዎች የግል ንጽሕናቸውን ካልጠበቁ በሌሎች ሰዎች ላይም ጉዳት እንደሚያደርሱ እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

ማጠቃለያ

ንፅሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት፡- የቤተሰብ ስራ መፍታት።ለተጨማሪ ወጭ ይዳርጋል።ለበሽታ መተላለፍ ምክንያት ይሆናል።ንፅሕናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ። ለምሣሌ ደስተኛ ሆነው ሊቀርቡን አይችሉም፣ አብረውን መቆየት አይችሉም ፣ አብረዉን መጫወት ፣ መማር ፣ እና መመገብ አይፈልጉም።

ሐ. በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች

- የትምህርቱ ጭብጥ

ኮሌራ፣ ተቅማጥ፣ የወስፋት በሽታ፣.እከክ፣የዓይን ማዝና የመሳሰሉት በግል ንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ናቸው።

የወስፋት በሽታ በአብዛኛው ህፃናትን ያጠቃል። ይህም የሆነበት ምክንያት ልጆች በተበከለ አፈር ሲጫወቱ በአፈር ውስጥ የወስፋት ትል እንቁላሎች በጥፍሮቻቸው ላይ ይጣበቃሉ። ልጆች እጃቸውን በሚገባ ካልታጠቡ እነዚህ ጥፍሮቻቸው ውስጥ የተጣበቁት እንቁላሎች በአፋቸው በኩል ወደ አንጀታቸው ይገባሉ። ኮሌራ አጣዳፊና ተዛማች የሆነ የተቅማጥና የትውከት በሽታ ነው።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦

- በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች ፣ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች፦
  - የቡድን ውይይት
  - ገለፃ
  - ጥያቄና መልስ
  - ምልከታ

- ቅድመ ዝግጅት
    - መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ማዘጋጀት ወይንም መሰብሰብ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ዘርዝሩ፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻ በፊት ተማሪዎች በቡድን በቡድን ሆነው በተሰጠው የቡድን ውይይት እንዲወያዩ ያድርጓቸው፡፡ በክፍል ውስጥ እየዞሩ የቡድኑን ውይይቶች ይመልከቱ፡፡

የማይሳተፉትን እንዲሳተፉ ያበረታቷቸው፡፡ የሚሳተፉትንም ሞራል ይስጧቸው፡፡ ሲጨርሱም በክፍል ውስጥ ወጥተው የተወያዩባቸውን ነጥቦች እንዲያቀርቡ ይርዷቸው፡፡ በመጨረሻ ማጠቃልያ ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 5 መልስ
በግል ንጽህና ጉድለት ከሚከሰቱ የተለያዩ በሽታዎች መካከል ጥቂቶቹ ኮሌራ ፣ ተቅማጥ ፣ የወስፋት በሽታ ናቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- በንፅህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን ዘርዝሩ፡፡

    - መ. ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር
- የትምህርቱ ጭብጥ

የተሟላ ጤንነት ያለው ሰው ጠንካራና ጤነኛ ነው፡፡ሕመምተኛ ሰው ግን ደካማና ፈዛዛ ነው:: ጤናማ ልጆች ጤናማ ናቸው፡፡ትምህርታቸውን በአግባቡ ይማራሉ፡፡ውጤታቸው በጣም ጥሩ

ነው።ስለዚህ ደስተኞች ይሆናሉ።ሕመምተኛ ልጆች ብዙውን ጊዜ ይታመማሉ።ትምህርታቸውን በአግባቡ መማር አይችሉም።ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል።ስለዚህ ደስተኞች አይሆኑም።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦

- ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎች፣ቪዲዮ፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች
  - - የቡድን ውይይት
  - - ገለፃ
  - - ጥያቄና መልስ
  - - ምልከታ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች፣ ፎቶግራፎችና ቻርት፣ ፖስተሮች ያዘጋጁ።

- የመማር ማስተማር ሂደት፦

መግቢያ

ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር።በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

- የትምህርቱ አቀራረብ

ገለጻ ከማድረግዎ በፊት ተማሪዎች ከዚህ በፊት ታመው እንደማያውቁና እንደሚያቁ ይጠይቁ። ከዚያም የተማሪዎች መልስ ታመን ነበር ከሆነ በታመሙበት ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማቸው እንደነበር ይጠይቋቸው። ይሰማቸው የነበረውን ስሜት ለክፍላቸው ተማሪዎች በማብራራት እንዲገዉል ያድርጉ።

- ተማሪዎቹን ህመም በትምህርታቸው ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ተጽዕኖ ይጠይቋቸው።

- ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን የሚያሳዩ ስዕሎችን፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮችን ለተማሪዎች በማሳየት ምን እንደተገነዘቡ ይጠይቋቸው።

ከዚያም በቡድን በቡድን ሆነው በመፅሐፋቸው ውስጥ በተሰጠው ሰንጠረዥ ላይ ከተወያዩ በኋላ ጤናማ የሆኑና የታመሙ ልጆችን በማነፃፀር የቀረውን እንዲሞሉ ያድርጉአቸው። ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን በማወዳደር ልዩነታቸውን የሚገልጽ ማስታወሻ በመስጠት በደንብ ያስረዷቸው።

የቡድን ውይይት 6

ጤናማ ልጆች	ህመምተኛ ልጆች
ጤነኛ ናቸው	ታማሚ ናቸው
ትምህርታቸውን በአግባቡ ይማራሉ፡	ትምህርታቸውን በአግባቡ መማር አይችሉም፡፡
ውጤታቸው በጣም ጥሩ ነው፡፡	ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡
ደስተኞች ይሆናሉ፡፡	ደስተኞች አይሆኑም፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ሕመምተኛ ሰው ከጤነኛ ሰው በምን ይለያል?

ማጠቃለያ

ጤናማ መሆን ትምህርታችንን እንድንከታተል ይረዳናል፡፡ ሥራችንን እንድናከናውን ይጠቅመናል፡፡ በራሳችን ደስታ እንዲሰማን ያደርጋል፡፡ ከጓደኞቻችን ጋር መጫወት እንችላለን፡፡

ሠ. ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤ

- የትምህርቱ ጭብጥ

ሕመምተኛ ሰዎችን መርዳት አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ለሕመምተኛ ሰዎች ፍቅር መስጠትም ያስፈልጋል፡፡ ሕመምተኞች የሚመገቡትን ምግብና የሚገለገሉበትን ቁሳቁስ በማቅረብ ልንረዳቸውና ልንከባከባቸው ይገባል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ለታመሙ ሰዎች የምናደርገውን ርህራሄና እንክብካቤ የሚያሳዩ ቪዲዮ፣ ሥዕሎች ፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች ይጠቀሙ፡፡

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች
  - - ገለፃ
  - - ጥያቄና መልስ
  - - ምልከታ
  - - ጭውውት
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

በመርጃ መሣሪያዎች ሥር የተጠቀሱትን መርጃ መሣሪያዎች ዝግጁ ያድርጉ፡፡ በትምህርቱ ንዑስ ርዕስ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን በማየት ለተማሪዎች የሚሆኑ አጫጭር ማስታወሻዎች ያዘጋጁ፡፡ለተማሪዎች አወያይ የሆኑ ጥያቄዎችን ያዘጋጁ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤ ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

በመፀሐፋቸው ውስጥ የተሰጠውን ጭውውት እንዲያቀርቡ ዕድል ይስጡአቸው፡፡ተማሪዎችን በቡድን በመመደብ ለታመሙ ሰዎች የምናደርገውን ርህራሄና እንክብካቤ የሚያሳዩ ሥዕሎች ፣ ፎቶግራፎችና ፖስተሮች በማሳየትና እንዲወያዩ በማድረግ የተገነዘቡትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ካደረጉ በኃላ ተጨማሪ ማብራርያ ይስጧቸው፡፡

ተግባር 3

ስድስት ተማሪዎች ቡድን በመመስረት አንድ ተማሪ እንደ ታማሚ በመሆን ሦስቱ ተማሪዎች ደግሞ እንደ አስታማሚ በመሆን አንድ ተማሪ ደግሞ እንደ ዶክተር ሌላኛው ተማሪ ደግሞ እንደ ነርስ በመሆን የታመመውን ልጅ ሲያሳክሙት፣ ሲንከባከቡትና በመጨረሻም የታመመው ልጅ ድኖ ለተደረገለት እንክብካቤ በማመስገን ትምህርቱን ሲቀጥል የሚያሳይ ጭውውት እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ ተማሪዎች ጭውውት በሚያቀርቡበት ሰዓት ድጋፍ ማድረግና ተማሪዎቹ ከጭውውቱ ምን እንደተረዱ በመጠየቅ ከመልሳቸው በመነሳት ማጠቃለያ ይስጧቸው፡፡ የጭውውቱ አላማ ተማሪዎች የታመሙ ሰዎችን መርዳትና መንከባከብ እነዳለብን ላማስገንዘብ ነው፡፡

ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

ለታመመ ሰው ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

- የታመመ ሰውን መርዳት ለምን ይጠቅማል?

ማጠቃለያ

ለሕመምተኛ ሰዎች ፍቅር ማሳየት ተገቢ ሥነ ምግባር ነው፡፡ሕመምተኛ ሰዎችን መርዳት አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ሕመምተኞች የሚመገቡትን ምግብና የሚገለገሉበትን ቁሳቁስ በማቅረብ ልንረዳቸውና ልንከባከባቸው ይገባል፡፡

የመልመጃ 2.4 መልሶች

ሀ. 1.እውነት 2.እውነት 3.እውነት 4.ሀሠት

ለ. 1.ለ 2.ሐ 3.ሀ

1. **ንፅሕናችንን ባለመጠበቃችን ምክንያት ሌሎች ሰዎች ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡ ለምሣሌለበሽታ መተላለፍ ምክንያት ይሆናል፡፡ ደስተኛ ሆነው ሊቀርቡን አይችሉም ፤ አብረውን መቆየት አይችሉም ፣ አብረዉን መጫወት ፣ መማር ፣ እና መመገብ አይፈልጉም፡፡**
2. **ዘወትር ጠዋት ከመኝታችን ስንነሳ ፊታችን እና እጃችንን በውሃና በሳሙና በሚገባ መታጠብ አለብን፡፡ምግብ ከተመገብን በኋላ አፍን በውሃ መጉመጥመጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ጥርሳችንን ዘወትር ጠዋት ከመኝታ እንደተነሳን በጥርስ ብሩሽ ወይም በዕንጨት መፋቂያ መፋቅ ያስፈልጋል፡፡ዘወትር ማታ ወደ መኝታችን ከመሄዳችን በፊት እግሮቻችንን መታጠብ አለብን፡፡ እንዲሁም ሰውነታችንን እና ፀጉራችንን መታጠብ አለብን፡፡ ልብሳችንን በአግባቡ መልበስና በንፅሕና መያዝ በሚቆሽሽበት ጊዜ ማጠብ አለብን፡፡**
3. **ጤናማና ልጆችጤናማ ናቸው፡፡ትምህርታቸውን በአግባቡ ይማራሉ፡፡ ውጤታቸው በጣም ጥሩ ነው፡፡ስለዚህ ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ሕመምተኛ ልጆች ብዙውን ጊዜ ይታመማሉ፡፡ትምህርታቸውን በአግባቡ መማር አይችሉም፡፡ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ደስተኞች አይሆኑም፡፡**

2.4 የቁስ አካል ሁነታዊ ለውጥ (ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ)

የተመደበው ክፍለ ጊዜ፦ 8

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- **የቁስ አካልን (የጠጣር፣ የፈሳሽና ጋዞች) የሁነት ለውጥ ይገልፃሉ።**
- **የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋዞች ባህርያትን ፍቺዎችን ይገልፃሉ።**
- **የትምህርቱ ጭብጥ**

ቁስ አካል ማለት ማንኛውም ቦታ የሚይዝና መጠነ ቁስ ያለው ነገር ነው። የቁስ አካል ባህርያት አካላዊ ባህርያትና ኬሚካዊ ባህርያት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

አካላዊ (ፊዚካዊ) ባህርያት የምንላቸው አንድን ቁስ አካል ባለበት ሁኔታ ከሌላው የሚለይበት ባህሪ ለመግለፅ የሚያስችሉ ናቸው። እነዚህም ቀለም፣ ሽታ፣ መጠን እና የመሳሰሉት ናቸው። የቁስ አካል ሁነቶች ሦስት ናቸው። እነርሱም ጠጣር ፣ ፈሳሽና ጋዝ ናቸው። የልዩ ቁስ ሁነት ማለት ልዩ ቁስ በአንድ ቋሚ ወይም የተወሰነ ደረጃ የሚገኝበት ሁኔታ ነው።

ጠጣሩ የተወሰነ ቅርፅ ያለውና ቦታ የሚይዝ ቁስ አካል ነው። ለምሣሌ፦ በረዶ ፣ጨው ፣ ድንጋይ ፣ ብረት የመሳሰሉት ናቸው።

ፈሳሹ የተወሰነ ቦታ የሚይዝና የራሱ የሆነ ቅርፅ የሌለው ሆኖ ነገር ግን የተያዘበትን (ያለበትን) ዕቃ ቅርፅ የሚይዝ ቁስ አካል ነው። ለምሣሌ፦ ውሃ ፣ ዘይት ፣ ቤንዚን እና የመሳሰሉት ናቸው።

ጋዙ፦ የተወሰነ ቅርፅ የሌለው ሆኖ የተገኘውን ቦታ የሚሞላ ቁስ አካል ነው፣ ለምሳሌ፦ እንፋሎት (ትነት) ፣ አየር ፣ ኦክስጅን ፣ ሃይድሮጅን እና የመሳሰሉት ናቸው።

የቁስ አካላት አካላዊ ባህርያት አላቸው። እነርሱም እፍጋት (Density) ፣ ነጥበ ቅልጠት (Melting point)፣ ነጥበ ብርደት (Freezing Point) ፣ ነጥበ ፍሌት (Boiling point) እና የመሳሰሉት ናቸው።

እፍጋት (Density) አንድ የተወሰነ መጠነ ቁስ (Mass) ከሚይዘው ቦታ ወይም ምድገት (Volume) ጋር በማነፃፀር የሚገለፅ ነው።

ነጥበ ፍሌት (Boiling point) ማለት አንድ ፈሳሽ ልዩ ቁስ ወደ እንፋሎትነት (ተን) የሚለወጥበት የሙቀት መጠን ማለት ነው።

ነጥበ ብርደት (Freezing Point) ማለት አንድ ፈሳሽ ልዩ ቁስ ወደ ጥጥርነት የሚለወጥበት የሙቀት መጠን ማለት ነው።

ነጥበ ቅልጠት (Melting point)ማለት አንድ ጥጥር ልዩ ቁስ ወደ ፈሳሽነት የሚለወጥበት

የሙቀት መጠን ማለት ነው።

ኬሚካዊ ባሕርያት፦ ቁስ አካላት በሚቃጠሉበት ፣ በሚሞቁበት ወይም ከሌላ ቁስ ወይንም ንጥረ ነገር ጋር ሲዋሀዱ ፍፁም የሆነ ኬሚካዊ ለውጥ ይከሰታል። ለምሳሌ መቃጠል ፣ መንደድ ፣ መዛግና የመሳሰሉት ናቸው።

- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
  - ስለልዩ ቁስ ሁነቶች የሚገልፅ ስዕላዊ መግለጫዎች ወይም ፎቶ ግራፎች
  - በረዶ ፣ውሃ፣ ምድጃና ብረት ድስት
- የማስተማርያ ዘዴዎች፦
  - ውይይት
  - ጥያቄና መልስ
  - የተግባር እይታ
  - ገለፃ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር ዓላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራትና የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- ስለልዩ ቁስ ሁነቶች የሚያሳይ ሥዕል ወይም ፎቶ ያዘጋጁ።
- በማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ ሙከራ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮችን(በረዶ ፣ውሃ፣ ምድጃና ብረት ድስት) አዘጋጁ።
- ለክፍል ውይይት የሚያገለግሉ ጥያቄዎችን ይምረጡ።በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ባሻገር ተጨማሪ ክንውኖች ማዘጋጀት

- የመማር ማስተማሪያ ሂደት
  - መግቢያ

የቁስ አካልን የሁነት ለውጥና የጠጣር ፣ የፈሳሽና የጋዝ ባህርያትን ፍቺዎች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

ተማሪዎች ቁስ አካል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።
ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን ቁስ አካላት እንዲዘረዝሩ ያድርጉ።

- የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎች የቁስ አካል ሦስቱ ሁነቶችን እንዲዘረዝሩ በማድረግ ትምህርቱን ይጀምሩ።
በትናንሽ ቡድኖች በመመደብ በተማሪዎች መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትንሥዕሎችና የመወያያ ነጥቦች ተንተርሰው እንዲወያዩና ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ያድርጉ። እንዲሁም ከየቡድኑ አንድ አንድ ተማሪ እያስነሱ የተወያዩባቸውን ነጥቦች ለክፍሉ ተማሪዎች ገለፃ እንዲያደርጉ ዕድል

በመስጠት ትምህርቱን ይስጧቸው።የማጠቃለያ ሐሳቦችን በመስጠት የመማር ማስተማርን ውጤታማ እንዲሆን ያድርጉ።

የቡድን ውይይት 6 መልስ

1. ጠጣር ማለት ውስን የሆነ ቅርፅና ይዘት ያለው ቁስ አካል ነው።
2. ለምሣሌ ብረት ፣ ድንጋይ ፣ ጠመኔየመሳሰሉት ናቸው።
3. ፈሳሽ ማለት ውስን የሆነ ይዘት ያለው ነገር ግን ውስን የሆነ ቅርፅ የሌለው ቁስ አካል ነው።ለምሣሌ፦ውሃ፣ዘይትናወተት
4. ጋዝ ማለት ውስን የሆነቅርፅም ሆነይዘት የሌለው ቁስ አካል ነው።ለምሣሌ፦እንፋሎት፣አየር
5. በአካባቢያቸው የሚገኙትን የጠጣር፣ የፈሳሽ፣ የጋዝ ምሳሌዎችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ።

የቡድን ውይይት 7 መልስ

ሁነት	ውስን ቅርጽ	የቅንጣጢት አቀማመጥ	ውስን ይዘት
ጠጣር	አለው	የተጠጋጋ ነው	አለው
ፈሳሽ	የለውም	ከጠጣር አንጻር የተራረቀ ነው	አለው
ጋዝ	የለውም	ከጠጣርና ፈሳሽ አንጻር የተራራቀ ነው	የለውም

የተግባር 4 መልስ

በተማሪዎች መጽሐፍ የቀረበውን የተግባር ክንውን ተማሪዎች እንዲሰሩና ሲሰሩም ድጋፍ ያድርጉላቸው በመጨረሻም ከተግባር ክንውኑ ያገኙትን ውጤት እንዲብራሩ ያድርጉና ማስተካከያ ካስፈለገው ማስተካከያ ይስጡ።እያንዳንዳቸው ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡት መከራዎች በቤታቸው በመተግበር ያገኙትን ውጤት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው።

የሚያስፈልጉ ቁሶች፦ በረዶ ፣ ምድጃ ፣ የውሃ መጣጃ (ብረት ድስት)

የአሠራር ቅደም ተከተል፦

1. **በረዶውን ብረት ድስቱ ውስጥ በመጨመር ምድጃ ላይ ይጣዱት። የተመለከቱትን በደብተራቸው ላይ ይፃፉ።**
2. **ውሃን ብረት ድስት ውስጥ በመጨመር ምድጃ ላይ ያፍሉት። ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከጠበቁ በኋላ ያዩትን ውጤት በደብተራቸሁ ላይ ይፃፉ።**
3. **ውሃን በበረዶ ማስቀመጫ በማድረግ ፍሪጅ ውስጥ ያስቀምጡ። ከቆይታ በኋላ ያዩትን ውጤት በደብተራቸው ላይ ይፃፉ።**

የተግባሩ ዓላማ ተማሪዎች ውሃ በሦስቱ ሁነቶች እንደሚገኝና በሙቀት ልዩነት ከአንዱ ወደ ሌላኛው ሁነት እንደሚቀየር በተግባር በማረጋገጥ እንዲረዱ ለማድረግ ነው።

- **ምዘናና ግምገማ**

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል።

1. **የቁስ አካል ሁነቶች ማለት ምን ማለት ነው?**
2. **የቁስ አካላት ሁነቶች በስንት ይከፈላሉ? ዘርዝሯቸው።**

ማጠቃለያ

የቁስ አካል ሁነቶች ማለት አንድ ቁስ አካል በአንድ ቋሚ ወይም የተወሰነ ደረጃ የሚገኝበት ሁኔታ ነው። የቁስ አካል ሁነቶች በሦስት ይከፈላሉ። እነርሱም፦ ጠጣር፣ ፈሳሽ ፣ ጋዝ ናቸው።

የመልመጃ 2.5 መልስ

ሀ. 1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. እውነት 5.እውነት

ለ. 1. ሲፈላ 2. ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ

2.5 የብርሃን ጥቅም

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የብርሃን ጥቅሞችን ይዘረዝራሉ።

የትምህርቱ ጭብጥ

ብርሃን ከተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ከሆኑ ምንጮች ማግኘት ይቻላል። ለምሳሌ፦ ከፀሐይ፣ ከጨረቃ፣ ከሚበራ አምፑል፣ ከሚበራ ሻማና ከመሳሰሉት ብርሃን እናገኛለን።

ብርሃን ከሌለ ነገሮችን ማየት አንችልም። የፀሐይ ብርሃን በነፃ የሚገኝ የጉልበት ምንጭ ነው። ከፀሐይ የሚገኘውን ጉልበት በመጠቀም ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን ይቻላል። ለምሣሌ፦ ልብስን ለማድረቅ ፣ ተክሎች ምግባቸውን ለማዘጋጀት የፀሐይ ብርሃን ይጠቅማል። ከፀሐይ የኤሌክትሪክ ጉልበት ማመንጨት ይቻላል። ይህን ጉልበት ለመብራት ፣ ለመኪናዎች እና ለውሃ ማሞቂያ ሊያገለግል ይችላል። በተጨማሪም የፀሐይ ጉልበት ውሃ ከወንዝ ፣ ከሐይቅ ፣ ከባሕርና ከውቅያኖስ እንዲተንና ተመልሶ በዝናብ መልክ ወደ መሬት እንዲዘንብ ያደርጋል።

ጥራጥሬዎችን፣ እንጨትን፣ ቅጠላቅጠሎችን እና የመሳሰሉትን ለማድረቅ ይረዳል። የአከባቢያችን አየር ለማሞቅ ይጠቅማል።

- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
  - ስለብርሃን ምንጮች የሚገልፅ ስዕላዊ መግለጫዎች ወይ ሞዴል ወይም ፎቶግራፎች
  - ስለብርሃን ጥቅሞች የሚገልፅ ስዕላዊ መግለጫዎች ወይም ፎቶግራፎች
- የማስተማሪያ ዘዴዎች
  - ውይይት
  - ጥያቄና መልስ
  - በተግባር ማየት
  - ገለፃ
- ቅድመዝግጅት

- ስለብርሃን ምንጮችና ጥቅሞች የሚገልፁ ስዕላዊ መግለጫዎችን ወይም ፎቶ ግራፎችንና ወይ ሞዴል ያዘጋጁ ወይም ያሰባስቡ።

- የፀሐይ ብርሃን ተክሎች ላይ ያለውን ጥቅም የሚያሳይ ሙከራ በቅድሚያ ይሞክሩ።

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ስለብርሃን ምንጮችና ጥቅሞች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡በሂደቱም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የሚያውቁትን የብርሃን ምንጮችና ጥቅሞችን እንዲዘረዝሩ ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

የብርሃን ምንጮችና ጥቅሞችን የሚያሳዩ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም በየቡድናቸው እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡እያንዳንዳቸው ቡድን ከውይይቱ ያገኙትን ጠቃሚ ነገሮች ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው፡፡ ስለብርሃን ጥቅም ለመረዳት ተግባር 14 እንዲሰሩ ያድርጓቸው፡፡ ከመከራቸውም ያገኙትን ውጤት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡ ተማሪዎች ከሰጡት ሀሳብ ተነስተው ማጠቃለያ ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 8 መልስ

1. ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የብርሃን ምንጮችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ፡፡ ስህተት ካለ ማስተካከያ ይስጡ፡፡
2. ከፀሐይ የሚገኘውን ጉልበት በመጠቀም ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን ይቻላል፡፡ለምሣሌ ልብስን ለማድረቅ፣ ለማየት፣ ለእፅዋት እድገት፣ ሰብልን ለማድረቅ፣ ብርሃንን ወደ ሙቀት ጉልበት በመቀየር ምግብን ለማብሰል፣ ወደ ኤሌክትሪክ ጉልበት በመቀየር ለተለያዩ ነገሮች መጠቀምና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ተግባር 5

በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የተግባር ክንውኖች ተማሪዎች በተግባር እንዲያከናውኑና ማከናወናቸው መገምገም ይኖርብዎታል፡፡ በተጨማሪም ስለተግባራዊ ክንውኑ ተማሪዎችን በማሳተፍ ማጠቃለያ ይስጡ፡፡

ሁሉም ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡት መከራዎች በቤታቸው በመተግበር ያገኙትን

ውጤት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው፡፡

የሚያስፈልጉ ቁሶች፦ ሁለት በጣሳ የተተከሉ ችግኞች

የአሠራር ቅደም ተከተል፦

1. አንዱን ችግኝ የፀሀይ ብርሃን ያለው ስፍራ ማድረግና ለተወሰኑ ቀናት ማቆየት
2. ሁለተኛውን ችግኝ የፀሀይ ብርሃን የሌለው (ጨለማ) ስፍራ ማድረግና ለተወሰኑ ቀናት ማቆየት
3. በተመሳሳይ ሰዓት እኩል መጠን ያለው ውሃ ማጠጣትና ለተወሰኑ ቀናት የሁለቱን ችግኞች ልዩነትን በማስተዋል ከሙከራው ያገኙትን ውጤት በደብተራቸው ላይ በመመዝገብ እንዲገልጹ ያድርጉ፡፡

በጨለማ ስፍራ ያለው ችግኝ ምግቡን ማዘጋጀት ስለማይችል እድገቱ እየቀጨጨ ይሄዳል ፡፡ለብዙ ቀናት የፀሀይ ብርሀን ካላገኘ ችግኙ ይሞታል፡፡ ነገር ግን የፀሀይ ብርሀን ያገኘው ችግኝ ምግቡን ማዘጋጀት ስለሚችል በጥሩ ሁኔታ ያድጋል፡፡

የተግባሩ ዓላማ፡- ተማሪዎች ዕፅዋት ምግባቸውን እንዲያዘጋጁና ለዕድገታቸው ብርሃን አስፈላጊ መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ ነው፡፡

በጨለማ ስፍራ ያለው ችግኝ ምግቡን ማዘጋጀት ስለማይችል በበቂ ሁኔታ አያድግም

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች የንዑስ ርዕሱን ዋና መልዕክት መረዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- - የብርሃን ምንጮችን እንዲዘረዝሩ ያበረታቷቸው
- - የብርሃን ጥቅሞችን እንዲዘረዝሩ አድርጓቸው
-
-

ማጠቃለያ

ብርሃን ከተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ከሆኑ ምንጮች ማግኘት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፦ ከፀሐይ ፣ ከጨረቃ ፣ ከሚበራ አምፑል ፣ ከሚበራ ሻማና ከመሳሰሉት ብርሃን እናገኛለን፡፡ ከፀሐይ የሚገኘውን ጉልበት በመጠቀም ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን ይቻላል፡፡ለምሣሌ ልብስን ለማድረቅ፣ ለማየት፣ ለእፅዋት እድገት፣ ሰብልን ለማድረቅ፣ ብርሃንን ወደ ሙቀት ጉልበት በመቀየር ምግብን ለማብሰል፣ ወደ ኤሌክትሪክ ጉልበት በመቀየር ለተለያዩ ነገሮች መጠቀምና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

የመልመጃ 2.6 መልስ

ሀ) 1.እውነት	ለ) 1.ሐ	ሐ) 1.መ
2. እውነት	2.ሀ	2.ሐ
3. ሐሠት	3.ለ	3.መ

የምዕራፉ የማጠቃለያ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ሀ) 1. እውነት	ለ) 1.ለ	ሐ) 1.ሐ
2. ሐሠት	2.ሀ	2.ሀ
3. እውነት	3.ሐ	3.ሐ
4. ሐሠት		4.ሀ
5. እውነት		5.ሐ

መ.1. ኮሌራ፣ የወስፋት ትልና ተቅማጥ ናቸው።

2. አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬዎች፣ ሥጋወተትና የወተት ውጤቶች ናቸው።

3. የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ ናቸው።

ምዕራፍ ሦስት

ተፈጥሮአዊ አካባቢ

ለምዕራፉ የተመደበ የክፍለ ጊዜ ብዛት--54

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በክፍለ ከተማችን በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የምናገኛቸው ለሕይወታችን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በዝርዝር ለተማሪዎች የሚያስተምር ነው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለክፍለ ከተማችን የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት፣ ስለተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶች፣ የተፈጥሮ ሀብቶች ለክፍለ ከተማቸው ህልውናና ዕድገት ስላላቸው ፋይዳ፣ በትምህርት ቤትና በወረዳቸው የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችና ስለተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተዕዕኖዎች ይማራሉ።ተማሪዎች ትምህርቱን በውይይት፣ በጥያቄና መልስ፣ በሰርቶ ማሳየት፣ በዕብረቃ፣ በገለጻ፣ በመስክ ጉብኝት፣ በተግባር ሥራ ይማራሉ። እርስዎም ለተማሪዎች ምቹ ሁኔታን በመፍጠርና ተማሪዎችን በመምራት፣ በመከታተል፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ ማስታወሻና ማጠቃለያ ሐሳቦችን በመስጠት የመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን ጥረት ያድርጉ።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነቶችን ይገልጻሉ።
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት ይገመግማሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የዝናብ መጠን ሥርጭት ያወዳድራሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮች (ከፍታ፣የደን ሽፋንና ከባህር ያለው ርቀት) ይለያሉ።
- የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይለያሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ይገልጻሉ።
- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንሥኤዎችንና ውጤቶችን ይገልጻሉ።

- በክፍለ ከተማቸው የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን ይገልጻሉ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ዋጋ ይሰጣሉ፡፡
- ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሐሳቦችን ያቀርባሉ፡፡
- በትምህርት ቤታቸውና በወረዳቸው መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ያዘወትራሉ፡፡
- ቆሻሻን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢያቸው ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ይገልጻሉ፡፡
- ንጽሕናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሐሳብ ይሰጣሉ፡፡
    - የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች
    - 3.1. የክፍለ ከተማችን አየር ንብረት
    - 3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች
    - 3.3. የተፈጥሮ ሀብቶች ለክፍለ ከተማቸው ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ
    - 3.4. በትምህርት ቤት እና በወረዳቸው የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ
    - የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች
    - 3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች

3.1. የክፍለ ከተማችን አየር ንብረት

- የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት--8
    - ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነቶችን ይገልጻሉ፡፡
- በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን ይገልጻሉ፡፡
- በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት ይገመግማሉ፡፡
- በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የዝናብ መጠን ስርጭት ያወዳድራሉ፡፡
- በክፍለ ከተማቸው የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ይለያሉ፡፡
    -

- የትምህርቱ ጭብጥ

የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ አካባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው፡፡ ዋና ዋና የአየር ሁኔታ መገለጫዎች የሚባሉት ሞቃታማ፣ ቀዝቃዛማ፣ ዝናባማ፣ ደመናማ፣ ውርጫማ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የአየር ንብረት ማለት በአንድ አካባቢ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች የሚባሉት ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የአየር ግፊት እርጥበት፣ ንፋስ፣ የፀሐይ ጨረርና የዝናብ ስርጭት ናቸው፡፡

ወቅቶች በዐራት ይከፈላሉ። እነርሱም፡- መኸር፣ በጋ፣ በልግና ክረምት ናቸው። እነዚህ ወቅቶች የራሳቸው የሆነ የተለያየ የአየር ሁኔታ አላቸው።

የወቅቶች የአየር ሁኔታ

1. መኸር፡- ልምላሜ የሚታይበት
2. በጋ፡- ደረቃማ፣ፀሐያማ (ሞቃታማ)
3. በልግ፡- ከፊል ዝናባማ፣ ከፊል ደመናማ
4. ክረምት፡- ዝናባማ፣ ደመናማ፣ ቀዝቃዛ

የአየር ንብረት የሰው ልጅ የዘወትር እንቅስቃሴን ሊወስን የሚችል ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው። ለምሳሌ፦ የእርሻ ሥራን፣ የከብት እርባታን፣ የዕፅዋት ዕድገትን፣የአኗኗር ዘይቤን የመሳሰሉት ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ አለው።

- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
  - የክፍለ ከተሞችን የሙቀት መጠን ስርጭት የሚያሳይ ግራፍ ይጠቀሙ።
  - የክፍለ ከተሞችን የዝናብ መጠን ስርጭት የሚያሳይ ግራፍ ይጠቀሙ።
  - ወቅቶችን የሚያሳይ ቻርት ይጠቀሙ
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - ጥያቄና መልስ
  - የመስክ ምልከታ
  - ዕብረቃ
  - የተግባር ስራ
- ቅድመ ዝግጅት
  - መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃቶች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣ የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።
  - የክፍለ ከተሞችን የሙቀት መጠን ስርጭት የሚያሳይ ግራፍ ያዘጋጁ።
  - የክፍለ ከተሞችን የዝናብ መጠን ስርጭት የሚያሳይ ግራፍ ያዘጋጁ።
  - ወቅቶችን የሚያሳይ ቻርት ያዘጋጁ።
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የክፍለ ከተማችን የአየር ንብረትን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በዚህ

ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብሞታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ
  - ከገለጻው በፊት ስለአየር ሁኔታና ስለአየር ንብረት፣ ስለአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች፣ በተለያዩ ወቅቶች ስለሚኖረው የአየር ሁኔታ፣ በክፍለ ከተማቸው ስለሚኖረው የሙቀት መጠንና የዝናብ መጠን ስርጭት ይጠይቋቸውና የቀረበውን የመወያያ ጥያቄና የተግባር ስራ ያሰሯቸው፡፡
  - ተማሪዎች የተሰጠውን የቡድን ውይይት በቡድናቸው እንዲወያዩና መልሳቸውን በክፍል ውስጥ በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች አቅርበው ሲጨርሱ ያበረታቷቸው፤ ያድንቋቸው ከዚያም ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡
  - የተግባር 1 እና 2 ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩና መልሱን እንዲያሳዩ ያድርጉ፡፡
  - ስለአየር ሁኔታና ስለአየር ንብረት፣ ስለአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች፣ በተለያዩ ወቅቶች ስለሚኖረው የአየር ሁኔታ፣ በክፍለ ከተማቸው ስለሚኖረው የሙቀት መጠንና የዝናብ መጠን ስርጭት ማስታወሻና ማብራሪያ ይስጧቸው፡፡

ውይይት 1 መልስ

1. የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ አከባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው፡፡
2. የአየር ንብረት ማለት በአንድ አከባቢ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡
3. ያላቸው ዝምድና
   - ሁለቱም ስለ አንድ አካባቢ የአየር ስርጭት የሚያብራሩ ናቸው፡፡
   - የአየር ሁኔታ ሳይኖር የአየር ንብረት አይኖርም፡፡ ምክንቱም የአየር ንብረት የአየር ሁኔታ አማካይ ውጤት ነው፡፡

ያላቸው ልዩነት

- የአየር ሁኔታ በየቀኑ የሚታይና የሚለዋወጥ የአየር ባህሪይ ነው
- የአየር ንብረት ከረጅም ጊዜ በኋላ የሚታወቅ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው

ተግባር 1 መልስ

ተማሪዎች የክፍለ ከተማቸውን የአየር ሁኔታ ለአንድ ሳምንት እንዲከታተሉና ሪፖርት እንዲያደርጉ ይንገሯቸው፡፡ ከዚያም እንደ ሚኖሩበት ክፍለ ከተማ የሚኖረው የሙቀት መጠንና የዝናብ መጠን ስርጭት የተለያየ እንደሚሆን ይንገሯቸው፡፡

ተግባር 2 መልስ

ተማሪዎች የክፍለ ከተማቸውን የደን ሽፋንና ከፍታ በመመልከት ከአየር ንብረት ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲገመግሙ ያድርጉ፡፡ ያገኙትን ውጤት በክፍል ውስጥ እነዲቀርቡ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ክፍለ ከተማቸው የደን ሽፋን ካለው ተስማሚ የአየር ንብረት እንደሚኖረው የደን ሽፋን ከሌለው ተስማሚ ያልሆነ የአየር ንብረት እንደሚኖረው ይንገሯቸው፡፡ የክፍለ ከተማቸው ከፍታ መካከለኛ ከሆነ ምቹ የአየር ንብረት ይኖረዋል፡፡ ዝቅተኛ ከሆነ ምቹ ያልሆነ የአየር ንብረት ለምሳሌ ሞቃታማና ደረቃማ የአየር ንብረት ይኖረዋል፡፡ የክፍለ ከተማቸው ከፍታ ከፍተኛ ከሆነ ቀዝቃዛማና ደመናማ የአየር ንብረት እንደሚኖረው ያስረዷቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ከንዑስ ርዕሱ ምን እንደተገነዘቡ ለመረዳትና ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የአየር ሁኔታ ምንድን ነው?
- የአየር ንብረት ምንድን ነው?
- የአየር ሁኔታ መገለጫዎችን ተናገሩ፡፡
- የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎችን ዘርዝሩ፡፡
- የወቅቶች የአየር ሁኔታን ተናገሩ፡፡

- ማጠቃለያ

የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ አከባቢ ከጊዜና ከቦታ አንፃር በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ባህርይ ነው፡፡ የአየር ንብረት ማለት በአንድ አከባቢ ረዘም ላለ ጊዜ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡ የአየር ሁኔታ መገለጫዎች ሞቃታማ፣ ደመናማ፣ ዝናባማ፣ ቀዝቃዛማ፣ ፀሀያማ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች የሚባሉት ንፋስ፣ እርጥበት፣ የዝናብ ስርጭት፣ መፋቅና ቅዝቃዜ፣ የአየር ግፊትና የፀሀይ ጨረር ናቸው፡፡

- የወቅቶች የአየር ሁኔታ ፡-

- መኸር፡- ቀዝቃዛማ
- በጋ፡- ደረቃማ፣ ፀሀያማና ሞቃታማ
- በልግ፡- ከፊል ዝናባማ፣ ከፊል ደመናማ
- ክረምት፡- ዝናባማ፣ ደመናማ፣ ቀዝቃዛማ

መልመጃ 3.1 መልስ

ሀ. 1. ሐሰት 2. እውነት 3. እውነት

ለ. 1. ለ 2. ሀ 3. መ 4. ሐ

ሐ. 1. ንፋስ፣ እርጥበት፣ የዝናብ ስርጭት፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የአየር ግፊትና የፀሀይ

ጨረር ናቸው።

2. ሞቃታማ፣ ደመናማ፣ ዝናባማ፣ ቀዝቃዛማ፣ ፀሀያማ የመሳሰሉት ናቸው።

3.2. የተፈጥሮ ሀብቶች

የተመደበለት ክፍለጊዜ ብዛት--18

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይለያሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ይገልጻሉ።
- የትምህርቱ ጭብጥ

የተፈጥሮ አካባቢያችን ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ይይዛል። የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ የምናገኛቸውና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው። የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት አፈር፣ ውሃ፣ እፅዋት፣ አየርና የዱር እንሰሳት ናቸው።

ሰው ሠራሽ ሀብቶች የሰው ልጅ እውቀቱን፣ ጥበቡንና ሀብቱን ተጠቅሞ የሰራቸውና የሚጠቀምባቸው ሀብቶች ናቸው። ሰው ሠራሽ ሀብቶች የሚባሉት ሐውልቶች፣ ቤተ-መንግስት፣ ቤተ-እምነቶች፣ ተቋማት፣ መንገዶችና አደባባዮችና የመሳሰሉት ናቸው።

- የትምህርት መርጃ መሳሪያ
  - ውሃ፣ አፈርና እፅዋት ይጠቀሙ
  - የዱር እንሰሳትን ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
  - ሰው ሠራሽ ሀብቶችን የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
    •
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
  - ጥያቄና መልስ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - የመስክ ጉብኝት
  - ፅብረቃ

- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃቶች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- ወሃ፣ አፈርና እፅዋት ያዘጋጁ፡፡
- የዱር እንሰሳትን ፎቶግራፍ፣ ፖስተር፣ ቻርትና ሥዕል ያዘጋጁ፡፡
- የሰው ሠራሽ ሀብቶችን የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ንዑስ ርዕስ በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡ ፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ስለተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶች ምንነትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረቡትን የመወያያ ጥያቄዎች በቡድናቸው እንዲሰሩ ትዕዛዝ ይስጡ፡፡ ተማሪዎች መልሳቸውን በክፍል ውስጥ በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች አቅርበው ሲጨርሱ ያበረታቷቸው፣ ያድንቋቸው ከዚያም ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡ ስለተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶች ማስታወሻ ለተማሪዎች በመስጠት ማብራሪያ ያድርጉላቸው፡፡

የቡድን ውይይት 2 መልስ

1. የተፈጥሮ ሀብት ማለት በተፈጥሮ የምናገኘውና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡
2. ሰው ሠራሽ ሀብት ማለት የሰው ልጅ እውቀቱን፣ ጥበቡንና ሀብቱን ተጠቅሞ የሰራውና የሚጠቀምበት ሀብት ነው፡፡
3. የተፈጥሮ ሀብቶችና ሰው ሠራሽ ሀብቶች እርስ በርሳቸው ግንኙነት አላቸው፡፡ ሰው ሠራሽ ሀብቶች ለመሥራት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ሀብቶችን ይጠቀማል፡፡ ለምሳሌ:- ሐውልቶችን፣ መንገዶችን፣ ቤተ-እምነቶችን፣ ቤተ-መንግስትን፣ ድልድዮችንና የመሳሰሉትን ለመገንባት አፈር፣ ውሃ፣ አፅዋት፣ አየር ይጠቅማል፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ መርዳታቸውን ለማወቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

1. ስለተፈጥሮ ሀብቶች ምንነት መጠየቅ፡፡
2. ስለሰው ሠራሽ ሀብቶች ምንነት መጠየቅ፡፡
3. የተፈጥሮ ሀብቶችንና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን እንዲዘረዝሩ ማድረግ፡፡
   -

ማጠቃለያ

የተፈጥሮ አካባቢያችን ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ሀብቶችን ይይዛል፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ የምናገኛቸውና ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች የሚባሉት አፈር፣ ውሃ፣ እፅዋት፣ አየር፣ እንስሳት እና ማዕድናት ናቸው፡፡ ሰው ሠራሽ ሀብቶች የሰው ልጅ እውቀቱን፣ ጥበቡንና ሀብቱን ተጠቅሞ የሰራቸውና የሚጠቀምባቸው ሀብቶች ናቸው፡ ፡ ሰው ሠራሽ ሀብቶች የሚባሉት ሐውልቶች፣ ቤተ-መንግስት፣ ቤተ-እምነቶች፣ ተቋማት፣ መንገዶችና አደባባዮችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

1. የአፈር ጥቅም
   - የትምህርቱ ጭብጥ

አፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ ነው፡፡አፈር በመሬት ገፅ ላይ የሚታይ ከጥቃቅን የድንጋይ ስብርባሪ፣ የእፅዋትና እንስሳት ብስባሽ የሚፈጠር የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ አፈር ለሰው ልጅና ለእጽዋት ከፍተኛ ጥቅም ስላለው ልንከባከበው ይገባል፡፡ አፈር ለእጽዋት እድገት፣ ለሸክላ ሥራ፣ ለእርሻ ሥራ፣ ለግንባታ ሥራና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-
  - ከአፈር የተሠሩ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች(ጀበና፣ የሸክላ ምጣድ...) ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት
  - ከአፈር የተሠሩ ግንባታዎች ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት
  - የእርሻ ሥራ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት
    -
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች፡-
  - ጥያቄና መልስ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - የተግባር ሥራ

- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃቶች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣ የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- ከአፈር የተሠሩ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት ማዘጋጀት
- ከአፈር የተሠሩ ግንባታዎች ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት ማዘጋጀት
- የእርሻ ሥራ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ፖስተር፣ ሥዕል፣ ቻርት ማዘጋጀት
- ስለአፈር ጥቅም ማስታወሻ ያዘጋጁ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የአፈር ጥቅም ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርት አቀራረብ

ከገለጻው በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

- አፈር ምንድን ነው?
- የአፈርን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

መምህር! በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላ ማስተካከያ ያድርጉላቸው ፡፡ ስለአፈር ጥቅም ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 3 መልስ

የውሃ ጥቅም፡- ለንፅህና መጠበቂያ፣ ለእፅዋት እድገት፣ ለመጠጥነት፣ ለእርሻ ሥራ፣

ምግብ ለማዘጋጀት፣ ለመዝናኛ፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫና ሌሎችም፡፡
የአፈር ጥቅም፡- ለእፅዋት እድገት፣ ለሸክላ ሥራ፣ ለግንባታ ሥራና ሌሎችም፡፡
የአየር ጥቅም፡- ለሰው ልጅ፣ ለእንሰሳትና ለእፅዋት ለመተንፈስ፣ ለእፅዋት እድገት፣

የመኪና ጎማን፣ ኪስንና ፊኛን በአየር ለመሙላትና ሌሎችም፡፡
የእፅዋት ጥቅም፡- ለቤት መሥሪያ፣ ለምግብነት፣ ለዱር እንሰሳት መጠለያ፣

ለማገዶነት፣ መድኃኒት ለመሥራት፣ አፈር እንዳይሸረሸር ለመከላከል፣ ለዱር እንሰሳት

መጠለያ፣ ለልብስ መሥሪያ፣ ለወረቀት መሥሪያና ሌሎችም፡፡

የዱር እንሰሳት ጥቅም፡- ለቱሪስት መስህብነት፣ ሲያረጁ የአካል ክፍላቸውን ሸጦ ገቢ

ለማግኘትና ሌሎችም፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል፡፡

- አፈር ምንድን ነው?
- የአፈር ጥቅምን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡

ማጠቃለያ

አፈር በመሬት ገፅ ላይ የሚታይ ከጥቃቅን የድንጋይ ስብርባሪ፣ የእፅዋትና እንስሳት ብስባሽ የሚፈጠር የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ አፈር ለእጽዋት እድገት፣ ለሸክላ ሥራ፣ ለእርሻ ሥራ፣ ለግንባታ ሥራና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡፡

2. የእፅዋት ጥቅም
   - የትምህርቱ ጭብጥ

እፅዋት ሕይወት ላላቸው ነገሮች በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣሉ፡፡እፅዋት ለቤት መሥሪያ፣ ለምግብነት፣ ለዱር እንሰሳት መጠለያ፣ ለማገዶነት፣ መድኃኒት ለመሥራት፣ አፈር እንዳይሸረሸር ለመከላከል፣ ለዱር እንሰሳት መጠለያ፣ ለልብስ መሥሪያ፣ ለወረቀት መሥሪያና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ፡፡ ስለዚህ እፅዋት ጉዳት እንዳይደርስባቸው መጠበቅና ሌሎች ተጨማሪ እፅዋትን መትከል ያስፈልጋል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፡-
  - የተለያዩ እፅዋትን (ማንጎ፣ ባህር ዛፍ፣ ፅድ...) ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርትና ፖስተር ይጠቀሙ፡፡
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
  - ጥያቄና መልስ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - የመስክ ጉብኝት
  - ፅብረቃ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- የተለያዩ እፅዋትን ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርትና ፖስተር ያዘጋጁ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የእፅዋት ጥቅም ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

- እፅዋት ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

መምህር! በቀረበው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው ስለእፅዋት ጥቅም ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የእፅዋትን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡

ማጠቃለያ

እፅዋት ለልዩ ልዩ አልባሳት መሥሪያነት ለምሳሌ፦ ጥጥ፣ መጠለያዎችን ለመገንባት ለምሳሌ፦ እንጨትና ሳር፣ ለምግብ ምንጭነት ለምሳሌ፡-አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ እህልና ጥራጥሬ፣ አፈር እንዳይሸረሸር በሥራቸው ደግፈው ለመያዝ፣ የዱር እንስሳት እንዳይሰደዱ ለመጠለያነት ፣ከኤለክትሪክ በተጨማሪ ምግብን ለማዘጋጀት ለጉልበት ምንጭነት ፣የተለያዩ መድኃኒቶችን ለመሥራትና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ፡፡

3. የውሃ ጥቅም

- የትምህርቱ ጭብጥ

ውሃ ከተፈጥሮ ሀብቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ውሃ ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡

ውሃ በቤት ውስጥ፦ ምግብ ለማዘጋጀት፣ ለንፅሕና መጠበቂያ፣ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል፡፡

ለግብርና፦ ለመስኖ አገልግሎት፣ ለእንስሳት መጠጥ ይጠቅማል፡፡

ለኢንዱስትሪ፦ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለማቀዝቀዝ፣ ቆሻሻን ለማስወገድ፣ ነገሮችን ለማሟሟት ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ይጠቅማል፡፡ ስለሆነም ውሃ እንዳይባክንና እንዳይበከል መጠበቅ አለብን፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያ፡-
  - የውሃን ጥቅም የሚያሳይ(ለመስኖ ስራ፣ ለመጠጥ፣ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ...) ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ፡፡
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች፡-
  - ጥያቄና መልስ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - የመስክ ጉብኝት
  - ዕብረቃ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- የውሃን ጥቅም የሚያሳይ(ለመስኖ ስራ፣ ለመጠጥ፣ ለኤሌክትሪክ ኃ ይ ል ማመንጫ...) ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደት፡-

መግቢያ

የወሃ ጥቅም ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

- ውሃ ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

መምህር! በቀረበው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው ስለውሃ ጥቅም ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ፡-

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የውሃን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
-

-

- ማጠቃለያ

ውሃ በቤት ውስጥ፡ ምግብ ለማዘጋጀት፣ ለንፅሕና፣ ለመጠጥ አገልግሎት ይውላል።

ለግብርና፡ ለመስኖ አገልግሎት፣ ለእንስሳት መጠጥ ይጠቅማል።

ለኢንዱስትሪ፡ የማምረቻ መሣሪያዎችን ለማቀዝቀዝ፣ ቆሻሻን ለማስወገድ፣ ነገሮችን ለማሟሟት ይጠቅማል። በተጨማሪም ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ይጠቅማል። የትምህርቱን ዋና መልዕክት በዚህ መልክ ማጠቃለል ይኖርብዎታል።

4. የዱር እንሰሳት ጥቅም፡-

- የትምህርቱ ጭብጥ፡-

የዱር እንስሳት ለገቢ ምንጭነት ይሆናሉ። የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመሳብ እና አርጅተው ሲሞቱ የአካል ክፍሎቻቸውን (ቆዳቸውን፣ቀንዳቸውን፣ጥርሳቸውን) የመሳሰሉትን በመሸጥ ገቢ ያስገኛሉ።

- የትምህርት መርጃ መሳሪያ

የዱር እንሰሳት(አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብ፣ ዝሆን..) ሞዴሎች፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።

- የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች
  - ጥያቄና መልስ
  - የቡድን ውይይት
  - ገለጻ
  - የመስክ ጉብኝት
  - ፅብረቃ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- የዱር እንሰሳት(አንበሳ፣ ነብር፣ ጅብ፣ ዝሆን...) ሞዴሎች፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ።
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የዱር እንሰሳት ጥቅም ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህሪና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት

ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

- የዱር እንሰሳት ለምን ለምን ይጠቅማሉ?

መምህር! በቀረበው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ ስለዱር እንሰሳት ጥቅም ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የዱር እንሰሳትን ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
  - ማጠቃለያ

የዱር እንስሳት ለገቢ ምንጭነት ይሆናሉ፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመሳብ እና አርጅተው ሲሞቱ የአካል ክፍሎቻቸውን (ቆዳቸውን፣ቀንዳቸውን፣ጥርሳቸውን) የመሳሰሉትን በመሸጥ ገቢ ያስገኛሉ፡፡

5. የአየር ጥቅም
   - የትምህርቱ ጭብጥ

አየር ለሰው ልጅ በአጠቃላይ ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ ነው፡፡ አየር ለሰው ልጅ፣ ለእንሰሳትና ለእፅዋት ለመተንፈስ ያገለግላል፡፡ እፅዋት ለእድገታቸው አየርን ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም አየር የመኪና ጎማን፣ ካስን፣ ፊኛን ለመሙላት ይጠቅማል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሳሪያ
- በአየር ያልተሞላ ካስና ፊኛ ክፍል ውስጥ ይዞ በመግባት አየር ሞልቶ ማሳየትን መጠቀም፡፡
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
- የተግባር ሥራ
- ጥያቄና መልስ
- የቡድን ውይይት
- ገለጻ
- ዕብረቃ

- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- በአየር ያልተሞላ ኪስና ፊኛ ማዘጋጀት፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የአየር ጥቅም ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ጥያቄ በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

- አየር ለምን ለምን ይጠቅማል?

መምህር! በቀረበው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ ስለአየር ጥቅም ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የአየር ጠቀሜታ እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
  -
  - ማጠቃለያ

አየር ለሰው ልጅ በአጠቃላይ ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ ነው፡፡ አየር ለሰው ልጅ፣ ለእንሰሳትና ለእፅዋት ለመተንፈስ ያገለግላል፡፡ እፅዋት ለእድገታቸው አየርን ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም አየር የመኪና ጎማን፣ ኪስን፣ ፊኛን ለመሙላት ይጠቅማል፡፡

መልመጃ 3.2 መልስ

ሀ. 1. መ 2. ለ 3. ሀ 4. ሐ

ለ. 1. ለ 2. መ 3. ለ

ሐ. 1. - የተፈጥሮ ሀብቶች፡- አፈር፣ ውሃ፣ እፅዋት፣ አየርና የዱር እንሰሳት ናቸው።

- ሰው ሠራሽ ሀብቶች፡- ሐውልቶች፣ ድልድዮች፣ ቤተ-እምነቶች፣ ቤተ-መንግስት፣ አደባባዮችና የመሳሰሉት ናቸው።

2. የዱር እንስሳት ለገቢ ምንጭነት ይሆናሉ፡- የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመሳብ እና አርጅተው ሲሞቱ የአካል ክፍሎቻቸውን (ቆዳቸውን፣ቀንዳቸውን፣ጥርሳቸውን) የመሳሰሉትን በመሸጥ ገቢ ያስገኛሉ።

3.3 የተፈጥሮ ሀብቶች ለክፍለ ከተማችሁ ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ

- የክፍለ ጊዜ ብዛት--16

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ

- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችንና ውጤቶችን ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚዘወትሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን ይገልጻሉ።
- የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልጻሉ።

ሀ. የተፈጥሮ ሀብት ምንነት

- የትምህርቱ ጭብጥ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች በመጠን እና በአይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ ካልተያዙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ በመሄድ በመጨረሻም ሊጠፉ ይችላሉ። ስለዚህ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በሚደርሰው የጉዳት መጠን የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ይከሰታል።

- ትምህርት መርጃ መሳሪያ
  - የደን መመናመን የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ይጠቀሙ።
  - የተሸረሸረ አፈር የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ይጠቀሙ።
  - የዱር እንሰሳት የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ይጠቀሙ።
- የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ
  - -. የተግባር ሥራ
  - - ጥያቄና መልስ
  - - የቡድን ውይይት
  - - ገለጻ
  - - ዕብረቃ
  - - የመስክ ጉብኝት
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣ የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- የደን መመናመን የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ያዘጋጁ።
- የተሸረሸረ አፈር የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ያዘጋጁ።
- የዱር እንሰሳት ሲሰደዱ የሚያሳይ ቪዲዮ፣ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል ያዘጋጁ።
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነት ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በተማሪው መጽሀፍ በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት መጠየቅና እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ። በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል።

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት ስለተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምንነትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረበውን የመወያያ ጥያቄ በቡድናቸው እንዲሰሩ ትዕዛዝ ይስጡ።

መምህር! በቀረበው ጥያቄ ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው። ስለተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምንነት ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው።

የቡድን ውይይት 4 መልስ

1. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች በመጠን እና በአይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች እንዲያብራሩ መጠየቅ፡፡
  -
  - ማጠቃለያ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ማለት በተፈጥሮ የሚገኙ ሀብቶች በመጠን እና በአይነት እየቀነሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች በአግባቡ ካልተያዙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ በመሄድ በመጨረሻም ሊጠፉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በሚደርሰው የጉዳት መጠን የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ይከሰታል፡፡ የትምህርቱን ዋና መልዕክት በዚህ መልክ ማጠቃለል ይኖርብዎታል፡፡

ለ. በክፍለ ከተማችን የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶች

- የትምህርቱ ጭብጥ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች፡- አርሶ አደሮች ሰፊ የእርሻ ቦታ ለማግኘት፣ የማገዶ እንጨት ለማግኘት፣ ለግንባታ ሥራና የመገልገያ እቃዎችን ለመሥራት እዕዋትን ይጨፈጨፋሉ፡፡ ከፍተኛ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት አፈር በጎርፍ አማካኝነት ይሸረሸራል፡፡ የዱር እንሰሳት ደኖች በሚጨፈጨፉበት ሰዓት ይሰደዳሉ፡፡ አየር ከኢንዱስተሪ፣ ከተሸከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል በሚወጡ ጭሶች ይበከላል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን የሚያስከትለው ውጤት፡- ጎርፍ፣ የሙቀት መጨመር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ የብዝኃሕይወት መመናመን፣ ረሃብና ድርቅ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- የትምህርት መርጃ መሳሪያ
  - ሰዎች ለማገዶ እንጨት፣ለግብርና ሥራ፣ ለግንባታ ሥራና የመገልገያ እቃዎች ለመሥሪያ እዕዋት ሲቆርጡ የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  - አየር ከኢንዱስተሪ፣ ከተሸከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል በሚወጡ ጭሶች ሲበከል የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  - አፈር በጎርፍ ሲሸረሸር የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  - ሰዎች የዱር እንሰሳት ሲያሳድዱና ሲያድኑ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  - ሰዎች የግጦሽ መሬትን በተደጋጋሚ ሲያስግጡ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  - ውሃ ያለአግባብ ሲፈስ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ይጠቀሙ፡፡
  -
  -

- የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ
  - - ጥያቄና መልስ
  - - የቡድን ውይይት
  - - ገለጻ
  - - ፅብረቃ
  - - የመስክ ጉብኝት
  -
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- ሰዎች ለማገዶ እንጨት፣ለግብርና ሥራ፣ ለግንባታ ሥራና የመገልገያ እቃዎች ለመሥሪያ እፅዋት ሲቆርጡ የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- አየር ከኢንዱስተሪ፣ ከተሸከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል በሚወጡ ጭሶች ሲበከል የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- አፈር በጎርፍ ሲሸረሸር የሚሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- ሰዎች የዱር እንሰሳት ሲያሳድዱና ሲያድኑ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- ሰዎች የግጦሽ መሬትን በተደጋጋሚ ሲያስግጡ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- ውሃ ያለአግባብ ሲፈስ የሚያሳይ ፎቶግራፍ፣ ሥዕል፣ ቪዲዮ፣ ቻርት ያዘጋጁ፡፡
- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

በከተማችን ስለሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሀፍ ንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ከገለጻው በፊት በክፍለ በከተማችን ስለሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶች ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረቡትን የመወያያ ጥያቄዎች በቡድናቸው እንዲሰሩ ይዘሏቸው፡፡

መምህር! በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ በከተማችን ስለሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችና ውጤቶች ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 5 መልስ

1. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች፡- የማገዶ እንጨት ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍ፣ ለግንባታ ሥራ እፅዋትን መቁረጥ፣ ከፍተኛ ዝናብ መዝነብ፣ ከኢንዱስተሪ፣ ከተሽከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጡ ጭሶች፣ አርሶ አደሮች ሰፊ የእርሻ ቦታ ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍና ሌሎችም።
2. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ውጤቶች፡- የአየር መበከል፣ ጎርፍ፣ የሙቀት መጨመር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ የብዝኀ ሕይወት መመናመን፣ ረሃብ፣ ድርቅና ሌሎችም።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።

- የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤዎችን እነዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ውጤቶችን እነዲዘረዝሩ መጠየቅ።

ማጠቃለያ

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች፡- የማገዶ እንጨት ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍ፣ ለግንባታ ሥራ እፅዋትን መቁረጥ፣ ከፍተኛ ዝናብ መዝነብ፣ ከኢንዱስተሪ፣ ከተሽከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጡ ጭሶች፣ አርሶ አደሮች ሰፊ የእርሻ ቦታ ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍና የመሳሰሉት ናቸው።

የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ውጤቶች፡- የአየር መበከል፣ ጎርፍ፣ የሙቀት መጨመር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ የብዝኀ ሕይወት መመናመን፣ ረሃብና ድርቅና የመሳሰሉት ናቸው።

ሐ. በክፍለ ከተማችን የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች

- የትምህርቱ ጭብጥ

ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ህዝቦች ከጥንት ጀምሮ የራሳቸውን እውቀት ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብትን የሚንከባከቡበት ዘዴ ነው። በክፍለ ከተማችሁ የሚዘወትሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች አሉ። እነዚህም፡-

“የእንስሳት ጽዳጅ (ፍግ)” ይባል። የአፈር ለምነትን ለመጨመር ይጠቅማል።

ዛፍ መትከል፡- የአፈር መሸርሸርን፣ የአየር ብክለትን ይከላከላል።

- የዱር እንስሳት እንዳይሰደዱ ለመጠበቅ ይረዳል።
- የአካባቢን ውበት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው።

አዝዕርትን አፈራርቆ መዝራት፡- አዝዕርቶች በየጊዜው እየተፈራረቁ በሚዘሩበት ወቅት የአፈር ለምነት ይጨምራል።

እርከን መሥራት፡- አፈር በቀላሉ በጎረፍ እንዳይሸረሸርና ለምነቱን ጠብቆ ይረዳል።

አግድም ማረስ፡- አፈር በቀላሉ በውሃ እንዳይሸረሸርና ለምነቱን ጠብቆ እንዲቆይ ይረዳል።

የአፈር አጠባበቅ ዘዴዎች

አፈር እንዳይሸረሸር የሚረዱ የመከላከያ ዘዴዎች፦ ዛፍ መትከል፣ የዕፅዋት መቃጠልን መከላከል፣ እርከን መሥራት፣የግጦሽ መሬትን ከመጠን በላይ አለማስጋጥ አፈር በጎርፍና በንፋስ አማካኝነት እንዳይሸረሸር የሚረዱ ናቸው።

የእፅዋት አጠባበቅ ዘዴዎች

የዕፅዋት ጥበቃ ማለት ዛፎችን ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ አለመጨፍጨፍ እና አለማቃጠል ነው።

የዕፅዋት ውድመትን ለመከላከል የሚጠቅሙ ዘዴዎች፡- ማንኛውንም ዛፍ ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ እፅዋቶች እንዳይቃጠሉ ጥናቃቄ ማድረግ፣ ለአገልግሎት በተቆረጡ ዛፎች ምትክ ብዙ የዛፍ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ የመሳሰሉት ናቸው።

የእፅዋት መትከል አስፈላጊነት፡- የአየር ብክለትን ለመቀነስ፣ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ መገልገያ እቃዎችን ለመስራትና ለመሳሰሉት ያስፈልጋል።

የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠው ጥቅም፡- ቀጣዩ ትውልድ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ማለትም መጠለያቸውን፣ ምግባቸውን፣ ልብሳቸውንና የሚያከናውኗቸውን ስራዎች በቀላሉ ለማሟላት ይጠቅማቸዋል። ሀገራቸው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኝዎች ተስማሚ እንድትሆን ያደርጋል። ቀጣዩ ትውልድ ምቹ የሆነ አካባቢ እንዲያገኝና ደስተኛ ሆኖ እንዲኖር ይረዳዋል። በመሆኑም ቀጣዩ ትውልድ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዲከባከብ ትልቅ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን መረዳት ይኖርበታል።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች
- ሰዎች እፅዋት ሲተክሉ የሚያሳይ ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- መሬት ላይ የተሠራ እርከን ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- አግድም የታረሰ ወይም እየታረሰ ያለ እርሻ ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- የተፈጥሮ ማዳበሪያን ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።

- ማስተማር ስነ-ዘዴዎች
    - -ጥያቄና መልስ
    - - የቡድን ውይይት
    - - ገለጻ
    - - ፅብረቃ
    - - የመስክ ጉብኝት
    - - የተግባር ሥራ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣ የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- ሰዎች እፅዋት ሲተክሉ የሚያሳይ ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- መሬት ላይ የተሠራ እርከን ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- አግድም የታረሰ ወይም እየታረሰ ያለ እርሻ ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- የተፈጥሮ ማዳበሪያን ሥዕል፣ ፎቶ ግራፍ፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
    - የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

በክፍለ ከተማችን ስለሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሀፍ ንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

በክፍለ ከተማችን ስለሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረቡትን የመወያያ ጥያቄዎችና ተግባራት በቡድናቸው እንዲሰሩ ይዘሏቸው፡፡

መምህር! በቀረቡት ጥያቄዎችና ተግባራት ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ በክፍለ ከተማችን ስለሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 6 መልስ

ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች፡- የእንስሳት ፅዳጅ መጠቀም፣ እርከን መሥራት፣ እፅዋት መትከል፣ አግድም ማረስ፣ አዝዕርትን አፈራርቆ መዝራትና የመሳሰሉት ናቸው።

የቡድን ውይይት 7 መልስ

የእፅዋት መጨፍጨፍን ለመከላከል የሚጠቅሙ ዘዴዎች፡-
ማንኛውንም እፅዋት ያለበቂ ምክንያት አለመቁረጥ፣ የቤት እንስሳት እንዳይበሏቸው መከለል፣ እንዳይቃጠሉ ጥናቃቄ ማድረግ፣ በማገዶ እንጨት ምትክ የኤሌክትሪክ ኃይል ለምግብ ማዘጋጃ መጠቀም፣ ለአገልግሎት በተቆረጡ እፅዋቶች ምትክ ብዙ እፅዋቶችን መትከልና መንከባከብ የመሳሰሉት ናቸው።

ተግባር 3 መልስ

እፅዋትን የመትከል ጥቅም፡- የአየር ብክለትን ለመቀነስ፣ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅና ለመጨመር፣ ጎርፍን ለመከላከል፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ መገልገያ እቃዎችን ለመስራትና ለመሳሰሉት እፅዋትን መትከል ይጠቅማል።

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል።

- ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት ምን ማለት ነው?
- ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- ፅፅዋትን የመትከል ጥቅም እንዲዘረዝሩ መጠየቅ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጥቅም እንዲገለጹ ማድረግ።

ማጠቃለያ

ሀገር በቀል የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ያሉ ህዝቦች ከጥንት ጀምሮ የራሳቸውን እውቀት ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብትን የሚንከባከቡበት ዘዴ ነው።

ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዘዴዎች፡- የእንስሳት ፅዳጅ

መጠቀም፣ እርከን መሥራት፣ እፅዋት መትከል፣ አግድም ማረስ፣ አዝዕርትን አፈራርቆ መዝራትና የመሳሰሉት ናቸው።

እፅዋትን የመትከል ጥቅም፡- የአየር ብክለትን ለመቀነስ፣ የአፈር ለምነትን ለመጠበቅና ለመጨመር፣ ጎርፍን ለመከላከል፣ አካባቢን ለማስዋብ፣ መገልገያ እቃዎችን ለመስራትና ለመሳሰሉት እፅዋትን መትከል ይጠቅማል።

የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠው ጥቅም፡- ቀጣዩ ትውልድ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ማለትም መጠለያቸውን፣ ምግባቸውን፣ ልብሳቸውንና የሚያከናውኗቸውን ስራዎች በቀላሉ ለማሟላት ይጠቅማቸዋል። ሀገራቸው ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኝዎች ተስማሚ እንድትሆን ያደርጋል። ቀጣዩ ትውልድ ምቹ የሆነ አካባቢ እንዲያገኝና ደስተኛ ሆኖ እንዲኖር ይረዳዋል። በመሆኑም ቀጣዩ ትውልድ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዲከባከብ ትልቅ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑን መረዳት ይኖርበታል።

መልመጃ 3.3 መልስ

ሀ. 1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. ሐሰት

ለ. 1. መ 2. ለ. 3. ለ 4. ሐ 5. መ

3.4 በትምህርት ቤትና በወረዳችን የሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ--7

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ከጠናቀቁ በኋላ፦

- ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሀሳቦችን ያቀርባሉ።
- በትምህርት ቤታቸውና በወረዳቸው መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ያዘወትራሉ።
- የትምህርቱ ጭብጥ

ቆሻሻ ማለት ምርቶች የመጀመሪያ አገልግሎታቸውን ከጨረሱ በኋላ የሚገኝ ተረፈ ምርት ነው። ነገር ግን ቆሻሻዎች በራሳቸው ሀብቶች ናቸው።

ብክለት በአንድ አከባቢ በሚገኙ ሀብቶች ላይ ጎጂ የሆነ ነገር መጨመር ነው።

ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-

ቆሻሻን አለማቃጠል፡- ቆሻሻን ማቃጠል አየርን ስለሚበክል ማቃጠል የለብንም።

ቆሻሻን በየቦታው አለማጣል፡- አካባቢን ስለሚያቆሽሽ ቆሻሻን በየቦታው መጣል የለብንም።

ቆሻሻን በማጣራቀሚያ ገንዳ ውስጥ ማስቀመጥ፡- የተጠራቀሙት ቆሻሻዎች መልሰው አገልግሎት

ላይ ስለሚውሉ ማጠራቀሚያ እቃዎች ውስጥ ማስቀመጥ ተገቢ ነው።

ለማሕበረሰቡ የግንዛቤ ትምህርት መስጠት፡- ለማህበረሰቡ ስለቆሻሻ ምንነትና አወጋገድ የግንዛቤ ማሰጨበጫ ትምህርት በመስጠት ቆሻሻዎችን በአግባቡ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ ማድረግ ይቻላል።

ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፡- ፋብሪካዎች የሚለቋቸውን ጭሶች፣ ደረቅና ፈሳሽ ተረፈ ምረቶች አካባቢን ከመበከላቸው በፊት በአግባቡ አጣርቶ ማስወገድ ያስፈልጋል።

የተጠቀምንበትን ዕቃ መልሶና ደጋግሞ መጠቀም፡- የተጠቀምንባቸውን ምርቶች ከመጣል ይልቅ መልሶና ደጋግሞ መጠቀም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡- የመጠጥ ጠርሙሶችን፣ የፕላስቲክ እቃዎችን (ፌስታልና ሀይላንድ) ደጋግሞ መጠቀም እንዲሁም የወዳደቁ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን(ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒዩተር፣ ስልክ...)፣ የፕላስቲክ እቃዎችን፣ ወረቀቶችን፣ የወዳደቁ ብረቶችን፣ የምግብ ተረፈ ምርቶችንና ሌሎችን መልሶ መጠቀም የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ ይጠቅማል።

- የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች
- ውሃ ውስጥ የእንሰሳት ዕዳጅና የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ሲገቡ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- ከፋብሪካዎች፣ ከመኪናዎችና ቆሻሻዎች ሲቃጠሉ የሚወጣ ጭስ ወደ ከባቢ አየር ሲሰራጭ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- የማይበሰብሱ(የፕላስቲክ ወጤቶች፣ ጠርሙሶች...) አፈር ላይ ተጥለው የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
- ከፋብሪካዎች የሚወጡ ተረፈ ምርቶችና ቆሻሻዎች ተጠራቅመው ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ሥዕል፣ ቻርት፣ፖስተር ይጠቀሙ።
- መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ይጠቀሙ።
  - የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
    - - ጥያቄና መልስ
    - - የቡድን ውይይት
    - - ገለጻ
    - - ዕብረቃ
    - - የመስክ ጉብኝት
    - - የተግባር ሥራ
  - ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንዑስ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል።

- ውሃ ውስጥ የእንስሳት ፅዳጅና የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ሲገቡ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- ከፋብሪካዎች፣ ከመኪናዎችና ቆሻሻዎች ሲቃጠሉ የሚወጣ ጭስ ወደ ከባቢ አየር ሲሰራጭ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- የማይበሰብሱ(የፕላስቲክ ወጤቶች፣ ጠርሙሶች...) አፈር ላይ ተጥለው የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- ከፋብሪካዎች የሚወጡ ተረፈ ምርቶችና ቆሻሻዎች ተጠራቅመው ጥቅም ላይ ሲውሉ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡

• የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

በትምህርት ቤትና በወረዳችን ስለሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች ንዑስ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሀፍ ንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

• የትምህርቱ አቀራረብ

በትምህርት ቤትና በወረዳችን ስለሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረቡትን የመወያያ ጥያቄዎችና ተግባራት በቡድናቸው እንዲሰሩ ይዘሏቸው፡፡

መምህር! በቀረቡት ጥያቄዎችና ተግባራት ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ በትምህርት ቤትና በወረዳችን ስለሚስተዋሉ ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 8 መልስ

‘

ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-

ቆሻሻን አለማቃጠል፣

ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል፣

ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስቀመጥ፣

ቆሻሻን ማጠራቀሚያ እቃ ውስጥ ማስቀመጥና ሌሎችም፡፡

ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-

ቆሻሻን ማቃጠል፣

ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣

የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን አፈር ላይ መጨመር፣

የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን በአንድ ላይ ማስቀመጥና ሌሎችም፡፡

ተግባር 4 መልስ

ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ የሚገኙትን ቆሻሻዎች ለማስወገድ የተጠቀሙበት ዘዴ ቆሻሻን በየቦታው ሳይጥሉ በቆሻሻ ማስቀመጫ እቃ ውስጥ በማስቀመጥ ተሰብስበው ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ሊያርጉ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤታቸው ሳቢና ማራኪ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ስለቆሻሻ ምንነት መጠየቅ፡፡
- ብክለት ማለት ምን ማለት ነው?
- ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
- ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
- መልሶና ደጋግሞ ስለመጠቀም ምንነት መጠየቅ፡፡

ማጠቃለያ

ቆሻሻ ማለት ምርቶች የመጀመሪያ አገልግሎታቸውን ከጨረሱ በኋላ የሚገኝ ተረፈ ምርት ነው፡፡

ብክለት በአንድ አከባቢ በሚገኙ ሀብቶች ላይ ጎጂ የሆነ ነገር መጨመር ነው።

ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች የሚባሉት፡- ቆሻሻን አለማቃጠል፣ ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል፣ ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስቀመጥ፣ ቆሻሻን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃ ውስጥ ማስቀመጥና የመሳሰሉት ናቸው።

ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች የሚባሉት፡- ቆሻሻን ማቃጠል፣ ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣ የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን አፈር ላይ መጨመር፣ የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን በአንድ ላይ ማስቀመጥና የመሳሰሉት ናቸው። የተጠቀምንባቸውን ቁሳቁሶች መልሶና ደጋግሞ በመጠቀም የምናወጣቸውን ወጪና ብክለትን መቀነስ ይቻላል።

መልመጃ 3.4 መልስ

- ተገቢ የሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-
  - ቆሻሻን አለማቃጠል፣
  - ቆሻሻን በየቦታው አለመጣል፣
  - ፋብሪካዎች ማጣሪያ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣
  - የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን ለይቶ ማስቀመጥ፣
  - ለቆሻሻን በቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቃ ውስጥ ማስቀመጥና ሌሎችም።
- ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፡-
  - ቆሻሻን ማቃጠል፣
  - ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣
  - የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን አፈር ላይ መጨመር፣
  - የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን በአንድ ላይ ማስቀመጥና ሌሎችም።

3.5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች

የተመደበለት ክፍለ ጊዜ--5

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፦

- ቆሻሻን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢያቸው ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ ይገልጻሉ።
- ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሀሳብ ይሰጣሉ።
  - የትምህርቱ ጭብጥ

ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያስከትላል። እነዚህም፡-

ጎርፍ፡- የውሃ መፍሰሻ ቦይ ውስጥ ቆሻሻዎችን መጣል ዝናብ በሚዘንብበት ሰዓት ውሃው መፍሰሻ ሲያጣ ጎርፍ ይከሰታል።

የአካባቢ ብክለት፡-ቆሻሻዎች በየአካባቢው ያለአግባብ ሲጣሉ ውሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ምግብና የመሳሰሉት እንዲበከሉ ያደርጋል፡፡

የበሽታ መስፋፋት፡- ቆሻሻ በአግባቡ ካልተወገደ ውሃ፣ አየር፣ ምግብና የመሳሰሉት ስለሚበከሉ በሽታዎች በቀላሉ እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ጉንፋን፣ የአንጀት ተስቦ፣ ተቅማጥ፣ ወስፋትና የመሳሰሉት በሽታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

ንጽህናው የተጠበቀ አካባቢ፡- ሥራን ደስተኛ ሆኖ ለመሥራት፣ ለመዝናናት፣ በሽታን ለመከላከል፣ ንፁህ አየር ለማግኘት፣ ጎብኝዎችን ለመሳብ፣ ደስተኛ ሆኖ ለመኖርና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡፡

- የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የውሃ መፍሰሻ ቦይ በቆሻሻ ተዘግቶ ጎርፍ ሲከሰት የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ቪዲዮ፣ ፖስተር ይጠቀሙ፡፡
- በየቦታው ቆሻሻ የተጣለበት አካባቢንና ንፁህ አካባቢን በንፅፅር የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ቪዲዮ፣ ፖስተር ይጠቀሙ፡፡
  - የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
    - ጥያቄና መልስ
    - የቡድን ውይይት
    - ገለጻ
    - ዕብረቃ
    - የመስክ ጉብኝት
    - የተግባር ሥራ
- ቅድመ ዝግጅት

መምህር! የንፁህ ርዕሱን ዝርዝር የመማር ብቃት በመከተል የተማሪዎችን ተግባራት፣የመመዘኛ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ከፋፍሎ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

- የውሃ መፍሰሻ ቦይ በቆሻሻ ተዘግቶ ጎርፍ ሲከሰት የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ቪዲዮ፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡
- በየቦታው ቆሻሻ የተጣለበት አካባቢንና ንፁህ አካባቢን በንፅፅር የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፣ ሥዕል፣ ቻርት፣ ቪዲዮ፣ ፖስተር ያዘጋጁ፡፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች ንፁህ ርዕስን በማስተዋወቅ በመማሪያ መጽሀፍ ንፁህ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ተማሪዎች ስላላቸው ቅድመ እውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡ በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ ፣ባህርይና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት ይኖርብዎታል፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ስለተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎችና ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ዝርዝር ሁኔታ የሚያውቁትን ይጠይቋቸውና የቀረቡትን የመወያያ ጥያቄዎችና ተግባራት በቡድናቸው እንዲሰሩ ይዘሏቸው፡፡

መምህር! በቀረቡት ጥያቄዎችና ተግባራት ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና መልሳቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዲያቀርቡ ያድርጉ፡፡ ካቀረቡ በኋላም ማነቃቂያና ማስተካከያ ያድርጉላቸው፡፡ ስለተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎችና ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ማስታወሻና ማብራሪያ ለተማሪዎች ይስጧቸው፡፡

የቡድን ውይይት 9 መልስ

ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎች፡-

- የአካባቢ መቆሸሸ
- የበሽታ መስፋፋት
- የጎርፍ መከሰት
- የአየር መበከልና ሌሎችም፡፡

- ምዘናና ግምገማ

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ በመማራቸው ያዳበሩትን ግንዛቤ ለመመዘን ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል፡፡

- ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተፅዕኖዎችን እንዲዘረዝሩ መጠየቅ፡፡
- ንፅህናው የተጠበቀ አካባቢ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ሀሳብ እንዲሰጡ መጠየቅ፡፡

ማጠቃለያ

ተገቢ ያልሆነ የቆሻሻ አወጋገድ የተለያዩ ተፅዕኖዎችን ያስከትላል፡፡ እነዚህም፡-

ጎርፍ፡- የውሃ መፍሰሻ ቦይ ውስጥ ቀሻሻዎችን መጣል ዝናብ በሚዘንብበት ሰዓት ውሃው መፍሰሻ ሲያጣ ጎርፍ ይከሰታል፡፡

የአካባቢ ብክለት፡-ቆሻሻዎች በየአካባቢው ያለአግባብ ሲጣሉ ውሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ምግብና የመሳሰሉት እንዲበከሉ ያደርጋል፡፡

የበሽታ መስፋፋት፡- ቆሻሻ በአግባቡ ካልተወገደ ውሃ፣ አየር፣ ምግብና የመሳሰሉት ስለሚበከሉ በሽታዎች በቀላሉ እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ጉንፋን፣ የአንጀት ተስቦ፣ ተቅማጥ፣ ወስፋትና የመሳሰሉት በሽታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

ንጽህናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠው ጥቅም፡- ሥራን ደስተኛ ሆኖ ለመሥራት፣ ለመዝናናት፣ በሽታን ለመከላከል፣ ንፁህ አየር ለማግኘት፣ ጎብኝዎችን ለመሳብ፣ ደስተኛ ሆኖ ለመኖርና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡

መልመጃ 3.5 መልስ

ሀ. 1. ሐ 2. መ 3. ሀ

ለ.

1. ሥራን ደስተኛ ሆኖ ለመሥራት፣ ለመዝናናት፣ በሽታን ለመከላከል፣ ንፁህ አየር ለማግኘት፣ ጎብኝዎችን ለመሳብ፣ ደስተኛ ሆኖ ለመኖር
2. የመጠጥ ጠርሙሶችን፣ የፕላስቲክ እቃዎችን ደጋግሞ መጠቀም የወዳደቁ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን፣ የፕላስቲክ እቃዎችን፣ ወረቀቶችን፣ የወዳደቁ ብረቶችን፣ የምግብ ተረፈ ምርቶችንና ሌሎችን መልሶ መጠቀም ይቻላል::

የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

ሀ. 1. ሐሰት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. እውነት

ለ. 1. ለ 2. ለ. 3. መ 4. ሐ 5. መ

ሐ. 1. የአየር ንብረት 2. የተፈጥሮ ሀብት 3. ብክለት
4. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን 5. የአየር ሁኔታ

መ.

1. የተፈጥሮ ሀብቶች ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ናቸው። ለምሳሌ፦ አየር ለመተነፈስ፣ እፅዋት መሠረታዊ ፍላጎቶቻችን ለማሟላት፣ አፈር ለእርሻ ሥራ፣ የዱር እንሰሳት ለቱሪስት መስህብነት፣ ውሃ ለንፅህና መጠበቂያና የመሳሰሉት።
2. በአራት እነርሱም፦ መኸር፣ በጋ፣ በልግና ክረምት ናቸው።
3. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎች፦ የማገዶ እንጨት ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍ፣ ለግንባታ ሥራ እፅዋትን መቁረጥ፣ ከፍተኛ ዝናብ መዝነብ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከተሽከርካሪዎችና ቆሻሻ ሲቃጠል የሚወጡ ጭሶች፣ አርሶ አደሮች ሰፊ የእርሻ ቦታ ለማግኘት እፅዋትን መጨፍጨፍና ሌሎችም።
4. የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ውጤቶች፦ የአየር መበከል፣ ጎርፍ፣ የሙቀት መጨመር፣ የበሽታ መስፋፋት፣ የብዝኀ ሕይወት መመናመን፣ ረሃብና ድርቅና ሌሎችም።
5. ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች፦
   - ቆሻሻን ማቃጠል፣
   - ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣
   - የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን አፈር ላይ መጨመር፣
   - የሚበሰብሱና የማይበሰብሱ ቆሻሻዎችን በአንድ ላይ ማስቀመጥና ሌሎችም።

ምዕራፍ አራት

ማኅበራዊ አካባቢ

ለምዕራፉ የተመደበው አጠቃላይ ጊዜ፦ 54 ክፍለ ጊዜያት

መግቢያ

መምህር! ተማሪዎቹ በሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸው ስለቤተሰብ አባላት ፣ ከዚያም አልፎ ከአቻዎቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ስለማዳበር ተምረዋል። ይህም ማለት በተጠቀሰው ደረጃ ስላለው 'ማኅበራዊ አካባቢ' ግንዛቤው አላቸው እንደማለት ነው።

በዚሁ በሦስተኛ ክፍል ትምህርታቸው ደግሞ ስለክፍለ ከተማቸው ማኅበረሰብ ይማራሉ። በዚህ ክፍል ማሕበረሰባቸውን ሊያውቁ ከሚችሉባቸው በርካታ ጉዳዮች ሁለቱ ተመሚል። እነርሱም በክፍለ ከተማ ደረጃ ያሉትን ባህልና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ናቸው።

እንዲህ መሆኑ በአካባቢያቸው የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ የሚመለከቷቸውን እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ለመገንዘብ ይጠቅማል። እስካሁን በተደራጀ መልክ ቦታ ሳይሰጧቸው የቆዩት ማህበረሰባዊ እና ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ከባህል አንፃር እንዲያዩዋቸው በር ይከፍታል።

ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢያቸው ስለሚከናወኑ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ያላቸውን ግንዛቤ ያዳብራሉ። በስተመጨረሻም ልጆቹ ሲያድጉ ከተጠቀሱት የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ራሳቸውን በየትኛው ጎራ ማግኘት እንደሚፈልጉ ወስነው ለመንገዝ ያግዛቸዋል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ፣ በቡድን ተወያይተው ሐሳባቸውን እንዲያቀርቡ ፣ በተግባር ሰርተው እንዲያሳዩ እና የግል ሥራዎችንም ሆነ ማስረጃ እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

የተማሪን ብቃት ከመለካት አንጻር ደግሞ በክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል የተለያየ ነው። ከአጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ በላይ የሚሰሩትን ተማሪዎችን በማመስገን ጠንክረው እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል። ከአጥጋቢ የመማር ብቃት ደረጃ በታች ለሚሰሩ ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ከሚደረግላቸው ክትትል በተጨማሪ በዕረፍት ጊዜና ከመደበኛው የትምህርት ጊዜ በኋላ ልዩ የትምህርት ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፦

- የባህልን ምንነት ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን ያብራራሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን ይለያሉ።
- ባህላዊ ብዝኃነትን በሥነ ጥበብ ያደንቃሉ።
- የአየር ንብረት በክፍለ ከተማቸው በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ያብራራሉ።
- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ይለያሉ።
- የገበያ ምንነትን ይገልጻሉ።
- የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው (ውጤቶቻቸው) በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የመንገዳገጥ ዘዴዎችን ያብራራሉ።

የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች፦

4.1 የባህል ብዝኃነት
4.2. በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

4.1 የባህል ብዝኃነት

የተመደበው ጊዜ፦ 20 ክፍለ ጊዜያት

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች፦

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- የባህልን ምንነት ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን ያብራራሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን ይለያሉ።
- ባህላዊ ብዝኃነትን በሥነ ጥበብ ያደንቃሉ።
- የአየር ንብረት በክፍለ ከተማቸው በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ።

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

ሀ. የባህልና ባህላዊ ክዋኔዎች ምንነትና ምሳሌዎች

ለ. በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎች

ሐ. በክፍለ ከተማችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች

የትምህርቱ ጭብጥ

ሀ. የባህልና ባህላዊ ክዋኔዎች ምንነትና ምሳሌዎች

ባህል በበርካታ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎች (definitions) ተሰጥቶበታል። ይህም በመሆኑ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ አለው ለማለት አዳጋች ነው። አብዛኛዎቹ የሚስማሙበት ብያኔና ማብራሪያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ባህል አንድ ሕብረተሰብ ለዘመናት ያካበተው ዕውቀት ፣ ልምድ ፣ እምነትና የመሳሰሉትን የሚያካትት የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ባህል የአንድ ማኅበረሰብ የሚጋራውና ከሌላው ጎልቶ የሚታይበት መለያ ነው። አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱ የሚታወቀው በባሕሉ ነው። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የየራሱ ባህል አለው።

የባህል ምሣሌዎች፦ ቋንቋ ፣ ኃይማኖት ፣ ምግብና አመጋገብ ፣ ልብስና አለባበስ ፣ ዘፈንና ጭፈራ ፣ ሠርግ ፣ ሰላምታ አሰጣጥና የመሳሰሉት የአንድ ማኅበረሰብ የባህል መገለጫዎች ናቸው።

ባህል የተለያዩ ባህርያት አሉት። ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል። ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብም ይወራረሳል። ከዚህ በተጨማሪ ባህል ያድጋል ፤ ይለወጣል። ስለዚህ ባሕል ቋሚ አይደለም።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዩኔስኮ[1] የሚባል ግዙፍ ድርጅት በማቋቋም ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን በመለየት ፣ በመጠበቅና በመከላከል ዙሪያ ይሰራል።

የባህል ብዝኃነት ማለት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው። ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ የሚያራምደው ባህል ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ በሚያራምደው ባህል አይዋጥም። የሁለቱም ባህሎች እኩል ይከበራሉ።

እንዲሁም ዝቅተኛ የህዝብ ቁጥር ያለውን ባህል የሚያራምዱት ከነዚያ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ካለው ማኅበረሰብ ያልተናነሰ የፖለቲካ ተሳትፎ ይኖራቸዋል። ከየትኛውም ጎራ ቢሆን በብቃቱ ብቻ ተለክቶ ከዝቅተኛው የአመራርነት ቦታ እስከላይኛው የሥልጣን እርከን ድረስ ለመምራት የሚያራምደው ባህል አያግደውም።

በእርግጥ የባህሎች የዕድገት ደረጃ ይለያያል። ነገር ግን እንዲህ መሆኑ አንዱን አስወድሶ ሌላውን የሚያስኮንን አይሆንም። ምክንያቱም ሁኔታዎች ከተመቻቹለት ማንኛውም ባህል ‘ኋላቀር እንደሆነ አይኖርም። በመሆኑም የባህሎች የዕድገት ደረጃም ሆነ ሌላ መለኪያ ግምት ውስጥ ሳይገባ ሁሉም ባህሎች በእኩል ደረጃ መከበር አለባቸው። እኛ የምንከተለው ባህል ይከበር ዘንድም የሌሎችን ባህል ማክበር ትክክልና ተገቢ ነው።

ስለዚህ የባህል ብዝኀነት ሲባል በአጭሩ መከባበርን፣ ልዩነት ማድነቅን፣ መቻቻልን፣ አንዱ ከሌላው በጎ በጎውን መማር እና የመሳሰሉትን እሴቶች የሚያጠቃልል ነው።

የባህል ክዋኔ አንድ የባህል መገለጫ ሲሆን በአንድ ሕብረተሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ድርጊቶች ናቸው። የባህል ክዋኔዎችም እንደባህል ሁሉ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ሊለያዩ ይችላሉ።

ለምሣሌ፦ ባህላዊ ሕክምና ፣ ባህላዊ የመኖርያ ቤት አሠራር ፣ ባህላዊ አስተዳደር ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት መንገዶች ፣ ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥበቃና እንክብካቤ ፣ የምግብ ምርጫና ባህላዊ የምግብ አሠራር ፣ ወላጆች ልጆችን የሚንከባከቡበት መንገድ ፣ ባህላዊ ደስታና ሐዘንን የመግለጫ መንገዶች ፣ የዕለት ተዕለት ህይወታችን የምንመራባቸው እንቅስቃሴዎችና የመሳሰሉት እዚህ ውስጥ ይመደባሉ።

ለ. በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተለያዩ ባህሎች

እርግጥ ነው ፤ በተለያዩ አከባቢዎች የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የሚጋሩዋቸው ባህሎች አሉ። ነገር ግን ባህል ከአካባቢ አካባቢ በተፈጥሮው ይለያያል። ሁሉም አካባቢ ያለው ባህል አንድ ዓይነት አይደለም። በቋንቋ ፣ በኃይማኖት ፣ በአመጋገብ ፣ በግጭት አፈታትና በመሳሰሉት ላይ የባህል ልዩነቶች አሉ።

ባህሎች ከአካባቢ አካባቢ የሚለያዩበት ዋናው ምክንያት ባህል በባህሪው የሚቀሰም (learned) ጉዳይ ስለሆነ ነው። ሰዎች ባህልን በመደበኛም በኢ-መደበኛም መንገድ ይማሩታል። ይህም ዕውቀት የሚቀሰመው ከወላጆች ፣ ከኃይማኖታዊ አስተምህሮቶች ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ካደጉበት ማኅበረሰብ ነው። ወላጆቻቸው ስለሚለያዩ ፣ የተማሩባቸው ትምህርት ቤቶች አንድ ስላልሆኑ ፣ ያደጉበት አካባቢም ለየቅል በመሆኑ ምክንያትም ባህሎቻቸው ሊለያዩ በቁ።

የአየር ንብረት በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በሚታዩ አለባበሶች ላይ ተጽዕኖ አለው። እንደአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዓይነት ሞቃታማ የአየር ንብረት ባላቸው አካባቢዎች የሚኖር ማኅበረሰብ ስስ ልብሶችን ያዘወትራል። ጉለሌ ክፍለ ከተማ ደግሞ የአየር ንብረቱ ቀዝቃዛ በመሆኑ ወፈር ያሉ ልብሶችን መልበስ የተለመደ ነው። ይህ የሚያሳየው የአየር ንብረት የአለባበስ ባህል ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ነው።

ሐ. በክፍለ ከተማችሁ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች

መምህር! ምዕራፍ ሦስት ላይ 'ሀገር በቀል የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን የመጠበቅ ዘዴዎች' የሚል ይዘት ተማሪዎቹ ተምረዋል። ይህኛው ርዕስ ካለፈው ርዕስ ጋር በጣም ይዛመዳል።

ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ብዙ ባህላዊ ክዋኔዎች አሉ። ከእነርሱ ውስጥም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. የእንስሳት ዕዳጅ (ፍግ)ን መጠቀም - የእንስሳት ዕዳጅ (ፍግ) አርሶ አደሮች ለብዙ ክፍለ ዘመናት የአፈርን ለምነት ለመጠበቅ ብሎም ለመጨመር ጥቅም ላይ የያዋሉት ባህላዊ

ክዋኔ ነው።

2. እርከን መሥራት - የአፈር ፣ ውሃና ዕፅዋትን የመንከባከብ ባህላዊ ዘዴ ነው። ይህ ባህላዊ ክዋኔ ከሀገርም አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ስም ለማስጠራት ችሏል። እ.አ.አ በ2011 በዩኔስኮ ሊመዘገብ የቻለ የኮንሶ የእርከን ሥራ ለዚህ ታላቅ ምሣሌ ነው።
3. አግድም ማረስ - ይህ አይነት ባህላዊ ዘዴም ብዙ ጊዜ የሚተገበረው በተዳፋት አይነት የእርሻ ቦታዎች ላይ ሲሆን አፈር መሸርሸርን በ50% ይከላከላል።

ከእነዚህ በተጨማሪ በማሕበረሰቡ በተለይም በኃይማኖት ሥፍራዎች ወፎችን መግደል ፣ ዛፎችን መቁረጥ እንዲሁም ተፈጥሮን በአጠቃላይ መጉዳት እንደነውር ይታያል። እንዲሁም ማህበረሰቡ ሀብትን ሳያባክን በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት በኃይማኖት አባቶች በየጊዜው ስለሚማር የተፈጥሮ ሀብቶች የሚጠበቁበት ሌላው ባህላዊ መንገድ ነው።

ሀ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ዘዴ

1. የተጠቆሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ ባህሎችና ባህላዊ ክዋኔዎች የሚያሳዩ ስዕሎች
- የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች
- የባህል ብዝኃነትን የሚያሳዩ ቻርቶች
- የአየር ንብረት ባህሎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚያሳዩ ስዕሎች

2. የተጠቆሙ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ስለባህል ምንነት ለማስረዳት ተማሪዎችን መጠየቅና ከዚያም በምሳሌ የተደገፈ ገለፃ መስጠት
- በክፍለ ከተማቸው ስላሉ የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን አስመልክቶ ታላላቅ ሰዎች / አዛውንቶችን በመጠየቅ እንዲሰበስቡ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግና ማመቻቸት። ከዚያም በቀደመው ውይይት ዙሪያ አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት።
- በክፍለ ከተማቸው ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎችን አስመልክቶ የአካባቢ አዛውንትን (በጉዳዩ ልምድ ያላቸው ባለሙያ ቢሆኑ ይመረጣል) ለሁሉም ተማሪዎች ገለጻ እንዲያደርጉ መጋበዝ። በመቀጠልም የተገነዘቡትን እንዲያብራሩ ዕድል በማመቻቸት አጠቃላይ ገለፃ መስጠት።
- በክፍለ ከተማቸው የአየር ንብረት በባህል ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ በሚመለከት በቤታቸው ሠርተው እንዲመጡና የሠሩትን ለሁሉም እንዲያቀርቡ ማድረግ

ለ. ቅድመ ዝግጅት

- ዘርዘር ያሉና የሚያሰሩ የትምህርት ዕቅዶችን ማዘጋጀት
- የተለያዩ ባህሎችና ባህላዊ ክዋኔዎች ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅ የሚረዱ ባህላዊ ክንዋኔዎችን ፣ የአየር ንብረት ባህሎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ የሚያሳዩ ስዕሎች ፣ የባህል ብዝኃነትን የሚያሳዩ ቻርቶች በቅድሚያ ማዘጋጀት
- ርዕሱን ከማስተማር በፊት በባህል ዙሪያ የተዘጋጁ የተለያዩ የኢንተርኔትና የመፃሕፍት ዕሑፎችን በማንበብ ፣ ሰዎችን መጠየቅና ከሥራ ባልደረቦች ጋር ውይይት ማድረግ

ያስፈልጋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ለተማሪዎቹ በሚመጥን መልኩ በማዘጋጀትም አስቀድሞ እንዲደርሳቸው ማድረግ።

- በአካባቢያቸው ተዘውትረው የሚንፀባረቁ ባህሎችና የባህል ክዋኔዎችን እንዲያጤኑና በዚሁ ሐሳብ ዙሪያ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲወያዩ መጠቆምና ማበረታታት።
- አስቀድመው የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለተማሪዎች በሚገባ ሊታዩ በሚችሉ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ።

ሐ. የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

ትምህርቱን የዋናውና የንዑስ ርዕሱን ምንነትና የተማሪ መፅሐፍ ላይ የሰፈሩትን የመወያያ ጥያቄዎችን እንደመነሻ በመጠቀም ተማሪዎች የራሳቸውን ሐሳብ እና ቀደም ብሎ የነበራቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ ማበረታታት ያሻል።

ከውይይት ፣ ከግል ሥራም ሆነ ከገለፃ በፊት መሪ ጥያቄዎችን ዝርዝር በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍና ማንበብ።

በተጨማሪም የልጆቹን ተሳትፎ ለማነቃቃት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል።

1. 'ባህል' የሚል ቃል ስትሰሙ ከምን ጋር ታያይዙታላችሁ?
2. በቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ 'ባህል' ውስጥ የሚመደቡ ምን ምን ነገሮችን ታስተውላላችሁ?

2. የትምህርቱ አቀራረብ

- ተማሪዎቹ በመግቢያ ላይ የተሰጡትን ሐሳቦች ካዳመጡ በኋላ ተሳትፎአቸውን በማበረታታት የባህልን ምንነት አጠር አድርገው ይግለፁላቸው።
- የተማሪዎችን ሐሳቦች በጥንቃቄ በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝና መመዝገብ
- ለሁሉም ጥያቄዎችና ለተሰጡ ሐሳቦች ወይንም አስተያየቶች አክብሮት ማሳየት፤ ለነበራቸው አስተዋጽኦ ተማሪዎችን ማመስገን
- ተማሪዎች የመከራከሪያ ሐሳባቸውን በማስረጃ አስደግፈው ለሌሎች ተከራካሪዎቻቸው በመግለጽ እንዲመልሱ መደገፍ
- የውይይቱ አቀራረብና አካሄድን በተመለከተ አጭር ማስተዋሻ መያዝና በሌላ ጊዜ ሌላ ውይይት ለማዘጋጀትና ለማቅረብ የተያዙትን ነጥቦች እንደመነሻ መጠቀም
- ተማሪዎችን ወደ ራስ ሐሳብና አረዳደድ ብቻ እንዲመጡ አለመሞከር፤ የተለያዩ ሐሳቦችንና ዕይታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ወይንም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ግምት ውስጥ ማስገባት

- **የተግባር መልስና አሠራር ፦**

የቡድን ውይይት 1.

- ተማሪዎችን ፊት ለፊት የዓይን ለዓይን ግንኙነት በመፍጠርና በክፍል ውስጥ በመንቀሳቀስና በመዘዋወር እያንዳንዳቸው ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው መንገር (የሁሉንም የቡድን አባላት ተሳትፎ ማረጋገጥ)
- ተማሪዎች በያዙት ርዕሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ
- አንዱ ከሌላው ጋር የሚኖረውን ተግባቦት ማመቻቸት- ለምሳሌ፤ አንዱ ለሌሎች ሐሳብ ቀጥተኛ መልስ እንዲሰጡ መጠየቅ፤ አንዱ የሌላውን ሐሳብ ከመንቀፍና ከማቋረጥ ይልቅ በምክንያታዊነት እንዲያዩ ማበረታት።
- በውይይቱ የሁሉም ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎና አስተዋጽኦ እንዲኖር ማድረግና ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተጽዕኖ ሥር እንዳይሆን መቆጣጠር
- ተማሪዎች በጉዳዮች ላይ ጥልቅና ከተለያዩ ዕይታዎች አንጻር ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን ግልጽና ውስን የሆኑ ጥያቄዎችን በውይይቱ ሂደት ሁሉ ማዘጋጀት
- ዋና ዋና ሐሳቦችን በመዘርዘር፤ በመግለጽና በማጠቃለል በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ
- የተዛነፉ አካሄዶችን ያርሙ። በመቀጠልም ባህልና የባህል ብዝኀነትን ምንነትና ቀለል ያሉ ምሣሌዎችን በመስጠት ሐሳቡን ተጨባጭ ለማድረግ ይርዷቸው።

የጥያቄዎቹ መልሶች፦

1. ባህል አንድ ሕብረተሰብ ለዘመናት ያካበተው ዕውቀት ፣ ልምድ ፣ እምነትና የመሳሰሉትን የሚያካትት የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው።
2. የባህል ብዝኀነት ማለት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው።
3. ባህልም ሆነ መገለጫዎቹ ከቦታ ቦታ ይለያያሉ። ነገር ግን መገለጫዎቻቸው ቋንቋ ፣ ኃይማኖት ፣ ምግብና አመጋገብ ፣ ልብስና አለባበስ ፣ ዘፈንና ጭፈራ ፣ ሠርግ ፣ ሰላምታ አሰጣጥና የመሳሰሉት መገለጫዎች ናቸው።

የተግባር 1 መልስና አሠራር ፦

እዚህ ላይ ደግሞ ልጆቹ የተሰጣቸውን ተግባር በንቃት እንዲያከናውኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። ቀሪዎቹ ተማሪዎችም የቀረበውን ትርኢት በማድነቅ የሞራል ድጋፍ እንዲሰጡ ያድርጉ። በዚያውም የባህል ብዝኀነት ምሰሶ የሆነውን መከባበር እንዲለምዱ በር መክፈት ያስፈልጋል።

የዚህ ተግባር ዋና ዓላማ የባህል ብዝኀነትን በስነጥበብ ማድነቅ ነው። ይህ ማድነቅ 'በልዩነት ውስጥ ውበት አለ' የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ያዘለ ነው። እርስ በርሳቸው ከተለያየ ማሕበረሰብ ቢሆኑም እንዲከባበሩ ያስችላል። ለእግረ መንገድም ሐሳብን መድረክ ላይ ያለ ምንም ሐፍረት የመግለፅ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ ፣ በራስ የመተማመን (Self Confidence) ሁኔታቸውም ያድጋል።

የተግባር 2 እና 3 መልስና አሠራር ፦

- ✓ ከላይ የተማሯቸውን የባህል ሐሳቦች ምን ያህል እንደተረዱ የሚፈትሹት ተግባር 2 እና 3ን በተገቢው መንገድ ሲሰሩ ነው። ተግባር 2ን ሲያከናውኑ አዛውንቶችን የመጠየቅ ሥራ ይሰራሉ። እንደ አንድ ዕውቀት ፈላጊና እንደ አንድ ታዳጊ ተገቢውን ሥነ ምግባር አስቀድሞ ማስታጠቅ የመምህሩ ተግባር ነው። በይዘቱም የባህል ክዋኔን በሚያውቁት ክፍለ ከተማ ካሉት ባህላዊ ክዋኔዎች ጋር ተዛምዶ እንዲቀርብ ስለሚፈለግ በማስታወሻ (note) ላይ የተጠቀሰውን አጠቃላይ ብያኔን መነሻ አድርገው እንዲሰሩት ማያያዝን ያሻል። ተፈላጊውን መረጃ ተሰብስቦ ሲመጣም የተዛነፉትን መረጃዎችና ሐሳቦች ለማረም የመምህሩን ድጋፍ ያስፈልጋል።

  - ተግባር ሦስትም ካለፈው ተግባር ጋር ያልተነጣጠለ ቢሆንም ይህኛው የሚያተኩረው የአየር ንብረት በባህል ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምን ዓይነት እንደሆነ ማብራራቱ ላይ ነው። ከባህሎች አንዱ የሆነው አለባበስ ተመርጦም የተማሪ መጽሐፍ ላይ መጠነኛ ማብራሪያ ተሰጥቷል። በዚህኛው ተግባር ላይ በዋነኛነት የሚሰራው የአየር ንብረት ከአለባበስ ውጭ ባሉ ባህሎች ላይ የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ነው።
  - ለምሳሌ፦ የሞቃታማ አካባቢና የቀዝቃዛ አካባቢ ባህላዊ የቤት አሠራር አንድ አይነት አይደሉም። ምግብና አመጋገብም እንዲሁ የቆላና የደጋው ልዩነት አለው። መተዳደሪያን መርጦ የመያዝ ባህላቸውም ያየን እንደሆነ ቆላ አከባቢ ብዙ ጊዜ የእንስሳት እርባታ ሲዘወተር ፣ ደጋው ደግሞ ቅይጥ ግብርናን (mixed farming) ያዘውትራሉ።

የተግባር 4 አሠራር ፦

- ተግባር 4 ላይ ተማሪዎቹ ለተግባሩ የተቀመጠውን ግብ እንዲያሳኩ የእርስዎ ድጋፍ አይለያቸው። ተጋብዘው ለሚመጡት እንግዳም ተገቢውን ክብር ማሳየትና ከእንግዳው ማግኘት ያለባቸውን ዕውቀትና ልምድ በተገቢው መንገድ እንዲያገኙ ዕድሉን በሚገባ መጠቀም ያሻል።

መ. ግምገማና ምዘና

እያንዳንዱ ተማሪ በንዑስ ርዕሱ የሚፈለጉትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ማሳካት መቻሉን ለመገምገም እና ብቃቱን ለመመዘን የሚከተሉትን ማሳካት መቻሉን ለመገምገምና ብቃቱን ለመመዘን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ የተማሪዎቹን ብቃት ማረጋገጥ ይገባል።

- የባህልን ምንነት እንዲገልፁ መጠየቅ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን እንዲያብራሩ መጠየቅ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን መለየት።
- ባህላዊ ብዝኀነትን በሥነ ጥበብ ማድነቅ።
- የአየር ንብረት በክፍለ ከተማቸው በሚንጸባረቁ ባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መግለፅ።

•

ባህል ፣ የባህል ክዋኔና የባህል ብዝኀነትን የተመለከቱ የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች ከተዳሰሱ በኋላ መልመጃ 4.1. በቤት ሥራ መልክ እንዲሰሩ ይስጧቸው። ከዚህም በተጨማሪ በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎቹ የሚጠበቁባቸውን ተግባራት እየፈፀሙ መሆኑን በየጊዜው መከታተል ያስፈልጋል። ተማሪዎቹ የሰሩትንም ሥራ በየጊዜው እያረሙ ዋጋ ይስጡት። መልካም የብቃት ደረጃ ያስመዘገቡ ተማሪዎችም ሊመሰገኑና ሊበረታቱ ይገባል። ጠንክረው እንዲሰሩና ከራሳቸው የቀድሞ ውጤት ጋር እንዲፎካከሩ ዘወትር ማስታወስ ያስፈልጋል።

ከአጥጋቢ የመማር ብቃት በታች የሚሰሩ ተማሪዎችን ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ለይቶ ማወቅ ይገባል። በመቀጠልም አጥጋቢ የመማር ብቃቱ ላይ ፣ አለፍ ሲልም ከዚያ በላይ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳቸው ዘንድ የተለየ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይገባል።

ማጠቃለያ

ባህል ማለት የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። ባህሎች ሁሉ እኩል ናቸው። የባህል ብዝኀነት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው። የባህል ክዋኔ አንድ የባህል መገለጫ ሲሆን በአንድ ማኅበረሰብየቀን ተቀን ሕይወት ውስጥ የሚታዩ ድርጊቶች ናቸው። የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች አሉ።

የመልመጃ 4.1. መልሶች

ሀ. የ“እውነት” ፣ ወይም “ሐሰት” መልሶች

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት

ለ. የሠንጠረዡ መልሶች

ሀ	(✓) (X)
➢ የአንድ ማሕበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ነው።	✓
➢ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል	✓
➢ የሁሉም ማሕበረሰብ ባህል ተመሳሳይ ነው።	X
➢ የሁሉም ባህሎች የዕድገት ደረጃ አንድ ዓይነት ነው።	X
➢ ባህሎች ሁሉ እኩል ናቸው።	✓
➢ አየር ንብረት በባህል ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል።	✓
➢ ባህል አያድግም።	X
➢ አንድ ማሕበረሰብ ማንነቱ የሚታወቀው በባህሉ ነው።	✓

ሐ. ቋንቋ አስተርጉሞ ማቅረብ እንደአከባቢውና እንደየቋንቋው ይለያያል።

4.2. በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

የተመደበው ጊዜ፦ 34 ክፍለ ጊዜያት

ከርዕሱ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ሲያጠናቅቁ፦

- በክፍለ ከተማቸው የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ያብራራሉ።
- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ይለያሉ።
- የገበያ ምንነትን ይገልጻሉ።
- የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ልምድ ይገልጻሉ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ያብራራሉ።

የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች

ሀ. በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

ለ. የገበያ ምንነት

ሐ. በክፍለ ከተማቸው ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶች

መ. በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት፤ ውጤቶችና የግብይት ክዋኔዎች

ሠ. ለሰዎችና ለዕቃዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች

የትምህርቱ ጭብጥ

ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች (Economic Activities)፦

ሰዎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለማኖር የተለያዩ ሥራዎችን ያከናውናሉ። እነዚህ ኑሮን ለመምራት የሚያከናውኑ የሥራ ዘርፎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ይባላሉ።

አንድ ሥራ ሕጋዊ እስከሆነ ፣ ገቢ እስካስገኘና ምርት እስካመረተ ድረስ ከምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይመደባል።

ከላይ እንደተጠቀመው ሥራን የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመመደብ አንዱ መስፈርት የገቢ ምንጭነቱ ነው። ገቢ ደግሞ በገንዘብ ብቻ ላይገለፅ ይችላል። ለምሣሌ፦ ለሲሶ ፣ ለሩብ ወይንም ለግማሽ ተስማምተው ለዋናው ባለ መሬት የሚያርሱ ገበሬዎች በተጨባጭ ብር ላያገኙ ይችላሉ። ሆኖም ሥራቸው የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ከመሆን ምንም አያግደውም።

አምራችነትም እንዲሁ ሌላው መስፈርት ነው። ለምሳሌ ፋብሪካ ውስጥ የሚሰራ አንድ ሠራተኛ ዕቃዎችን በማምረት ላይ ነው። እንደ እርስዎ ዓይነት ትምህርት ቤት ውስጥ ዜጎችን እያስተማረ ያለ አንድ መምህርም አገልግሎት በመስጠት ዜጎችን በማምረት ላይ ነው። ሌላው ቀርቶ አንድ ነገር የሚመረተው ለራስ ፍጆታ ብቻ እንኳን ቢሆን ያው ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው።

ሥራ ቢሆኑም ኢ-ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች (non-economic activities) የሆኑም ግን አሉ። ለምሣሌ፦ የመንፈሳዊ ፣ የበጎ አድራጎት ፣ አርበኝነትና የመሳሰሉት ሥራዎች ከኢ-ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ጎራ የሚመደቡ ናቸው። ሥራዎች ሆነውም ሰዎች ስለፍቅሩ ብቻ የሚያከናውኗቸው ዝንባሌዎች (hobbies) ከሆኑ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ብለን መለየት ያዳግታል። መስፈርቱን የማያሟሉ የሥራ ዓይነቶች ቢኖሩም 'ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ' ጠቅለል ባለ መልኩ 'ሥራ' ከሚለው ቃል ነጥለን ማየት አንችልም። ስለሆነም ስለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ስንወያይ ስለሥራ መሆኑን እንረዳለን። ሥራ ደግሞ በባህሪው በሰው የሚፈጠር ነው። መምህር! ሥራ የሚፈጠር መሆኑን ልጆቹ ማወቃቸው አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ብዙ ሰው ተምሮ ሲመረቅ መንግሥትን ወይንም ሌላ ቀጣሪ አካል ሥራ እንዲሰጠው የመጠበቅ አዝማሚያዎች ስላሉ ነው። ይህም መስተካከል ካለባቸው ማኅበረሰቡ ውስጥ ሰርፀው ከገቡ አመለካከቶች አንዱ ነው።

ሥራ ሁለንተናዊ ጥቅሞች አሉት። በግለሰብም በአገርም ደረጃ ካየን ሥራ የሕልውና ጉዳይ ነው። መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላትና ራስን ለመቻል የሚከናወን ወሳኝ ተግባር ነው። የማይሰሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጓቸው ነገሮችን ማሟላት ስለማይችሉ ዘወትር ችግር ውስጥ ናቸው። ጥገኛም ይሆናሉ። ይኼው ፅንሰ ሐሳብ (concept) ሀገር ላይም ይሰራል።

ስለሆነም ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ አንድ ሰውም ሆነ አንድ ሀገር ሕልውናቸውን ለማረጋገጥ የሚያከናውኑት ወሳኝ ድርጊት ነው።

ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ፣ እደ ጥበብና የከተማ ግብርና ናቸው።

1. ንግድ በሰዎች መካከል የሚከናወን ዕቃን ወይም አገልግሎትን የመሸጥ ፣ የመግዛትና የመለዋወጥ እንቅስቃሴ ነው። ገንዘብ ደግሞ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና አለው።

ንግድ አምራቾችንና ተጠቃሚዎችን የሚያገናኝ ድልድይ ነው። ሆኖም ግን አንዳንዴ በአምራቹና በተጠቃሚውም በቀጥታ ሊከናወን ይችላል። በክዋኔውም ሻጮች ገንዘብ እንዲያገኙ ፣ ገዢዎች ደግሞ ፍላጎታቸው እንዲሟላ ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ሻጮችም ሆኑ ገዢዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ንግድ በአንድ አገር ውስጥ ሊከናወን ይችላል። በአገሮች መካከል የመከናወን ባህሪም አለው። አገሮች ያላቸውን ሸጠው የሌላቸውን ወይንም ተጨማሪ አስፈልጓቸው የሚገዙበት ዓለም አቀፍ ንግድም የተለመደ አሠራር ነው። የአገር ውስጡም ሆነ ዓለም አቀፉ ንግድ ማሕበረሰብ ከማሕበረሰብ ከማቀራረብ አንፃር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ የንግድ ዓይነቶች ሦስት ናቸው። እነርሱም አስመጭና ላኪ ፣ የጅምላ ንግድና የችርቻሮ ንግድ ናቸው።

በአጠቃላይ የንግዱ ዘርፍ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች መገኛ ነው። ለምሣሌ፦ ምግብና መጠጦች ፣ ልብሶች ፣ ተሽከርካሪዎች ከነ መለዋወጫ ዕቃዎቻቸው ፣ ነዳጅ ፣ ጌጣ ጌጥና የመሳሰሉት ሰዎች በንግድ ዓለም ውስጥ ከሚለዋወጧቸው ዕቃዎች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። እንደቱሪዝም ፣ የማማከር ፣ የባንክ አገልግሎትና የመንገዣ አገልግሎቶች ደግሞ የአገልግሎት የንግድ አይነት ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል።

ከረዥም ጊዜ በፊት በአገራችንም ሆነ በሌላው ዓለም የተለመደ የንግድ ዓይነት ዕቃን በዕቃ የመለወጥ (bartering) ነው። በዚህ ዘመን ግን ገንዘብ የመገበያያ መሣሪያ (medium of exchange) በመሆን ቁልፍ ሚናውን ይዞ ይገኛል።

እንደአዲስ አበባ ከተማ ፣ ንግድ በየክፍለ ከተማው ጎልቶ የሚታይ የሥራ ዘርፍ ነው። በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የጅምላና የችርቻሮ ንግድ ይካሄዳል።

2. ኢንዱስትሪ፦ የሚለውን ቃል ብያኔ ለመስጠት ከስፋቱ አንፃር አስቸጋሪ ነው። ኢንዱስትሪ ምርትን ወይም አገልግሎትን አምርቶ የሚያቀርብ የአምራች ድርጅቶች ስብስብ ነው። በዚህ ብያኔ (definition) መሠረት እርሻ ፣ የማዕድን ሥራ ፣ ዓሳ ማጥመድ (fishing) እና መሰል ዘርፎችም ኢንዱስትሪ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም ቱሪዝም ፣ ስፖርት ፣ ሙዚቃ ፣ ፊልም ፣ ፋሽንና የመሳሰሉት የኢንዱስትሪው አካል ናቸው።

በዚህ የክፍል ደረጃ ግን ልጆቹ እንዲማሩ የተፈለገው በዋነኛነት ስለዕቃ አምራቹ ኢንዱስትሪ (manufacturing industry) ነው። ከዚህ አንፃር ኢንዱስትሪ እንደሚከተለው ይብራራል።

ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችን ዘመናዊ መሣሪያዎች በመጠቀም በአጭር ጊዜና በቀላል መንገድ ለገበያነት የሚቀርቡ ዕቃዎችን የማምረት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው። እነዚህ ያለቀላቸው ዕቃዎች (finished goods) ለተጠቃሚው ሊደርሱ ይችላሉ። እንደግብአትም ለሌላ ኢንዱስትሪ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ አንድ የፕላስቲክ ጠርሙስ አምራች ኢንዱስትሪ ለአንድ ሌላ የውሃ ወይም የለስላሳ መጠጥ አምራች ድርጅት ምርቱን የሚያሸግበት የፕላስቲክ ጠርሙሶች አምርቶ ሊያቀርብ ይችላል።

ኢንዱስትሪ የጎጆ ፣ ቀላልና ከባድ ተብሎ በሦስት ሊከፈል ይችላል።

ሀ. የጎጆ ኢንዱስትሪ፦ በልምድ በተገኘ ዕውቀትና በእጅ ወይንም ቀለል ያሉ መሣሪያዎችን በመጠቀም ጎብረተሰቡ የሚፈልገውን ቁሳቁስ ወይም አልባሳት የሚያመርቱ መሰረታዊ የኢዱስትሪ ተቋማት ናቸው። የሽመና ፣ የብረታ ብረት ፣ የጌጣጌጥ ፣ የሸክላ ፣ የእንጨት ፣ የቆዳ ፣ የጥልፍና የሹራብ ሥራዎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ።

ለ. ቀላል ኢንዱስትሪ፦ በአንፃሩ ቀላል የምንለው ኢንዱስትሪ በትንሽ ኢንቨስትመንትና ቀለል ባሉ ማሽኖች ሥራውን የሚያከናወን ነው። ነገር ግን መሥሪያ ቦታ (ህንፃ) ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ብዛት ያለው ጥሬ ዕቃ ስለሚጠቀም ከጎጆ ኢንዱስትሪ የተለየ ሆኗል። የሚያመርታቸው ምርቶችም ብዙ ጊዜ በቀጥታ ለተጠቃሚ የሚደርሱ በመሆናቸው ደግሞ ከከባድ ኢንዱስትሪ ከሚለያይባቸው ነጥቦች አንዱ ነው።

የጨርቃ ጨርቅ ፣ የምግብ ፣ የወረቀት ፣ የሕትመት ፣ የቆዳ መሰል ኢንዱስትሪዎች ለዚህ እንደምሣሌ ተጠቃሽ ሲሆኑ በአብዛኛው የእርሻ ውጤቶችን እንደጥሬ ዕቃ ይጠቀማል።

ሐ. ከባድ ኢንዱስትሪ የሚጠይቀው የገንዘብ ፣ የመሣሪያ አይነትም የሆነ የብቁ ባለሙያዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ምርቱም በዚያው ልክ ከፍተኛ ነው። የነዳጅ ማጣሪያ ፣ የብረት ፣ የሲሚንቶ ፣ የኬሚካል ፣ የጦር መሣሪያ ፣ የተሽከርካሪ ማምረቻና የመሳሰሉት እዚህ ውስጥ ይመደባሉ።

ከዚህ ከኢንዱስትሪ ዘርፍ ጋር በተገናኘ በታሪክ እጅጉን የገነነው የኢንዱስትሪ አብዮት (Industrial Revolution) ነው። ይህ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ተጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ መላ አውሮፓንና አሜሪካን ያጥለቀለቀው አብዮት የፈነዳው በእግሊዝ አገር ነበር። መጠነኛ የጎጆ ኢንዱስትሪና እደ ጥበብን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚናም ተጫውቷል።

በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ዘመናዊ የማምረቻ ኢንዱስትሪ የተጀመረው በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነው። አሁን በዘመናችን ፣ በተለይም በመዲናዋ አዲስ አበባና ዙሪያዋ በርካታ የጨርቃ ጨርቅ፣ የመጠጥ፣ የእንጨት ውጤቶች፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የብረታ ብረት፣ የጫማ፣ የሕንፃ መሣሪዎያች፣ የሕትመት ውጤቶች፣ የኬሚካል ውጤቶች ወዘተ ኢንዱስትሪዎች አሉ።

3. እደ-ጥበብ ሰዎች እጃቸውን ወይም ትንንሽ መሣሪያዎችን በመጠቀም ዕቃዎችን የሚያመርቱበት የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው። እደ ጥበብም ራሱን የቻለ የጎጆ ኢንዱስትሪ ነው። ከላይ የተጠቀሰው ታሪካዊው የኢንዱስትሪ አብዮት ለመሳካቱ እንደ ጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለገለው ይሄው የእደጥበብ ዘርፍ ነው።

እደጥበብ የአንድን አከባቢ ባህል ለመግለፅ ሁነኛ መንገድ ነው። 'ባህላዊ' ማለት የአንድ ማኅበረሰብ መለያነትን እንጂ 'ኋላቀርነትን አያመለክትም። ለምሳሌ፦ የሽመና ፣ የብረታ ብረት ፣ የጌጣጌጥ ፣ የሸክላ ፣ የእንጨት ፣ የቆዳ የጥልፍና የየሹራብ ሥራዎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። ዘመኑ በሚፈልገው ደረጃ እየተሻሻሉና ፈጠራ እየታከለባቸው ከተሰሩ ከአገር ውስጥ ገበያውም በላይ ዓለም አቀፍ ገበያው ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት የአገር ዋልታ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው። በአገር ውስጥም ቢሆን ብዙ ጊዜ ጎብኚዎች ከስጦታ መሸጫ ሱቆች (Souvenir shops) ሲሸምቷቸው ማየት የተለመደ ነው። ነገር ግን በዚህ ደረጃ ለመጠቀም ከማሰብ ይልቅ እዚህ ሥራ ላይ የተሰማራውን የሕብረተሰብ ክፍል በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ የተለያዩ ስሞችን በመስጠት የማሸማቀቅ ድርጊቶች ይስተዋሉ ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ የክፍለ ከተማ አካባቢዎች በርካታ ሀገር በቀል የእደ-ጥበብ ውጤቶች ይመረታሉ።

4. ግብርና

መሠረታዊ መነሻውን ስንፈትሽ ግብርና የሥልጣኔ ጥንስስ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በታሪኩ የሚታደኑ እንስሳትና ለምግብነት የሚሆኑትን ፍራፍሬዎችን ተከትሎ መንቀሳቀሱን በማቆም አንድ ቦታ መኖሪያ ቀልሶ በቋሚነት ወደ መኖር የተሸጋገረው በግብርና አማካኝነት ነው።

ግብርና በጣም አስፈላጊ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር መሰረታዊ የሆነውን ምግብ የሚያመረተው በግብርና ሥራ ነው።

ግብርና በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። እነርሱም፦ እርሻና የእንስሳት እርባታ ናቸው።

አልፎ አልፎ ቅይጥ ግብርናን (mixed farming) በመጨመር በሦስት ሊከፈል ይችላል። በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ ሰዎች አርሶ አደሮች ይባላሉ። በእንስሳት እርባታ የሚተዳደሩት ደግሞ አርብቶ አደሮች ይባላሉ። ሁለቱም የግብርና ዓይነቶች እርስ በርስ የመመጋገብ ባህሪ አላቸው። እንስሳት ለእርሻው ሥራ በብዙ መልኩ ወሳኝ ናቸው። እርሻውም እንዲሁ ለእንስሳቱ ህይወት ነው።

ሰብል ማምረት በሁለት ዓይነት መንገዶች ሊከናወን ይችላል። የመጀምሪያዎቹና በአከባቢያችን በስፋት የተለመዱት 'ኋላቀር መሣሪያዎች ናቸው። ዶማ ፣ መኮትኮቻ ፣ በጥማድ ከብቶች ላይ በማዋል የሚታረስባቸው ሙሉ የእርሻ መሳሪያዎች ተጠቃሽ ናቸው። በዚህ መንገድ የተመረተው ሰብል እንደ አገር ራስን ለመቻል በሚደረግ ጥረት የሚኖረው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው።

በሌላ በኩል ትራክተሮችና መሰል ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በአጭር ጊዜ ብዙ ለመሥራት ይጠቅማል። በዚሁም ሰፊ የእርሻ ቦታን በአጭር ጊዜ ለማረስ ያስችላሉ። ምርቱ ለመሰብሰብም የሚያስችሉ ቴክኖሎጂ ያፈራቸው በርካታ ዘመናዊ መሣሪያዎች ስላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርቱ ተሰብስቦ የታቀደለት ዓላማ ላይ ይውላል። የከብት እርባታም እንደሰብል ማምረቱ ሁሉ ዘመናዊና ኋላቀር አካሄዶች አሉት።

እንደአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ የወንዝ ዳርቻዎችና የመኖርያ ግቢዎች ውስጥ ልዩ ልዩ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ይመረታሉ። እንዲሁም የእንስሳት እርባታ አለ።

ግብርና አንዱ የምግብ ምንጭ ነው። ከሌሎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በበለጠ ከተፈጥሮ ጋር ግንኙነት አለው። ለኢንዱስትሪና ለእደ-ጥበብ ጥሬ ዕቃዎችን ያቀርባል። እዚህ ወስኝነቱ በተግባር በተረጋገጠ የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች እንደሌላው ሁሉ ክብር ይገባቸዋል።

በአጠቃላይ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ተመሳሳይ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የለም። ለምሳሌ፦ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ ቀጠና በመሆኑ ብዛት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ይገኙበታል። የኮልፌ ቀራንዮ፣ የጉለሌ፣ የቦሌ፣ የየካ ፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ፣ የለሚ ኩራና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተሞች ደግሞ የከተማ ግብርና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በስፋት ይታይባቸዋል። የአዲስ ከተማ፣ የልደታ፣ የአራዳና የቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ደግሞ ሰፊ የንግድ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይካሄድባቸዋል።

ሆኖም ሥራዎቹ በአጠቃላይ 'የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን' ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ ክብር የሚገባቸው ናቸው። ምክንያቱም የገቢ ምንጭ ሆነው ኑሮ ለመምራት ፣ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ፣ በግብርና በቀረጥ መልክ ከዘርፎቹ በሚገኘው ገቢም የተለያዩ የመሠረተ ልማት አውታሮች (infrastructures) እንዲገነቡና እንዲስፋፉ ቁልፍ ሚናውን ይጫወታል። በተጨማሪ የተለያዩ የማሕበረሰቡ ችግሮችን ከማቃለል አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበርከታሉ።

ሀ. በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ለመኖር የተፈጥሮ ሀብቶች ያስፈልጓቸዋል። ለምሳሌ፦ ሰዎች

የተፈጥሮ አየርን ይተነፍሳሉ፤ ውሃን ይጠቀማሉ፤ እንዲሁም ከእንጨትና ሌሎች ማዕድናት መኖሪያቸውን ይሰራሉ። በርካታ ጥቅሞች የሚሰጠንን የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብና መጠበቅ አለብን።

ነገር ግን አንዳንድ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

የኢንዱስትሪ አብዮት ያበረከተው መልካም ነገርን ያህል የሰው ልጅና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖውን አሳድሯል። በፍጥነት እያደገ ያለውን የህዝብ ቁጥር የምግብ ፣ የልብስና የመጠለያን ጨምሮ በርካታ መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉት። ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ኢንዱስትሪዎች ከንግዱ ዘርፍ ጋራ በመቀናጀት ዘወትር ይሰራሉ። በሂደቱም ደንን ይጨፈጭፋሉ ፣ የባሕርና የየብስ እንስሳትን በስፋት ያጠምዳሉ ፣ ማዕድናትን ቆፍረው ያወጣሉ። ይሄን ሁሉ ጥሬ ዕቃ በኢንዱስትሪ በኩል ለተጠቃሚዎች ተዘጋጅቶ ለገበያ ይቀርባል። በውጤቱ በርካታ የማሕበረሰብ ችግሮች ተፈተው ኑሮን ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ቢያቀልም የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ግን አሉታዊ ተጽዕኖውን አሳድሯል።

ላለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት ብቻ የንግዱ ዘርፍ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ተመንድጓል። በዚህ በአንፃራዊነት አጭር ሊባል የሚችል ጊዜ የንግዱ ዘርፍ 27 ዕጥፍ ለማደግ ችሏል። በንግድ ድርጅቶች መካከል ያለው ፉክክሩም በእጅጉ አይሏል። የዓለም የንግድ ድርጅት (WTO) ይህንኑ ትርፍን ብቻ እንደራዕይ አንግቦ የሚንቀሳቀስ የንግድ አካሄድ የቁልቁለት ፉክክር (race to the bottom) በማለት ይገልፀዋል።

ንግድና ኢንዱስትሪ ብቻ ግን አይደሉም። ሁሉም የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ለሕብረተሰብ የሚጠቅሙትን ያህል የተፈጥሮ ሀብትን በመጉዳት በኩልም አሉታዊ ሚና እየተጫወቱ ነው። የሚከተሉትን ቀላል ምሳሌዎች እንመልከት፦

ንግድ፦

- የፕላስቲክ ምርቶች አገልግሎታቸው ሲያበቃ በተገቢው መንገድ ካልተወገዱ ከባቢ አየርን ይበክላሉ።
- ምግብን አዘጋጅተው የሚሸጡ ነጋዴዎች የማገዶ እንጨትን ለማግኘት ሲሉ ደንን ይጨፈጭፋሉ።

ኢንዱስትሪዎች፦

- የሚለቀቀው ጭስ አየርን ይበክላል።
- የፋብሪካዎቹ ፍሳሽ ቆሻሻም እንደ ውሃና አፈር ባሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ያደርሳል።

የእደ-ጥበብ ሥራ፦

- ደን እንዲጨፈጨፍና አፈር እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናሉ።

ግብርና፦

- ሰዎች ለግብርና ሥራ የሚሆን መሬት ለማግኘት ደንን ይጨፈጭፋሉ።

በአጠቃላይ ብዙ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠቀሙት የተፈጥሮ ሀብቶችን ነው። በተጨማሪም ቆሻሻና ተረፈ ምርት በአግባቡ ባለመወገዳቸው ምክንያት ውሃን ፣ ዕጽዋትንና አየርን ይበክላሉ። ስለሆነም ሥራዎቹ ሲሰሩ የተፈጥሮ ሀብቶችን በማይጎዳ መልኩ እንዲሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። በሥራው ሂደት የሚገኙ ተረፈ ምርቶችንና ቆሻሻዎችን በተገቢው መንገድ ማስወገድ የተፈጥሮ ሀብቶች ለመጠበቅ ይረዳል። ምክንያቱም የተፈጥሮን ሀብቶች ከተበከሉ፣ ከተጎዱና ከጠፉ የሰው ልጅ በሕይወት መኖር አይችልም።

መምህር! ይህንን ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ መነሻ በመያዝ አከባቢያዊ ምሣሌ በመስጠት ለልጆቹ ነገሩን ይበልጥ ያብራሩላቸው።

ለ. የገበያ ምንነት

ገበያ ማለት የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ቦታ ነው። ገበያ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች ገዥና ሻጭ ይባላሉ። ሻጮቹ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ይዘው ወደ ገበያ ሲቀርቡ ገዢዎቹ በበኩላቸው ገንዘብ ይዘው ይቀርባሉ። ይህ መገበያያ ቦታ ልዩ ህንፃ ኖሮት የሚከናወን ወይም ክፍት የሆነ ቦታ ላይ የሚከናወን ሊሆን ይችላል።

ዘመናዊ ግብይት ላይ ደግሞ ገዢው ወደ ገበያ በአካል መሄድ ሳይጠበቅበት የሚገዛውን ነገር በድህረ-ገፅ አማካኝነት ምስሉን እና አስፈላጊ መረጃዎችን አይቶ በመምረጥና ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ዕቃውን ይረከባል።

ሐ. በክፍለ ከተማቸው ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶች

መምህር! በምዕራፍ ሦስት ትምህርትዎ ላይ ስለተፈጥሮ ሀብት ምንነትና እንክብካቤ አስተምረዋል። የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ማጎበረሰብን ይጠቅማል። በተቃራኒው ደግሞ የተፈጥሮ ሀብቶችን መጉዳትና ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት ለአደጋ ይዳርጋል።

ከተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ውጤቶችን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንሆናለን። ለምሣሌ፦ የተፈጥሮ ውሃን በመንከባከብ የታሸገ ውሃ ለገበያ ማቅረብ ይቻላል። የተፈጥሮ ደኖችን በመንከባከብ የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን መሥራት ይቻላል። አፈርን በመንከባከብ ደግሞ የተለያዩ የእደ-ጥበብ ውጤቶችን ለማምረት ያስችላል። ለዱር እንሰሳት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ጎብኚዎችን በመሳብ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ።

መ. በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችና የግብይት ክዋኔዎች

በአካባቢያችሁ ገበያዎች የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸው ለሽያጭ ይቀርባሉ። ለምሳሌ፦ የተጣራ ውሃ፣ የእንጨት ውጤቶች፣ የሸክላ ሥራዎች፣ የማዕድን ውጤቶችና የመሳሰሉት በተለያየ መልክ ለገበያ ይቀርባሉ።እነዚህና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸው ለኑሮ ጠቃሚ በመሆናቸው ገበያ በሚቀርቡበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ተፈላጊነት አላቸው። ጥሩ የገበያ ክዋኔ አላቸው። ነገር ግን የምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ስላስገኙልን ብቻ እንክብካቤና ጥበቃን በመተው ልንጠቀምባቸው አይገባም። ምክንያቱም ካልተንከባከብናቸው ይባክናሉ፤ እኛም እንጎዳለን። ከዚያም አልፎ በጣም ከተመናመኑ ህይወታችን አደጋ ውስጥ ይወድቃል።

ሠ. ለሰዎችና ለዕቃዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች

መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ዘዴ ነው። መጓጓዣዎች ሰዎች ረዥም ርቀትን በአጭር ጊዜ ለመድረስ የፈጠሯቸው ዘዴዎች ናቸው።

የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም፦ ባህላዊ መጓጓዣ እና ዘመናዊ መጓጓዣ ናቸው።

1. ባህላዊ መጓጓዣ፦ሰዎችንና ምርቶችን በሰው፣ በአህያ፣ በበቅሎ፣ በፈረስና በግመል ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት የመጓጓዣ ዓይነት ነው። ለብዙ ዘመናት አገልግሎት ላይ የዋለ ነው። አንዳንድ ከመሐል ከተማ ርቀው የሚገኙ ሰዎች አሁንም ድረስ ባህላዊ መጓጓዣዎችን ይጠቀማሉ።
2. ዘመናዊ መጓጓዣ፦ ሰዎችንና ምርቶችን በመኪና፣ በባቡር፣ በመርከብ፣ በአውሮፕላን ከቦታ ቦታ የምናንቀሳቅስበት የመጓጓዣ ዓይነት ነው። ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ውድና ፈጣን ናቸው።

መጓጓዣዎች በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣሉ። ለምሳሌ፦ ሰዎችን ወደ ሥራ ቦታ ፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ ወደ ሐኪም ቤትና የመሳሰሉት ማድረስና መመለስ፣ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ዘርፍን ለማቀላጠፍ ፣ እቃዎች ለማጓጓዝና ምርት ለሸማቾች ለማድረስ ይጠቅማሉ።

ሀ. የትምህርት መርጃ መሣሪያና የማስተማሪያ ዘዴ

1. የተጠቀሙ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- የተለያዩ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያሳዩ ስዕሎች
- የኢንዱስትሪ ዓይነቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች
- ዋና ዋናዎቹ ምጣኔ ሀብቶች ከሚሰጡት መሰረታዊ ጥቅሞች አንፃር የሚያሳዩ ቻርቶች
- የተለያዩ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተጽዕኖ ይወምያሳድሩበት መልክ የሚያሳዩ ሥዕሎች
- የገበያ እና ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያሳዩ ስዕሎች
- ሁለቱም ዓይነት መጓጓዣ የሚያሳዩ ስዕሎች
-

2. የተጠቀሙ የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ስለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት ለማስረዳት ተማሪዎችን መጠየቅና ከዚያም

በምሳሌ የተደገፈ ገለፃ መስጠት

- በክፍለ ከተማቸው ስላሉ የተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ፣ ስለኢንዱስትሪን ምንነትና ጠቀሜታን ፣ ሥለ ግብርና ምንነትና ጠቀሜታን ፣ በክፍለ ከተማችሁ በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ፣ በክፍለ ከተማችሁ ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶች ፣ በክፍለ ከተማችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶችና የግብይት ክዋኔዎች ፣ ለሰዎችና ለዕቃዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች አስመልክተው እርስበርስ እንዲወያዩና የተወያዩትን በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግና ማመቻቸት፡፡ ከዚያም በቀደመው ውይይት ዙሪያ አጠር ያለ ማብራሪያ ማከል፡፡

- የንግድን ምንነትና ጥቅምን ለመለየት ፣ በክፍለ ከተማችሁ በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ከልጆቹ መሐል በተመለመሉ ተማሪዎች አማካኝነት በድራማ የተደገፈ የመማር ማስተማር ዘዴን መጠቀም

- የእደጥበብ ጥቅምና ምንነትን ለመለየት ተማሪዎቹ ጉብኝት እንዲያደርጉ ፤ ሲመለሱም ሐሳቦቻቸውን እና የሰበሰቡትን መረጃ ከመቀበል በኋላ ገለፃ በመስጠት ሳይንሱ በዚያ ዙሪያ የሚለውን ማሳወቅ፡፡

- የገበያ ምንነትና ጥቅምን በግል የሚሰራ ሥራ እንዲሰሩ ማድረግን ተከትሎ ገለፃ መስጠት

ለ. ቅድመ ዝግጅት

- ዘርዘር ያሉና የሚያሰሩ የትህርት ዕቅዶችን ማዘጋጀት
- የተለያዩ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ፣ የኢንዱስትሪ ዓይነቶችን የሚያሳዩ ስዕሎችና ዋና ዋናዎቹ ምጣኔ ሀብቶች ከሚሰጡት መሰረታዊ ጥቅሞች አንፃር የሚያሳዩ ቻርቶችን አስቀድሞ ማዘጋጀት የተለያዩ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበት መልክ ፣ የገበያና ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ፣ ሁለቱም ዓይነት መጓጓዣ የሚያሳዩ ሥዕሎች
- ርዕሱን ከማስተማር በፊት በምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እና ሌሎች የርዕሱ ንዑሳን ጉዳዮች ዙሪያ የተዘጋጁ የተለያዩ የኢንተርኔትና የመፃሕፍት ዕሑፎችን በማንበብ ፣ ሰዎችን መጠየቅና ከሥራ ባልደረቦች ጋር ውይይት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለተማሪዎቹ በሚመጥን መልኩ በማዘጋጀትም አስቀድሞ እንዲደርሳቸው ማድረግ፡፡
- በአካባቢያቸው ያሉ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ፣ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ላይ ያለው ተፅዕኖ ፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች እንዲያጤኑና በዚሁ ሐሳብ ዙሪያ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲወያዩ መጠቆምና ማበረታታት፡፡
- አስቀድመው የተዘጋጁ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለተማሪዎች በሚገባ ሊታዩ በሚችሉ ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ፡፡

ሐ. የመማር ማስተማር ሂደት

1. መግቢያ

ትምህርቱን የዋናውና የንዑስ ርዕሱን ምንነትና የተማሪ መፅሐፍ ላይ የሰፈሩትን የመወያያ ጥያቄዎችን እንደመነሻ በመጠቀም ተማሪዎች የራሳቸውን ሐሳብ እና ቀደም ብሎ የነበራቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ ማበረታታት ያሻል።

ከውይይት ፣ ከግል ሥራም ሆነ ከገለፃ በፊት መሪ ጥያቄዎችን ዝርዝር በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍና ማንበብ።

በተጨማሪም የልጆቹን ተሳትፎ ለማነቃቃት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል።

1. 'የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ' የሚል ሐረግ ስትሰሙ ከምን ጋር ታያይዙታላችሁ?
   - 2. ቤተሰቦቻችሁ የሚሰሩት የሥራ ዓይነት ከምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎት የቱ
   - ውስጥ ይመደባል?
   - 3. ገበያን እንዴት ትገልፁታላችሁ?
   - 4. በዕለታዊ ህይወታችን የመጓጓዣ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

2. የትምህርቱ አቀራረብ

መምህር! ለሁሉም የቡድን ሥራዎችና ሌሎች ውይይት የሚያስፈልጋቸው ተግባራት የሚከተለውን አሠራር ይከተሉ፦

- ተማሪዎቹ በመግቢያ ላይ የተሰጡትን ሐሳቦች ካዳመጡ በኋላ ተሳትፎአቸውን በማበረታታት የባህልን ምንነት አጠር አድርገው ይግለፁላቸው።
- የተማሪዎችን ሐሳቦች በጥንቃቄ በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝና መመዝገብ
- ለሁሉም ጥያቄዎችና ለተሰጡ ሐሳቦች ወይንም አስተያየቶች አክብሮት ማሳየት፤ ለነበራቸው አስተዋጽኦ ተማሪዎችን ማመስገን
- ተማሪዎች የመከራከሪያ ሐሳባቸውን በማስረጃ አስደግፈው ለሌሎች ተከራካሪዎቻቸው በመግለጽ እንዲመልሱ መደገፍ
- የውይይቱ አቀራረብና አካሄድን በተመለከተ አጭር ማስተወሻ መያዝና በሌላ ጊዜ ሌላ ውይይት ለማዘጋጀትና ለማቅረብ የተያዙትን ነጥቦች እንደመነሻ መጠቀም
- ተማሪዎችን ወደ ራስ ሐሳብና አረዳደድ ብቻ እንዲመጡ አለመሞከር፤ የተለያዩ ሐሳቦችንና ዕይታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ወይንም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ግምት ውስጥ ማስገባት

የተግባር መልስና አሠራር ፦

የቡድን ውይይት 2.

- **ተማሪዎችን ፊት ለፊት የዓይን ለዓይን ግንኙነት በመፍጠርና በክፍል ውስጥ በመንቀሳቀስና በመዘዋወር እያንዳንዳቸው ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው መንገር (የሁሉንም የቡድን አባላት ተሳትፎ ማረጋገጥ)**
- **ተማሪዎች በያዙት ርዕሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ**
- **አንዱ ከሌላው ጋር የሚኖረውን ተግባቦት ማመቻቸት- ለምሳሌ፤ አንዱ ለሌሎች ሐሳብ ቀጥተኛ መልስ እንዲሰጡ መጠየቅ፤ አንዱ የሌላውን ሐሳብ ከመንቀፍና ከማቋረጥ ይልቅ በምክንያታዊነት እንዲያዩ ማድረግ)**
- **በውይይቱ የሁሉም ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎና አስተዋጽኦ እንዲኖር ማድረግና ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተጽዕኖ ሥር እንዳይሆን መቆጣጠር**
- **ተማሪዎች በጉዳዮች ላይ ጥልቅና ከተለያዩ ዕይታዎች አንጻር ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን ግልጽና ውስን የሆኑ ጥያቄዎችን በውይይቱ ሂደት ሁሉ ማዘጋጀት**
- **ዋና ዋና ሐሳቦችን በመዘርዘር፤ በመግለጽና በማጠቃለል በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ**
- **የተዛነፉ አካሄዶችን ያርሙ። በመቀጠልም የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን በመስጠት ሐሳቡን ተጨባጭ ለማድረግ ይርዷቸው።**

የጥያቄዎቹ መልሶች፦

1. **ኑሮን ለመምራት የሚያከናወኑ የሥራ ዘርፎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ይባላሉ። አንድ ሥራ ሕጋዊ እስከሆነ ፣ ገቢ እስካስገኘና ምርት እስካመረተ ድረስ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ይመደባል። የባህል ብዝኃነት ማለት የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የባህል ልዩነታቸውን እንደያዙና አንዱ ሌላውን እንዳከበረ የሚኖርበት የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓት ነው።**
2. **የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ከቦታ ቦታ ቢለያዩም ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ እደ-ጥበብና ግብርና ናቸው። በተማሪዎቹ ሊጠቀሱ የሚችሉ አንድም እነዚ ራሳቸው አሊያም እዚህ ውስጥ የሚመደብ ሌላ ምሣሌ ሊይመጡ ይችላሉ። ለምሳሌ ንግድ ከማለት ነጠል አድርገው 'ሱቅ' ፤ ወይም 'ክሊኒክ' ቢሉ ከሐቅ አይርቁም። ምክንያቱም ሱቅ ዕቃን ፣ ክሊኒክ ደግሞ አገልግሎት የሚሰጡን የንግድ ተቋማት ናቸውና።**

የተግባር 5 አሠራር ፦

እዚህ ላይ ደግሞ ልጆቹ በእያንዳንዱ ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ዙርያ ቤተሰብን ጠይቀው ያሰባሰቡትን መረጃ ተማርኒዎች ፊት ያለፍርሐት እንዲያቀርቡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያድርጉላቸው። ቀሪዎቹ ተማሪዎችም የቀረቡትን ሐሳቦች በማድነቅ ሞራል እንዲሰጡ ያድርጉ።

የዚህ ተግባር ዋና ዓላማ ስለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች መጠነኛ ግንዛቤ አዳብረው ለወደፊት ሲያድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉ ለመወሰን እንዲረዳቸው ነው። ለእግረ መንገድም ሒሳብን መድረክ ላይ ያለ ምንም ሐፍረት የመግለፅ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ ፣ በራስ የመተማመን (Self Confidence) ሁኔታቸም ያድጋል።

የተግባር 6 አሠራር ፦

መምህር! በመጀመሪያ ከተማሪዎቹ ሰባት ሰባት አባላት ያላቸው ሁለት ቡድኖችን መስርቱ። በመቀጠልም አንዱ ቡድን 'ሻጮች'፣ ሌላኛውን ቡድን 'ገዢዎች' በማለት ሲመዳደቡ ይርዷቸው፡ ፡ ከዚያም በየቤታቸው ከሄዱ በኋላ የሻጮቹ ቡድን ዋጋቸው እስከ አሥር ብር የሚያወጡ የተለያዩ በአከባቢያችሁ የሚሸጡ እቃዎችን በወረቀት ላይ በመሳል አዘጋጁ። የገዢዎቹ ቡድን ደግሞ መቶ ብርና ከዚያ በታች ያሉ ብሮችን በወረቀት መልክ አዘጋጅተው ያቅርቡ። ብሮቹ ከለራቸው ዋናውን ብር የግድ መምሰል የለበትም። ብር አስመስለው ነጩን ወረቀት ከከረከሙት ባኋላ ለመለያነት ቁጥር ብቻ ቢፅፉበት በቂ ነው። በመጨረሻም በክፍል ውስጥ የግብይት ድራማ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ። የድራማው ተመልካቾች የሆኑት ልጆች ደግሞ ድራማውን በጥሞና ይከታተሉና ከተመለከቱት ድራማ በመነሳት ንግድ ምን እንደሆነ ከእርስዎ ጋር ይወያዩ።

የቡድን ውይይት 3.

የጥያቄዎቹ መልሶች፦

1. ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችን ዘመናዊ መሣሪያዎች በመጠቀም በአጭር ጊዜና በቀላል መንገድ ለገበያነት የሚቀርቡ ዕቃዎችን የማምረት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ነው።

ኢንዱስትሪ የጎጆ ፣ ቀላልና ከባድ ተብሎ በሦስት ሊከፈል ይችላል።

ሀ. የጎጆ ኢንዱስትሪ፦ በለምድ በተገኘ ዕውቀትና በእጅ አሊያም ቀለል ያሉ መሣሪያዎችን በመጠቀም ቁሳቁስ ወይም አልባሳት የሚያመርቱ መሰረታዊ የኢዱስትሪ ተቋማት ናቸው።

ለ. ቀላል ኢንዱስትሪ፦ በአንፃሩ ቀላል የምንለው ኢንዱስትሪ በትንሽ ኢንቨስትመንትና ቀለል ባሉ ማሽኖች ሥራውን የሚያከናወን ነው። ነገር ግን መሥሪያ ቦታ (ህንፃ) ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና ብዛት ያለው ጥሬ ዕቃ ስለሚጠቀም ከጎጆ ኢንዱስትሪ የተለየ ሆኗል።

ሐ. ከባድ ኢንዱስትሪ የሚጠይቀው የገንዘብ ፣ የመሣሪያ አይነትም የሆነ የብቁ ባለሙያዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ምርቱም በዚያው ልክ ከፍተኛ ነው።

2. ልብስ ፣ የብረታ ብረት ውጤቶች ፣ የጌጣጌጥ ፣ የሸክላ ፣ የእንጨት ውጤቶች ፣ የቆዳ ውጤቶች ፣ ጨርቃ ጨርቅ ፣ ምግብ ፣ ወረቀት ፣ ሕትመት ፣ የቆዳ ፣ የነዳጅ ማጣሪያ ፣ የብረት ውጤት፣ ሲሚንቶ ፣ ኬሚካል ፣ የተሽከርካሪ ወዘተ ሦስቱን የኢንዱስትሪ ዓይነቶች ከሚሰጡን ምርቶች ጥቂቶቹ ናቸው። እነዚህ ታዲያ በርካታ ህይወትን ቀለል የሚያደርጉና እንዲሁም ብዙ ችግር የሚፈቱ ምርቶች ናቸው። ልጆቹ በክፍለ ከተማቸው የሚገኙት ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቷቸው ምርቶች የሚሰጡትን ጥቅም ከመዘርዘራቸው በፊት የሚያውቁት የአካባቢያቸው ኢንዱስትሪ ምን እንደሚያመርት በግልጽ ማወቅ ይገባቸዋል። ከዚያም ጥቅሙን በቀላሉ ይገልጹታል።

የተግባር 7 አሠራር ፦

መምህር! ልጆቹ በአከባቢያቸው በሚገኙ የእደ-ጥበብ ሥራ የሚያከናውኑ ግለሰቦችን ወይም ድርጅቶችን ከታላላቆቻቸው ጋር በመሆን እንዲጎበኙ መመሪያ ይስጡ። ታላቅም ሌላ ሆነ ሌላ የቅርብ ሰው እንዲኖር የተፈለገው ለልጆቹ ደሕንነትና ጥያቄዎችን አስተካክሎ ለመሰንዘርና እንዲሁም መልስ አዘጋገብ ላይ እንዲረዳቸው ነው። ከጎበኙ በኋላ በተሰጡት ሦስት ጥያቄዎች ላይ ከባለሙያዎቹ ጋር በመወያየት ያገኟቸውን መልሶች በክፍል ውስጥ ያቅርቡ።

በመወያያ ጥያቄዎቹ ዙርያ ለመምህሩ መነሻ የሚሆኑ መልሶች፦

1. **በመሰረቱ የእደጥበብ ሥራ የፈጠራ ክህሎትን ያሳድጋል። ሌሎች እሱን የተጠቀሙ ወይንም የተመለከቱ ሰዎች የማነቃቃት አቅሙም ከፍተኛ ነው።**
   - **ከዚህ ሌላ አገልግሎታቸው ያበቁ የቤት ቁስቁሶችን መልሶ በመጠቀም (recycling) የአከባቢ ንፅህናን ይጠብቃል። ሪሳይክልን ያሳድጋል። ራስን በራስ በመቅጠር የሥራ አጦች ቁጥርን ከመቀነሱ ባሻገር እንዲያውም ለሌሎች የሥራ ዕድልን ይፈጥራል። በዚህም የጥበበኛውም ሆነ የሀገር ምጣኔ ሀብታዊ አቅም ይጨምራል። ባህልን ከመጠበቅ አንፃር ያለው ሚና አሌ የማይባል ነው።**
2. **ጥጥ ፣ ብረታ ብረት ፣ አፈር ፣ እንጨት ፣ ቆዳና የመሳሰሉትን እንደግብአት ይጠቀማል።**
3. **እደጥበብ የአንድን አከባቢ ባህል ለመግለፅ ሁነኛ መንገድ ነው። 'ባህላዊ' ማለት የአንድ ማኅበረሰብ መለያነትን እንጂ 'ኋላቀርነትን አያመለክትም። ለምሳሌ፦ የሽመና ፣ የብረታ ብረት ፣ የጌጣጌጥ ፣ የሸክላ ፣ የእንጨት ፣ የቆዳ የጥልፍና የየሹራብ ሥራዎች እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ። ዘመኑ በሚፈልገው ደረጃ እየተሻሻሉና ፈጠራ እየታከለባቸው ከተሰሩ ከአገር ውስጥ ገበያውም በላይ ዓለም አቀፍ ገበያው ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት የአገር ዋልታ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ ነው። በአገር ውስጥም ቢሆን ብዙ ጊዜ ጎብኚዎች ከስጦታ መሸጫ ሱቆች (Souvenir shops) ሲሸምቷቸው ማየት የተለመደ ነው።**

የቡድን ውይይት 4

የጥያቄዎቹ መልሶች፦

1. **ግብርና ሰብሎችን የማምረት እና እንስሳትን የማርባት ሥራ ነው። ግብርና ለሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር መሰረታዊ የሆነውን ምግብ የሚያመረተው በግብርና ሥራ ነው።**
2. **በሰብል ምርት ልዩ ልዩ የእህል ሰብሎችን ፣ ጥራጥሬን እና የዘይት እህሎችን ይይዛል። ለምሳሌ፦ እህሎች (ጤፍ ፣ በቆሎ ፣ ማሽላ ፣ ዘንጋዳ ፣ ዳጉሳ ፣ ስንዴና ገብስን) ፤ ጥራጥሬ (አተር ፣ ሽንብራ ፣ ባቄላና ምስር) ፤ የዘይት እህሎች ደግሞ (ተልባ ፣ ኑግ፣ ሰሊጥና ሱፍን) ያካትታሉ። የእንስሳት እርባታም ላይ የቀንድ ከብቶች ፣ ፍየሎች ፣ በጎችንና ግመሎች ወዘተ... ማርባት ያጠቃልላል።**

-
-

•

የቡድን ውይይት 5

የጥያቄዎቹ መልሶች፦

መምህር! በመጀመሪያ አራት አባላት ያለውን ቡድን መስርቱ። በመቀጠልም ከዋና ዋናዎቹ የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ለየቡድኑ አንድ አንድ ርዕስ ስጧቸው። ያንን የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በክፍለ ከተማቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በማጠያየቅና ፣ በመወያየት ያገኟቸውን መልሶች በተወካያቸው አማካኝነት በክፍል ውስጥ ያቅርቡ።

ለመምህሩ የሚሆን የመነሻ መልስ፦

ንግድ፦

- የፕላስቲክ ምርቶች አገልግሎታቸው ሲያበቃ በተገቢው መንገድ ካልተወገዱ ከባቢ አየርን ይበክላሉ።
- ምግብን አዘጋጅተው የሚሸጡ ነጋዴዎች የማገዶ እንጨትን ለማግኘት ሲሉ ደንን ይጨፈጭፋሉ።

ኢንዱስትሪዎች፦

- የሚለቀቀው ጭስ አየርን ይበክላል።
- የፋብሪካዎቹ ፍሳሽ ቆሻሻም እንደ ውሃና አፈር ባሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ያደርሳል።

የእደ-ጥበብ ሥራ፦

- ደን እንዲጨፈጨፍና አፈር እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናሉ።

ግብርና፦

- ሰዎች ለግብርና ሥራ የሚሆን መሬት ለማግኘት ደንን ይጨፈጭፋሉ።

የተግባር 8 አሠራር፦

መምህር! በመጀመርያ 10 አባላት ያለው ቡድን ይመስርቱ። በመቀጠል “ደስተኛ አካባቢ” እና “የተከፋ አካባቢ” በሚል በሁለት ቡድን ይመድቧቸው። “ደስተኛ አካባቢ” የሚባለው ቡድን ለተፈጥሮ ሀብቶቹ ተገቢውን እንክብካቤ አድርጎ ጥሩ ውጤት በማግኘት ደስተኛ የሆነውን አካባቢ ይወክል። “የተከፋ አካባቢ” የተሰኘው ቡድን ደግሞ የተፈጥሮ ሀብቶቹ የተጎዱበት አካባቢ በመወከል በድራማ መልክ ያቅርቡ።

ድራማውን ጊዜ ተወስዶ ስክሪፕት ቢዘጋጅበት ፣ ትወናውን ቢለማመዱ ደግሞ ከክፍሉ አልፎ ለትምህርት ቤቱም ሊተርፍ ይችላል።

የተግባር 9 መልሶች፦

1. ገበያ ማለት የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ቦታ ነው። ገበያ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች ገዥና ሻጭ ይባላሉ። ሻጮቹ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ይዘው ወደ ገበያ ሲቀርቡ ገዢዎቹ በበኩላቸው ገንዘብ ይዘው ይቀርባሉ። ይህ መገበያያ ቦታ ልዩ ህንፃ ኖሮት የሚከናወን ወይም ክፍት የሆነ ቦታ ላይ የሚከናወን ሊሆን ይችላል።
2. ቴክኖሎጂን በመጠቀም መገበያየት (ዘመናዊ ግብይት) ማለት ደግሞ ገዢው ወደ ገበያ በአካል መሄድ ሳይጠበቅበት የሚገዛውን ነገር በድህረ-ገፅ አማካኝነት ምስሉን አይቶ በመምረጥና ተገቢውን ክፍያ በመፈፀም ዕቃውን ይረከባል።

የቡድን ውይይት 6 መልሶች፦

1. የተጣራ ውሃ፣ የእንጨት ውጤቶች፣ የሸክላ ሥራዎች፣ የማዕድን ውጤቶችና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብት ምርቶችን (ውጤቶችን) ናቸው።

2. ከተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ውጤቶችን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ እንሆናለን። ለምሣሌ፦ የተፈጥሮ ውሃን በመንከባከብ የታሸገ ውሃ ለገበያ ማቅረብ ይቻላል። የተፈጥሮ ደኖችን በመንከባከብ የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን መሥራት ይቻላል። አፈርን በመንከባከብ ደግሞ የተለያዩ የእደ-ጥበብ ውጤቶችን ለማምረት ያስችላል። ለዱር እንሰሳት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ጎብኚዎችን በመሳብ የገቢ ምንጭ ይሆናሉ።

የቡድን ውይይት 7 መልሶች፦

1. የተጣራ ውሃ፣ የእንጨት ውጤቶች፣ የሸክላ ሥራዎች፣ የማዕድን ውጤቶችና የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብት ምርቶችን (ውጤቶችን) ናቸው።

2. የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸው ለኑሮ ጠቃሚ በመሆናቸው ገበያ በሚቀርቡበት ጊዜ ከፍተኛ የሆነ ተፈላጊነት አላቸው። ጥሩ የገበያ ክዋኔ አላቸው። ነገር ግን የምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ስላስገኙልን ብቻ እንክብካቤና ጥበቃን በመተው ልንጠቀምባቸው አይገባም። ምክንያቱም ካልተንከባከብናቸው ይባክናሉ፤ እኛም እንጎዳለን። ከዚያም አልፎ በጣም ከተመናመኑ ህይወታችን አደጋ ውስጥ ይወድቃል።

የቡድን ውይይት 8 መልሶች፦

1. መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያንቀሳቅሱበት ዘዴ ነው። መጓጓዣዎች ሰዎች ረዥም ርቀትን በአጭር ጊዜ ለመድረስ የፈጠሯቸው ዘዴዎች ናቸው።
2. እንደየክፍለ ከተማው ተጨባጭ ሁኔታ ቢለያይም ከባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶችና ከዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነት ተካተው መጠቀስ አለባቸው። ለምሣሌ፦ ባቡሩ በሚያልፍባቸው አከባቢዎች ያሉ ልጆች ባቡሩን እንደምሳሌ ቢጠቅሱት ስሕተት አይሆንም።

-
-
-

መ. ግምገማና ምዘና

እያንዳንዱ ተማሪ በንዑስ ርዕሱ የሚፈለጉትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶች ማሳካት መቻሉን ለመገምገም እና ብቃቱን ለመመዘን የሚከተሉትን ማሳካት መቻሉን ለመገምገምና ብቃቱን ለመመዘን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ የተማሪዎቹን ብቃት ማረጋገጥ ይገባል።

- በክፍለ ከተማቸው የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያብራሩ መጠየቅ።
- ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ እንዲለዩ መጠየቅ።
- የገበያ ምንነትን እንዲገልፁ መጠየቅ።
- የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው (ውጤቶቻቸው) በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ተቀባይነት እንዲገልፁ መጠየቅ።
- በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የመንገዣ ዘዴዎችን እንዲያብራሩ መጠየቅ።

ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ የንዑስ ርዕሱ ይዘቶች ከተዳሰሱ በኋላ 4.2. እና 4.3. መልመጃዎች በቤት ሥራ መልክ እንዲሰሩ ይስጧቸው። ከዚህም ባሻገር በመደበኛው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎቹ የሚጠበቁባቸውን ተግባራት እየፈፀሙ መሆኑን በየጊዜው መከታተል ያስፈልጋል። ተማሪዎቹ የሰሩትንም ሥራ በየጊዜው እያረሙ ዋጋ ይስጡት። መልካም የብቃት ደረጃ ያስመዘገቡ ተማሪዎችም ሊመሰገኑና ሊበረታቱ ይገባል። ጠንክረው እንዲሰሩና ከራሳቸው የቀድሞ ውጤት ጋር እንዲፎካከሩ ዘወትር ማስታወስ ያስፈልጋል።

ከአጥጋቢ የመማር ብቃት በታች የሚሰሩ ተማሪዎችን ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ለይቶ ማወ ይገባል። በመቀጠልም አጥጋቢ የመማር ብቃቱ ላይ ፣ አለፍ ሲልም ከዚያ በላይ ውጤት ለማስመዝገብ ይረዳቸው ዘንድ የተለየ ድጋፍና ክትትል ማድረግ ይገባል።

- ማጠቃለያ

የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ የሚባለው ገቢ የሚያስገኝ ማንኛውም ሕጋዊ የሥራ መስክ ነው። ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ፣ እደ ጥበብና ግብርና ናቸው።

ገበያ ማለት የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ቦታ ሲሆን የሚሳተፉት ሰዎች ገዥና ሻጭ ይባላሉ። መጓጓዣ ሰዎችና ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ዘዴ ነው። የመጓጓዣ ዓይነቶች ሁለት ናቸው። እነርሱም፦ ባህላዊና ዘመናዊ ናቸው።

የመልመጃ 4.2. መልሶች

ሀ. የአዛምድ መልሶች

1. ሐ
2. መ
3. ለ
4. ሀ

ለ. የሠንጠረዡ መልሶች

ተ.ቁ	ድርጊቶች	አዎ/አይደለም
1	ስርቆት	አይደለም
	መምህርነት	አዎ
	ልመና	አይደለም
	አስመጪና ላኪ	አዎ
	ጋዜጠኝነት	አዎ

ሐ. በመመሪያው መሠረት ዘርዘር ያለውን ጽሑፍ ካቀረቡ በኋላ የእርስዎ ሥራ የሚሆነው ልጁ በመረጣቸው ሙያዎች ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ማከልና ለምን ያንን ዘርፍ እንደመረጠውና ምክንያታዊነቱን ማረጋገጥ ነው።

መልመጃ 4.3

ሀ. “እውነት” ወይም “ሐሰት”

1. ሐሰት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት

ለ. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በተገቢው መልስ ሙሉ።

1. ገበያ
2. ዘመናዊ እና ባህላዊ

•
•
•

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ. “እውነት” ወይም “ሐሰት”

1. እውነት
2. እውነት
3. እውነት
4. ሐሰት
5. እውነት
6. ሐሰት
7. እውነት
8. ሐሰት
9. እውነት
10. እውነት

ለ. ምርጫ

1. መ
2. መ
3. ሐ
4. መ
5. ሐ
6. ለ

ሐ. የክፍት ቦታውን መልስ

1. ባህል
2. የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ
3. ንግድ
4. ኢንዱስትሪ
5. መጓጓዣ

መ. የሠንጠረዥ መልስ

		(✓) (X)
1	በክረምት ቆሻሻን ከጎርፍ ጋር ቀላቅሎ መድፋት።	X
2	እርከን መሥራት	✓
3	ሽንትን ከመፀዳጃ ውጭ መሽናት	X
4	የእንስሳት ፅዳጅን መጠቀም	✓

ሠ. አጭር መልስ

1. የባህል ምሳሌዎች፦ ቋንቋ ፣ ኃይማኖት ፣ ምግብና አመጋገብ ፣ ልብስና አለባበስ ፣ ዘፈንና ጭፈራ ፣ ሠርግ ፣ ሰላምታ አሰጣጥና የመሳሰሉት የአንድ ማኅበረሰብ የባህል መገለጫዎች ናቸው።
2. ዋና ዋና የምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ንግድ ፣ ኢንዱስትሪ ፣ እደ ጥበብና ግብርና ናቸው።
3. እርሻና የእንስሳት እርባታ ናቸው።
4. ሰዎችን ወደ ሥራ ቦታ፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ ወደ ሐኪም ቤትና የመሳሰሉት ማድረስና መመለስ፣ ለምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ፣ እቃዎች ለማጓጓዝና ምርት ለሸማቾች ለማድረስ ይጠቅማሉ።

ምዕራፍ አምስት

ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች

ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ፡-30

መግቢያ

ተማሪዎች በሁለተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ተምረዋል። ይህም ምዕራፍ ይህንኑ ርዕስ ሰፋ በማድረግ ይዞ የቀረበ ነው። በመሆኑም መምህር በዚህ ርዕስ ዙሪያ ተማሪዎች ያላቸውን ቅድመ ዕውቀት መረዳት ያስፈልጋል።

ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች የሚያደርሱት ተጽዕኖ በአንድ አካባቢ ብቻ የማይወሰን ድንበር አልባነው:: በመሆኑምተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ከሚባሉት ውስጥ በዚህ ምዕራፍ የተካተቱት የመንገድ ደኅንነት እና ኤች.አይ. ቪ./ኤድስ ናቸው።

የመንገድ ደኅንነት በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የቀረበው ትምህርት ተማሪዎች የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀምን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል። የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን ማክበር ከዘወትር አኗኗራቸው ጋር ቁርኝት ያለው ስለሆነ ትምህርቱን ከዕለት ተዕለት አኗኗራቸው ጋር በማያያዝ ቀርቧል። በዚህም መሰረት ትምህርቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን ስለት በመቀየስ ማስተማር ያስፈልጋል።

ሌላው ንዑስ ርዕስ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ሲሆን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዘር ቀለም እና ዕድሜ ሳይለይ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል የሚያጠቃ አስከፊ ሕመም በመሆኑ ተጽዕኖ ከሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በመሆን በዚህ ምዕራፍ ስር ተካቷል። በተለይም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምልክቶች እና በመድኃኒቶች መካከል ስላለው ግንኙነት ትኩረት በማድረግ ያስረዳል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አካል ጉዳተኞችን፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን፣ የተለያየ የትምህርት አቀባበል ስልት ያላቸውን እንዲሁም ሴት ተማሪዎችን በተለየ ትኩረት ድጋፍ በማድረግ ማስተማር ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ተማሪዎች በዚህ ርዕስ የሚማሩት መሠረታዊ ዕውቀት እንዳለ ሆኖ በዋነኛነት የትምህርቱን ርዕስ ምክንያት በማድረግ በትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች እንደመመልከት፣ መጠየቅ፣ ሥዕላዊ መግለጫዎችንና ምልክቶችን መተርጎም፣ መተንተን፣ መግባባት፣ ማስረዳት እና የመሳሰሉትን የሳይንሳዊ ምርምር ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይገባል።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች

- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-
- የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም ይችላሉ፡፡
- በኤች. አይ. ቪ እና ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል

ያለውን ግንኙነት ይለያሉ፡፡

የምዕራፉ ይዘቶች

5.1 የመንገድ ደኅንነት

5.2 ኤች. አይ. ቪ./ ኤድስ

5.1 የመንገድ ደኅንነት

የተመደበው ክፍለ ጊዜ፡-18

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ፡-

- የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም ይችላሉ፡፡

የንዑስ ርዕሱ ይዘት

መንገድ ደኅንነት

የመንገድ ደኅንነት ደንቦች

የትምህርቱ ጭብጥ

የመንገድ ደኅንነት ደንቦች የመንገድ ደኅንነትን ለመጠበቅ እና የመንገድ አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚጠቅሙን ናቸው፡፡ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በማክበር ራሳችንን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ እንችላለን፡፡

የትራፊክ አደጋ በአሽከርካሪዎች ስህተት ብቻ የሚከሰት ሳይሆን በእግረኞች ቸልተኝነትም ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለዚህ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በመረዳት ተማሪዎች ራሳችውንና ቤተሰባቸውን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅ ይችላሉ፡፡

የመንገድ ደኅንነትን በሚገባ ለመጠበቅ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን ማክበር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ደንቦቹን በሁለት ከፍለን እናያለን፡፡ እነርሱም፡- የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦች እና የአሽከርካሪ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች ናቸው፡፡ የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን ደግሞ በተሽከርካሪ ውስጥ ስንሆን እና እግረኛ ስንሆን የምንከተላቸው ደንቦች በማለት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነርሱም፡- እግረኛ ስንሆን የምንከተላቸው የትራፊክ ደንቦችና በተሽከርካሪ ውስጥ ስንሆን የምንከተላቸው የትራፊክ ደንቦች፡፡

1. እግረኛ ስንሆን የምንከተላቸው የትራፊክ ደንቦች

ሀ. የትራፊክ መብራትን መመሪያ መከተል፡፡

የትራፊክ ማስተላለፊያ መብራቶች በሁለት የሚከፈሉ ናቸው፡፡ እነርሱም፡-የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራትና የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ መብራት ናቸው፡፡

1. የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራት

እግረኞች ከአደጋ ነፃ ሆነው መንገድ እንዲያቋርጡ የሚረዱ የትራፊክ መብራቶች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ እነርሱም ከላይ ወደታች ሲዘረዘሩ ቀይ እና አረንጓዴ ናቸው፡፡ የእግረኛ ማስተላለፊያ መብራቶች በውስጣቸው የእግረኛ ምስል አላቸው፡፡

ቀይ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት ሲበራ እግረኞች መንገድ እንዲያቋርጡ አይፈቀድላቸውም:: አረንጓዴ የእግረኛ ምስል ያለበት መብራት ሲበራ እግረኞች መንገድ እንዲያቋርጡ አይፈቀድላቸውም፡፡

2. የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ መብራት

ተሽከርካሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲተላለፉ በማድረግ አደጋን ለመቀነስ ይረዳል፡፡ የተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ የትራፊክ መብራት ቀለማት ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ናቸው፡፡ ቀለማቱ የሚሰጡትም ትርጉም ይለያያል፡፡ የሦስቱ ቀለማት ትርጉም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ አረንጓዴ፡- ተሽከርካሪዎች እንዲሄዱ እና እግረኞች እንዲቆሙ የሚያመለክት ነው፡፡

ቀይ፡- እግረኞች እንዲሄዱ (እንዲያቋርጡ) እና ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ የሚያመለክት ነው፡፡

ቢጫ፡- ከቀይ ወደ አረንጓዴ እና ከአረንጓዴ ወደ ቀይ ትዕዛዝ መሸጋገሪያ ጊዜ የሚሰጥ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች መንገድ ማቋረጥ ያለባቸው ቀይ የትራፊክ መብራት ሲበራ ብቻ ነው፡፡

የትራፊክ መብራት መመሪያን ማክበር የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንብ ብቻ ሳይሆን በዋነኛነት የአሽከርካሪዎች የመንገድ ደኅንነት ደንብነው፡፡ ምክንያቱም የሁለቱንም ደኅንነት መጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም እግረኞችም አሽከርካሪዎችም የትራፊክ መብራት መመሪያን ማክበር አለባቸው፡፡

ለ. እግረኛ ሁልጊዜ የመንገዱን የግራ መስመር ይዞ መሄድ አለበት፡፡

እግረኞች የግራ መስመራቸውን ይዘው ሲሄዱ ተሽከርካሪዎች ደግሞ በቀኝ በኩል ያለውን መስመራቸውን ይዘው ስለሚሄዱና አሽከርካሪዎችና እግረኞች ስለሚተያዩ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በቀላሉ መከላከል ይቻላል፡፡

ሐ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ተሽከርካሪ መምጣት አለመምጣቱን መቃኘት፡፡

የተሽከርካሪዎች ፍጥነት ከእግረኞች የበለጠ ስለሆነ ተሽከርካሪዎች አለመኖራቸውን ካረጋገጥንበኋላ ማቋረጥ ለአደጋ ተጋላጭ እንዳንሆን ያደርጋል፡፡

መ. የቆመ ተሽከርካሪ ተከልሎ አለማቋረጥ፡፡

የቆመ መኪና የአሽከርካሪዎችንም ሆነ የእግረኞችን እይታ የሚከለክል በመሆኑ ለአደጋ ያጋልጣል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የቆመ መኪናን ተከልለው ማቋረጥ የለባቸውም፡፡

ሠ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ አለማውራት እና አለመጫወት፡፡

መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ትኩረታችንን የሚስብ ሌላ ተግባር መፈጸም ለምሳሌ፡- ወሬ ማውራት፣ ምግብ መብላት፣ ስልክ መነካካትና የመሳሰሉትን ማድረግ የለብንም፡፡ ምክንያቱም ትኩረታችን በዋናነት ስለመንገዳችን ካልሆነ በቀላሉ ለአደጋ ልንጋለጥ እንችላለን፡፡

ረ. መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ንቁ መሆን፡፡

መንገድ በምናቋርጥበት ጊዜ ንቁ መሆን አለብነ፡፡ ስለዚህ ትኩረት ሰጥተን መንገድ ማቋረጥ አለብን ፡፡

ሰ. የአስፋልት መንገድ ስናቋርጥ የእግረኞች ማቋረጫን (ዜብራን) ብቻ መጠቀም፡፡

አሽከርካሪዎችም ሆኑ እግረኞች ጥንቃቄ የሚያደርጉበትና ለእግረኞች መተላለፊያ ተብሎ የተዘጋጀልዩ ቦታ በመሆኑ ለማቋረጥ ዜብራን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

2. በተሽከርካሪ ውስጥ ስንሆን የምንከተላቸው የትራፊክ ደንቦች

ሀ. በመኪና ስንጓዝ የመኪና ቀበቶን መጠቀም፡፡

ከአቅም በላይ የሆነ አደጋ ቢከሰት ቀበቶን በመጠቀማችን ብቻ አደጋው ሊያስከትል የሚችለውን የጉዳት መጠን መቀነስ ይቻላል፡፡

ለ. ከተሸካርካሪ ስንወርድ ከተሽከርካሪው በስተቀኝ መንገድ ዳር ባለው በር መውረድ፡፡

ከተሸካርካሪ ስንወርድ በሌላ ተሽከርካሪ እንዳንጎዳ የሚደረግ ጥንቃቄ ነው፡፡

ሐ. ተሸካርካሪ በደንብ ሳይቆም አለመውረድ እና አለመውጣት፡፡

ተሸካርካሪ በደንብ ሳይቆም ለመውረድም ሆነ ለመውጣት መሞከር ለከፍተኛ አደጋ ሊያጋልጠን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በመኪና እየተጓዙ አንገታቸውን በመስኮት ማውጣት የለባቸውም፡፡

2 የአሽከርካሪ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች

ከእግረኛ ደንቦች በተጨማሪ አሽከርካሪዎችም ሊያከብሯቸው የሚገቡ የአሽከርካሪ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር፡፡

የትራፊክ ምልክቶች የመንገድ ደኅንነት መሠረቶች ሲሆኑ የመንገድ ዳር ምልክቶች በማለት ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ የመንገድ ዳር ምልክቶች በሚያስተላልፉት መልዕክት ልዩነት ምክንያት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡- የሚያስጠነቅቁ፣ የሚቆጣጠሩና መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡

1. የሚያስጠነቅቁ የመንገድ ዳር ምልክቶች

አሽከርካሪዎች ስለሚያጋጥማቸው የመንገድ ሁኔታ አስቀድመው እንዲያውቁ የሚረዳ ነው። በአብዛኛው ሦስት ማዕዘን ሆነው ዙሪያቸው ቀይ የተቀባ እና በነጭ መደብ ላይ በጥቁር ቀለም በምስል፣ በቀስት ወይም በቁጥር በመቅረጽ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው።

የሚያስጠነቅቁ የመንገድ ዳር ምልክቶች ባሉበት ሁሉ ፍጥነትንና የትራፊክ እንቅስቃሴውን መቃኘት ተገቢ ነው።

2. የሚቆጣጠሩ የመንገድ ዳር ምልክቶች

የሚቆጣጠሩ የመንገድ ዳር ምልክቶች በሦስት ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላሉ። እነርሱም የሚከለክሉ፣ ቅድሚያ የሚያሰጡና የሚያስገድዱ ናቸው።

2.1 የሚከለክሉ፡- ቅርጻቸው ክብ ዙሪያቸው ቀይ ቀለም የተቀቡና መደባች ነጭ ሲሆን የሚያስተላልፉት መልዕክትም በጥቁር ቀለም በተሰራ ሥዕል፣ ቀስት ወይም ፅሑፍ ሊሆን ይችላል።

2.2 ቅድሚያ የሚያሰጡ፡- ቅርፃቸው የተለያየ ሲሆን ምልክቶቹም የሚያስተላልፉት መልዕክት አንድ ዓይነት ነው። ይኸውም “ቅድሚያ አለህ” ወይም “ቅድሚያ ስጥ” የሚል ነው።

2.3 የሚያስገድዱ፡- ቅርፃቸው ክብ መደባቸው ሰማያዊ ሲሆን የሚያስተላልፉት መልዕክት በነጭ ቀለም በተሰራ ሥዕል፣ ቀስት ወይም ጽሑፍ ሊሆን ይችላል።

3. መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች

መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች ቅርጻቸው ዐራት ማዕዘን ሆኖ በሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም በቀጥታ መረጃ ሰጪ እና አቅጣጫ አመልካች ናቸው።

3.1 በቀጥታ መረጃ ሰጪ፡- አገልግሎት የምናገኝባቸው ቦታዎችን፣ የፍጥነት ወሰን መረጃዎችንና የመሳሰሉትን ይሰጠናል። ለምሳሌ፡-ሆቴል፣ ነዳጅ ማደያ፣ መኪና ማቆሚያ ቦታና የመሳሰሉት ናቸው።

3.2 አቅጣጫ አመልካች፡- አቅጣጫ አመልካች የመንገድ ዳር ምልክቶች የመንገድን ቅድመ ሁኔታ፣ ዘላቂ መሆንና አለመሆንን እንዲሁም የከተሞችን አቅጣጫና ርቀት በጽሑፍ ወይም በሥዕል ይገልጻል። ለምሳሌ መስቀለኛ መንገድ ላይ ወዴት እንደምንሄድ ይጠቁማል።

ለ. የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክትን ማክበር እና የመሳሰሉት ናቸው።

የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክቶች የተለያዩ ሲሆኑ የሚያስተላልፉትም መልዕክት ይለያያል። ስለዚህ የትራፊክ ፖሊስ የእጅ ምልክትን መረዳት አለብን።


ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን እና ሌሎች የትራፊክ መመሪያዎችን ሁልጊዜ ማክበር ይጠበቅብናል። ምክንያቱም ደንቦችን የማናከብር ከሆን ለትራፊክ አደጋ እንጋለጣለን።

የትራፊክ አደጋ ማንኛውንም የማኅበረሰብ ክፍል ያጠቃል። አንድ የትራፊክ አደጋ እኛ ከምንገምተው በላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ምክንያቱም አንድ የትራፊክ አደጋ ሲከሰት በተሸከርካሪው ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሱ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብና በንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳል። የጉዳቱን መጠን በጥልቀት ለመተንተን በአደጋው ቦታ ተገኝተን በቀጥታ ከምናየው ጉዳት በስተጀርባ የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መረዳት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ:- ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች ሀገር የምታጣው ጥቅም፣ የሚባክን ጊዜ፣ የንብረት ውድመት ፣ የአካል ጉዳተኝነት መጨመር፣ ወላጅ አልባ ሕፃናት ቁጥር መጨመር፣ አዛውንቶች ጧሪ ማጣት እና ሌሎች ናቸው።

ሀ/ የትምህርት መርጃ መሳሪያና የማስተማር ሥነ-ዘዴ

1.የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የመንገድ ደኅንነት ሰራተኞች በሥራ ላይ ሆነው የሚያሳዩ ሥዕሎችና ፖስተሮች
- የትራፊክ ደንቦችን የሚያሳይ ሰንጠረገዥ፣ ሥዕል፣ ፎቶግራፍና ቪዲዮ
- የትራፊክ ምልክቶች ሥዕልና ፖስተሮች
- የትረፊክ አደጋን የሚያሳይ ሥዕል፣ ፎቶግራፍ፣ ቪዲዮና ፖስተር
- ከዚህ በታች ያሉትን የትራፊክ ምልክቶች እንደየአስፈላጊነታቸው በማዘጋጀት መጠቀም



- ሥዕል 1. የትራፊክ ምልክቶች

- የመማር ማስተማር ዘዴዎች
- ስለ መንገድ ደኅንነት ደንቦችና አጠቃቀም በጥያቄና መልስ ማስተማር
- ተማሪዎች በግላቸው ቤተሰብና ታላላቆቻቸውን በመጠየቅ አንድ እውነተኛ የትራፊክ አደጋ ያስከተለውን የጉዳት መጠን እንዲተነትኑ ማድረግ።
- ተማሪዎች ስለ መንገድ ደኅንነትና አጠቃቀም በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ።
- ስለ መንገድ ደኅንነት የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው እንግዳ በመጋበዝ ስለ ትራፊክ ደንቦች፣ ስለ ትራፊክ አደጋ መንሥኤና ጉዳቶች እንዲያብራሩ ማድረግ።
- የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በምልክት የመግለጽ ጨዋታ በማጫወት ደንቦችን እንዲረዱ ማድረግ።
- ተማሪዎችን በመንገድ ላይ በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን በቤተሰብና በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲያብራሩ ማገዝ።
- ተማሪዎች እንደ ትራፊክ ፖሊስና በተሽከርካሪዎች መንገድ ላይ ኪስ የሚጫወቱ ሕፃናትን ሁኔታ በመወከል በሚና ጨዋታመንገድ ላይ ኪስ መጫወት እንደሌለባቸው እንዲያሳዩ ማድረግ ።

ለ. ቅድመ ዝግጅት

- የየዕለቱን የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጀት።
- የመንገድ ደኅንነት ሠራተኞች በሥራ ላይ ሆነው የሚያሳዩ ሥዕሎችና ቪዲዮ ማዘጋጀት።
- የትራፊክ ደንቦችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ እና ሥዕል ማዘጋጀት።
- የትራፊክ ምልክቶች ሥዕልና የትረፊክ አደጋን የሚያሳይ ሥዕል ማዘጋጀት።
- የሚና ጨዋታ አዘገጃጀት እና አቀራረብን የሚያሳይ ናሙናዎችን አስቀድሞ በማዘጋጀት ተማሪዎች እንዲረዱት ማድረግ።
- በምልክት የመግለጽ ጨዋታ መመሪያ ማዘጋጀት። መመሪያው የሚይዛቸው ዋና ዋና ነጥቦች በምልክት ከሚገልጸው/ከምትገልጸው ተማሪ ምን ይጠበቃል፣ ከቡድኑ አባላት ምን ይጠበቃል፣ ከሌሎች ቡድን አባላት ምን ይጠበቃልና ከመምህር ምን ይጠበቃል የሚሉ ናቸው።
- ተማሪዎች ሊያከብሯቸው ስለሚገቡ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች ዙሪያ የሚያስረዱ እንግዳ በመጋበዝ ሥነ-ዘዴ ለማስተማር የሚጋበዙ እንግዶችን መለየት ና የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የድርጊት መርሀ ግብሩ ሊያካትታቸው የሚገቡ ነጥቦች፡- ጊዜ፣ የእንግዳውተግባር፣ የመምህሩተግባር፣ የተማሪዎች ተግባር፣ አስፈላጊ ቁሳቁች እና ሌሎች ናቸው።

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ንዑስ ርዕሱ ስለ መንገድ ደኅንነት መሆኑን ማስተዋወቅና በንዑስ ርዕሱ ስር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ስላላቸው ቅድመ ዕውቀት መጠየቅ። ስለ መንገድ ደኅንነት እንዲወያዩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር። በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ፡-

- ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡም ሆነ ከትምህርት ቤትስትሄዱ የመንገድ አጠቃቀማችሁ ምን ይመስላል?
- በመንገድ አጠቃቀም ዙሪያ ከሌሎች ሰዎች ምን አስተዋላችሁ? የሚሉና የመሳሰሉትን መጠየቅ፡፡

በዚህም ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይ እና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ንዑስ ርዕስ የሚጠበቁትን አጥጋቢ የመማር ብቃቶችን ማስተዋወቅ፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

የመንገድ ደኅንነት፡-

ተማሪዎች ሥዕሎችን በማየት እንዲያብራሩ ማድረግና ማነቃቂያ ሐሳቦችን መስጠት፡፡ የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን የሚያብራራ አጭር ማስታወሻ መስጠት፡፡

የቡድን ውይይት -1- መልስ

በዚህ ውይይት በተማሪዎችም ሆነ በአሽከርካሪዎች ሊከበሩ የሚገባቸውን የትራፊክ ደንቦች መግለጽ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- የሚያስጠነቅቁ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የሚቆጣጠሩ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ መረጃ ሰጪ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በዚህ ተግባር ትኩረት የሚደረገው ከተማሪዎች የሚጠበቁ የትራፊክ ደንቦችን ማወቅ እና መጠቀም ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሚያውቋቸውን ያህል ጥንቃቄዎችን ከዘረዘሩ በኋላ ከተግባሩ በታች ያለውን ማስታወሻ እንዲረዱ ማድረግ፡፡

የተግባር-1- መልስ

የመጀመሪያው ተግባር የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በምልክት በመግለጽ እንዲለዩ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የግራ መስመርን ይዞ መሄድ፣ በዜብራ መሻገር፣ ቀበቶ መጠቀም፣ መንገድ ላይ ኳስ አለመጫወትና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ በዚህ መሠረት በምልክት የመግለጽ ጨዋታ መመሪያን ለተማሪዎች ማስረዳት፡፡ በመቀጠልም የእግረኞች የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በምልክት የመግለጽ ጨዋታ እንዲጫወቱ ተማሪዎችን በአራት ቡድን በመክፈል ከየቡድናቸው በምልክት ማስረዳት ይችላሉ ያሉዋቸውን ሦስት ሦስት ተማሪዎች ማስመረጥ፡ ፡ ከተመረጡት ተማሪዎች መካከል አንድ አንድ ተማሪ በየተራ በማስነሳት ከቡድኑ አባላት ውጪ ለሆኑት የመንገድ ደኅንነት ደንቦችን በሚስጥር በማሳየት በምልክት እንዲያስረዳ (እንድታስረዳ) በማድረግ ሌሎች የቡድኑ አባላት ደንቦቹን እንዲገምቱ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም ብዙ የመለሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም ሁለቱ አሸናፊ ቡድኖች እነዲጫወቱ በማድረግ ማጠቃለያ መስጠት፡፡

የተግባር -2- መልስ

ሁለተኛው ተግባር የግል ሥራ ሲሆን በጨዋታ መልክ የመንገድ ደኅንነት ደንቦች ጥሰትን ከሥዕል15 ላይ እንዲለዩ ማድረግ ነው። በዚህም መሠረት የመንገድ ደኅንነት ደንቦች ጥሰትን የሚያሳይ ሥዕል የቀረበ ስለሆነ ተማሪዎች እስከ 20(ሀያ) የሚደርሱ ሥሕተቶችን በጨዋታ መልክ እንዲለዩ በማድረግ በአጭር ጊዜ ብዙ ሥሕተቶችን የለዩ ተማሪዎችን በማበረታታት ስለሥሕተቶቹ እንዲያብራሩ ዕድል መስጠት እና ሁሉም ተማሪዎች ሥሕተቶቹን እንዲለዩ ማድረግ።

ሥሕተት ከሆኑ ድርጊቶች ውስጥ ለምሳሌ፦

1. መንገድ ላይ ኳስ መጫወት።
2. መኪናን መንገድ ላይ አቁሞ መሄድ።
3. የመንገድ ዳር ንግዶች።
4. ቤተሰብ ለልጆች የሰጠው ትኩረት ማነስ እና ሌሎች የሚጠቀሱ ናቸው።

የተግባር-3- መልስ

ሦስተኛው ተግባር እንግዳ መጋበዝ ሲሆን እንግዳው/ዋ ገጠመኞችን ሊያካትቱ እንደሚችሉ ይታመናል። በመሆኑም ለተማሪዎች ተስማሚ በሆነ መንገድቀደም ብሎ ዝግጅት የተደረገበትን የእንግዳ መጋበዝ ሂደት የድርጊት መርሀ ግብሩን በመከተል ከተማሪዎችና ከእንግዳው ጋርመወያየት። በመጨረሻም በውይይቱ ወቅት የተነሱ ፍሬ ሐሳቦችን መነሻ በማድረግ ማጠቃለያመስጠት።

የተግባር-4- መልስ

አራተኛው ተግባር የተቀረጸው ተማሪዎች በሚና ጨዋታ የትራፊክ አደጋ

መንሥኤና የሚያስከትለውን ጉዳት እንዲያሳዩ ነው። በመሆኑም የሚና ጨዋታ ናሙናዎች ላይ አጭር ገለጻ በማድረግ ተማሪዎች ተዘጋጅተው የመጡበትን የሚና ጨዋታ እንዲያቀርቡ ማድረግ። በመጨረሻም ከሚና ጨዋታው የተረዱትን በመጠየቅ ማጠቃለያ መስጠት።

የተግባር -5-መልስ

አምስተኛው ተግባርየግል ሥራ ሲሆን ተማሪዎች ቀደም ሲል በሚና ጨዋታ ያቀረቡትን ሐሳብ የሚያጠናክር ነው። በተለይም አንድ አደጋ የሚያስከትለውን ጉዳት በመተንተን ላይ ያተኩራል:: በመሆኑም ተማሪዎች አንድ የትራፊክ አደጋ ሲከሰት በዕለቱ ከሚታየው ጉዳት በስተጀርባ ያሉ ሌሎች ጉዳቶችን መተንተን አለባቸው።ስለዚህ ተማሪዎች ያቀረቡትን ውስን ጥናት ሲተነትኑ የሚከተሉትን ሐሳቦች ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በማገዝ ትንተናውን ማጠቃለል።

- ሀገር ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች የምታጣው ጥቅም
- የሚባክን ጊዜ
- የንብረት ውድመት
- የአካል ጉዳተኝነት መጨመር
- ወላጅ አልባ ሕፃናት ቁጥር መጨመር
- አዛውንቶች ጧሪ ማጣት እና ሌሎች ናቸው።
  - ምዘናና ክትትል
    - የተማሪዎችን ጽብረቃ መከታተል
    - የተማሪዎችን የመረጃ ትንተናና መደምደሚያ መመዘን
    - የክፍል ሥራ እና የቤት ሥራ
    - የቃል ጥያቄ
    - ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሠሩትን ተግባራት በመመልከታ መመዝገብ።

ማጠቃለያ

የንዑስ ርዕሱ ማጠቃለያ መልመጃን በማየት መልሶቹን ከተጨማሪ ማብራሪያ ጋር መስጠት እና የንዑስ ርዕሱን ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦች በመከለስ ተማሪዎች እንዲጠይቁ ማነቃቃት ። በመጨረሻም የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት ግብ መምታት አለመምታቱን የሚያሳይ ጥቅል መረጃ መያዝ ያስፈልጋል።

የመልመጃ 5.1 ጥያቄ መልሶች

ሀ. የእውነት ሐሰት ጥያቄ መልሶች

1.እውነት 2.እውነት 3. ሐሰት 4.እውነት 5. ሐሰት 6. እውነት

ለ. የማብራሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. በትራፊክ አደጋዎች ሊመጡ የሚችሉትን ውስብስብ ችግሮችን ለማስቀረት ነው።
2. ሀ/አረንጓዴ፡- ተሽከርካሪዎች እንዲሄዱ እና እግረኞች እንዲቆሙ የሚያመለክት ነው።

   ለ/ቀይ፡-እግረኞች እንዲሄዱ(እንዲያቋርጡ) እና ተሽከርካሪዎ እንዲቆሙ ያመለክታል።

   ሐ/ቢጫ፡- ከቀይ ወደ አረንጓዴ እና ከአረንጓዴ ወደ ቀይ ትዕዛዝ መሸጋገሪያ ጊዜ ይሰጣል።

5.2 ኤች. አይ. ቪ / ኤድስ

ከንዑስ ርዕሱ የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት

ተማሪዎች ይህንን ንዑስ ርዕስ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ፡-

• በኤች. አይ. ቪ እና ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል

ያለውን ግንኙነት ይለያሉ፡፡

የንዑስ ርዕሱ ይዘት

- ኤች. አይ. ቪ / ኤድስ
  - የትምህርቱ ጭብጥ

ተማሪዎች በሁለተኛ ክፍል ትምህርታቸው ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተምረዋል፡፡ ስለሆነም የሚያስታውሱትን የኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ የመተላለፊያ እና የመከላከያ መንገዶችን ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይተው እንዲገልጹ ማድረግ፡፡

ኤች. አይ. ቪ የኤድስ ሕመም መንስኤ የሆነ ቫይረስ መጠሪያ ስም ነው፡፡

ኤድስ ማለት በኤች. አይ. ቪ ምክንያት የሚመጣና ሰውነትን ለተለያዩ ሕመሞዎች በቀላሉ እንዲጋለጡ የሚያደርግ በሽታ ነው፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ፈጽሞ ለማዳን ወይም ከደም ውስጥ ቫይረሱን ሊያጠፋ የሚችል መድኃኒትም ሆነ ክትባት አልተገኘለትም፡፡ ነገር ግን ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ያለባቸው ሰዎች ለሌላ ሕመም እንዳይጋለጡ እና የቫይረሱ መራባትን ለመቆጣጠር የሚያስችል መድኃኒት አለው፡፡ ቢሆንም መድኃኒቱ ፈዋሽ ባለመሆኑ የተሻለ የሚሆነው ቫይረሱ እንዳይዘን አስቀድመን መጠንቀቅ ነው፡፡

ምልክቶችን በማየት ብቻ በደም ውስጥ ኤች. አይ. ቪ ቫይረስ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በደም ውስጥ ኤች. አይ. ቪ ቫይረስ መኖሩን ማረጋገጥ የሚቻለው በምርመራ ብቻ ነው፡፡ የኤች. አይ.ቪ/ኤድስ ሕመም ምልክቶች የሚባሉት እንደ ማስመለስ፣ ክብደት መቀነስ፣ ከፍተኛ ላብ ማላብ፣የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ተቅማጥ፣ ሳል፣ ትኩሳት፣ የጉሮሮ ቁስለት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ምልክቶች ደረጃ በደረጃ እየተባባሱ ስለሚሄዱ መድኃኒቶችን እንደየሕመሙ ደረጃ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡

የትምህርት መርጃ መሳሪያና የማስተማር ሥነ-ዘዴ

- የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
- የ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ምልክቶችን የሚያሳይ ሥዕል
- የ ኤች. አይ. ቪ./ኤድስ ሕመም ደረጃዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ
  - የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ተማሪዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በሁለተኛ ክፍል የተማሩትን ለማስታወስ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

- ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምንነትና ምልክቶች ገለጻ ማድረግ፡፡
- ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምንነትና ምልክቶች በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶችና መድኃኒቶች ስላላቸው ግንኙነት በግላቸው ታላላቆቻቸውን እንዲጠይቁና በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡
- ቅድመ ዝግጅት

ይህንን ንዑስ ርዕስ ለማስተማርና ጽንሰ ሐሳቡን ለማሥረጽ ይቻል ዘንድ፡-

- ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የተሟላ ግንዛቤ የሚያስይዙ ጽሑፎችን በማፈላለግ ማንበብ ያስፈልጋል፡፡
- የ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕመም ምልክቶችን የሚያሳይ ሥዕል ማዘጋጀት፡፡
- የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሕመም ደረጃዎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡ ፡

- የመማር ማስተማር ሂደት

መግቢያ

ንዑስ ርዕሱ ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ መሆኑን ማስተዋወቅና በንዑስ ርዕሱ ሥር በተቀመጡት ይዘቶች ላይ ስላላቸው ቅድመ ዕውቀት በመጠየቅ ትምህርቱን ማስጀመር፡፡በተጨማሪም የማነቃቂያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ፡-

1.ተማሪዎች ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምንድን ነው?

2. የኤች አይ ቪ/ ኤድስ መድኃኒት ከኤድስ ሕመም ያድናልን? እና የመሳሰሉትን መጠየቅ፡፡

በዚህ ሂደትም የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ ባህርይ እና ልዩ ፍላጎቶቻቸውን መለየት፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ንዑስ ርዕስ የሚጠበቁትን አጥጋቢ የመማርብቃቶችን ማስተዋወቅ፡፡

- የትምህርቱ አቀራረብ

ተማሪዎች ሥዕሎችን በማየት እንዲያብራሩ ማድረግና በቡድን ውይይት ጊዜ በመከታተል ድጋፍ ማድረግ፡፡

ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የሚያብራራ አጭር ማስታወሻ መስጠት፡፡

የቡድን ውይይት -2- መልስ

ተማሪዎችየቡድን ውይይት ሲያደርጉ ማበረታታትና ድጋፍ ማድረግ። በመጨረሻም ከውይይቱ የሚገኘው ፍሬ ሀሳብ እንደሚከተለው ይጠቃለላል።

ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ሲሆን የሰዎችን ነጭ የደም ሕዋስን የሚያጠቃና የነጭ ደም ሕዋስን ቁጥር እንዲቀንስ ያደርጋል። በዚህ የተነሳም ሰዎች ለልዩ ልዩ ሕመም በመጋለጥ ይታመማሉ።

ኤች. አይ. ቪ፡-

- ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ
- ከቫይረሶች ውስጥ የሚመደብ፤ በደም ውስጥ የሚራባ፤
- ሰውነታችን ሕመምን እንዲቋቋም የሚያስችሉትን ነጭ የደም ሕዋሶችን በማጥቃት የሰውነታችንሕመምን የመከላከል ሥርዓት የሚደመስስ፤
- የኤድስን ሁኔታ የሚፈጥር ቫይረስ ነው።

ስያሜው የተወሰደ “ሂውማን ኢሚዩኖ ዴፊሸየንሲ ቫይረስ” ከተሰኘው የእንግሊዘኛ ስያሜ ሲሆን ወደ አማርኛ ሲመለስ፡-

ሂውማን(Human) ማለት የሰው(ሰውን ብቻ የሚያጠቃ)

ኢሚዩኖ ዴፊሸየንሲ ቫይረስ(Immuno deficiency virus) ማለት የሕመም መከላከል ሥርዓት አልባ አድራጊ ቫይረስ ማለት ነው።

ኤድስ የሚለው ምጎላረቃል የተወሰደው ደግሞ “ሂዩማን ኢሚዩኖ ዴፊሸየንሲ ቫይረስ” ከተሰኘው የእንግሊዘኛ ስያሜሲሆን መሠረታዊ ሐሳቡ ወደ አማርኛ ሲመለስ፡-አኳየርድ(Aquired) ከሰው ወደ ሰው የተላለፈ፤ ኢሚዩኖ ዴፊሸየንሲ (Immuno deficiency) ማለት የሰውነት የመከላከያ ሥርዓት አልባነት ሲሆን፤ ሴንድሮም(Syndrome) ማለት ደግሞ የሕመም ምልክቶች ማለት ነው።

ኤድስ በራሱ ሕመም ሳይሆን የሰውነት ሕመም መከላከል ሥርዓት በመውደሙ ምክንያት ለሞት የሚያበቁ የተለያዩ የሕመምዓይነቶች የመጋለጥ ሁኔታነው።

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምልክቶች የሚባሉት እንደማስመለስ፣ ክብደትመቀነስ፣ ከፍተኛ ላብ ማላብ፣የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ ተቅማጥ፣ ሳል፣ ትኩሳት፣ የጉሮሮ ቁስለት እና የመሳሰሉት ናቸው።

የተግባር -6- መልስ

ተማሪዎች ታላላቆቻቸውን ወይም ወላጆቻቸውን ሲጠይቁ የተግባሩን ዓላማ ሊያሳኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳለባቸው ግልጽ መመሪያ መስጠት።

ይህ ተግባር የግል ሥራ ሲሆን ተማሪዎች ታላላቆቻቸውን ሲጠይቁ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምልክቶችና መድኃኒቶች ስላላቸው ትስስር ነው። በዚህም መሠረት መረዳት ያለባቸው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምልክቶች ደረጃ በደረጃ እየተባባሱ የሚሄዱ መሆናቸውን

ነው። ስለዚህ መድኃኒቶችን እንደየ ሕመሙ ደረጃ መጠቀም ተገቢ ነው። ምክንያቱም ሕመሙ ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሱ በፊት በሐኪም ትዕዛዝ መሠረት መድኃኒት መጠቀም ይቻላል።

- ምዘናና ክትትል
  - የተማሪዎችን ጽብረቃ መከታተል
  - የተማሪዎችን የመረጃ ትንተናና መደምደሚያ መመዘን
  - መልመጃዎችን ማሰራት
  - በውይይት ጊዜ ምልከታ ማድረግ
  - ተማሪዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ አጭር ገለጻ እንዲያቀርቡ ማድረግ
  -

ማጠቃለያ

የንዑስ ርዕሱ ማጠቃለያ መልመጃን በማየት መልሶቹን ከተጨማሪ ማብራሪያ ጋር መስጠት እና የንዑስ ርዕሱን ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦች በመከለስ ተማሪዎች እንዲጠይቁ ማነቃቃት ።

በመጨረሻም የንዑስ ርዕሱ አጥጋቢ የመማር ብቃት ግብ መምታት አለመምታቱን የሚያሳይ ጥቅል መረጃ መያዝ ያስፈልጋል።

የመልመጃ 5.2 መልሶች

ሀ. የእውነት ሐሰት ጥያቄ መልሶች

እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. ሐሰት

ለ. የአዛምድ ጥያቄ መልሶች

1.መ 2.ሀ 3.ሐ 4.ለ

የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

ሀ. የእውነት ሐሰት ጥያቄ መልሶች

እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት 5. እውነት

ለ. የአዛምድ ጥያቄ መልሶች

1.መ 2.ሐ 3.ሀ 4.ለ

ሐ. የምርጫ ጥያቄ መልሶች

1.መ 2.ሀ 3.ለ 4.መ 5.መ

ዋቢ መጻሕፍትና ድህረ ገጾች

ዋቢ መጻሕፍት

- መሪ የአሸከርካሪዎች የስልጠና መጽሐፍ (10ኛ እትም፡ 2010 ዓ.ም)
- ቶፕ መሠረታዊ የአካባቢ ሳይንስ አጋዥ መጽሐፍ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል 2008 ዓ.ም በድጋሚ 5ኛ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመ
- ጎብረተሰብ ሳይንስ የትምህርት መማሪያ መጽሐፍ 5ኛ እና 7ኛ ክፍል የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2003 ዓ.ም
- አ.አ.መ ት/ቢሮ (1990-1995) 5ኛ ክፍል የጎብረተሰብ ሳይንስ የተማሪ መጽሐፍ
- አካባቢ ሳይንስ ከ2ኛ-4ኛ ክፍል የመምህር መምሪያ የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2006 ዓ.ም
- አካባቢ ሳይንስ የተማሪ መጽሐፍ ከ2ኛ-4ኛ ክፍል የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2006 ዓ.ም
- የተቀናጀ ሳይንስ የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ እና 6ኛ ክፍል የአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ 2006 ዓ.ም

- ### ድህረ ገጾች

- http://people.tamu.edu/~i-choudhury/culture.html
- https://www.livescience.com/2147□8-what-is-culture-definition-of-culture.html
- https://www.toppr.com/guides/commercial-knowledge/business-and-commercial-knowledge/what-are-economic-activities/
- https://www.investopedia.com/terms/t/trade.asp
- https://link.springer.com/article/10.1007/BF01624609
- https://voxeu.org/article/trade-natural-resources-and-wto?__cf_chl_captcha_tk__=pmd_jaEI.9ECjdqG7v6uwDIQJXp5ukrK0neFsfK_RnGfw4I-1629231863-0-gqNtZGzNAuWjcnBszQh9
- https://www.oecd.org/trade/topics/trade-and-the-environment/

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት

የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የይዘት ፍሰት፣ የመማር ብቃትና መርሐ ትምህርት

ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት የይዘት ፍሰቶች
ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

ምዕራፍ	የመማር ይዘት መስኮች	አንደኛ ክፍል	ሁለተኛ ክፍል	ሦስተኛ ክፍል	ዐራተኛ ክፍል	አምስተኛ ክፍል	ስድስተኛ ክፍል
አንድ	መገኛ	• የመገኛ ምንነት	• የወረዳችን መገኛ	• የክፍለ ከተማችን መገኛ	• የከተማችን መገኛ	• የኢትዮጵያ አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ	• የምሥራቅ አፍሪካ አንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ
ሁለት	ሳይንስን መገንዘብ	• የሰውነታችን ክፍሎች • ምግብና ጥቅሙ • የብርሃን ምንነት	• ውጫዊ የሰውነት ክፍሎቻችንና • የስሜት አካላቶቻችን • የቁሶች አካላዊ ባሕርያት • የብርሃን ምንጮች	• ምግብና ጤና • የምግብ ጥቅም • ዐራቱ የምግብ ምድቦች (ጥራ ጥሬዎች፣ ሥጋ፣ ወተት፣ አትክልትና ፍራፍሬዎች) • የምግብ ብክለት • የቁስ አካል ሁኔታዊ ለውጥ (ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች) • የብርሃን ጥቅም	• ምግብና ጤናማ አኗኗር • ውስጣዊ የሰውነት አባል አካላት • አስፈላጊ የምግብ ንጥረ ነገሮች • የተመጣጠነ አመጋገብ • የቁስ አካል አካላዊና ኬሚካዊ ባሕርያት • የብርሃን ባሕርያትና ጥላ	• የሥርዓተ ልመት ዋና ዋና ክፍሎች • ቁስ አካል • የጉልበት ምንጮች	• የደም ዝውውር • ጉርምስና • የአየር ምንዝሮች • ሥርዓተ ትንፈሳ • ጉልበትና ጥቅሙ
ሦስት	ተፈጥሮአዊ አካባቢ	• የአየር ሁኔታ • ሕይወት ያላቸውና ሕይወት የሌላቸው ነገሮች • ለማዳና የዱር እንስሳት • የመኖሪያ አካባቢያችንን መንከባከብ	• የአየር ሁኔታእና የአየር ንብረት • በወረዳችን የሚገኙ እንስሳ ትና ዕፅዋት • በወረዳችን የሚገኙ ቁሳዊ ሀብቶች • የወረዳችንን አካባቢ መንከባከብ	• የክፍለ ከተማችን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የክፍለ ከተማችንን አካባቢ መንከባከብ	• የከተማችን ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የከተማችንን አካባቢ መንከባከብ	• የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የኢትዮጵያን አካባቢ መንከባከብ	• የምሥራቅ አፍሪካ ተፈጥሮአዊ ሀብቶች • የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢ መንከባከብ

ምዕራፍ	የመማር ይዘት መስኮች	አንደኛ ክፍል	ሁለተኛ ክፍል	ሦስተኛ ክፍል	ዐራተኛ ክፍል	አምስተኛ ክፍል	ስድስተኛ ክፍል
ዐራት	ማኅበራዊ አካባቢ	• ቤተሰብና ማኅበረሰብ • አካባቢያችን	• ቤተሰብና ማኅበረሰብ በወረዳችን • አካባቢያችን	• የክፍለ ከተማችን ሕዝቦችና ባህሎች • የክፍለ ከተማችን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች	• የከተማችን ሕዝቦችና ባህሎች • የከተማችን ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች	• የባህል ብዝኃነት በኢትዮጵያ • ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ	• የሕዝብ ብዙኃነት በምሥራቅ አፍሪካ • ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በምሥራቅ አፍሪካ
አምስት	ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ	• የመንገድ ደኅንነት • ኤች አይ ቪ /ኤድስ	• የኬሚካል አጠቃቀም ደኅንነት • ኤች አይ ቪ እና ሌሎች ተላላፊ ሕመሞች • ድርቅና ረሃብ በከተማችን	• የኬሚካል አጠቃቀም ደኅንነትና አደንዛዥ ዕፅ • ድርቅና ረሃብ በኢትዮጵያ • ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወረዳችንና በክፍለ ከተማችን	• አደንዛዥ ዕፅና ሱሰኝነት • ድርቅና ረሃብ በምሥራቅ አፍሪካ • ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በከተማችንና በሀገራችን

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የሦስተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ግንቦት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

ምዕራፍ አንድ ፡- የክፍለ ከተማችን መገኛ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 34

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ ፡- • አቅጣጫን የመለየት ክህሎት ማዳበር • ሥዕላትንና ካርታዎችን በመጠቀም ከሰዎች ጋር ለመግባባት ፈቃደኝነት ማሳየት • የአንጻራዊ መገኛን ምንነትን መግለጽ • የፍጹማዊ መገኛን ምንነት መግለጽ • የክፍለ ከተማቸውን አንጻራዊ መገኛ ማመልከት • በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የክፍለ ከተማቸውን መገኛ ማመልከት • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ቁልፍ ቦታዎችን ለማመልከት ኬክሮስና ኬንትሮስን መጠቀም • የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ በመጠቀም በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ጠቃሚ ቦታዎችን ማመልከት	የክፍለ ከተማችን መገኛ • የአንጻራዊ መገኛ ምንነት • የፍጹማዊ መገኛ ምንነት • የክፍለ ከተማችን አንጻራዊ መገኛ • የክፍለ ከተማችን ፍጹማዊ መገኛ • በክፍለ ከተማችን የሚገኙ ዋና ዋና ቦታዎች መገኛ • የክፍለ ከተማችን አዋሳኝ ክፍለ ከተማዎች መገኛና ስማቸው	• ተማሪዎች ስለ ኬክሮስና ኬንትሮስን ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ • ተማሪዎች ስለ አንጻራዊ መገኛ ምንነት የሚያውቁትን እንዲናገሩ መጠየቅ • ተማሪዎች በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የክፍለ ከተማቸው መገኛ እንዲያመለክቱ ማድረግ • ተማሪዎች በካርታ ላይ ኬክሮስና ኬንትሮስን በመጠቀም የተለያዩ ቦታዎችን መገኛ እንዲያመለክቱ ማድረግ • ተማሪዎች የክፍለ ከተማቸውና የአጎራባች ክፍለ ከተማዎችን መገኛ የሚያሳይ ቀላል ንድፍ ካርታ እንዲሠሩ ማድረግ • ተማሪዎች የጎግል ካርታ መፈለጊያ መተግበሪያ ተገቢ አጠቃቀም እንዲያሳዩ መጠየቅ • ተማሪዎች የሠሩትን ሥራ ለሌሎች የክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማመቻቸት • ተማሪዎች ወደ ቤታቸው ሲሄዱ በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ጠቃሚ ቦታዎችን ፈልገው እንዲመለከቱ የቤት ሥራ መስጠት	• ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ መመልከት •ተማሪዎች በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ነገሮችን ለማመልከት የሚያደርጉት ጥረት መሻሻሉን መከታተል •ተማሪዎች ሐሳባቸውን ሲገልጹ መመልከት •ተማሪዎች ሥራቸውን ሲያቀርቡ ያላቸውን ተሳትፎ መመልከት • የተማሪዎችን ዘገባ በመመልከት አወንታዊ ግብረ መልስ መስጠት • ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምዘና ማድረግ

ምዕራፍ ሁለት :- ሳይንስን መገንዘብ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 42

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ፡- • ጤናማ ምግቦችና መጠጦችን መለየት ይችላሉ • ምግቦቸን በዐራት ዋና ዋና ምድቦች ይከፍላሉ • የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችሉ የንጽሕና አጠባበቅ መንገዶችን ይለያሉ • የንጽሕና መጠበቂያ መንገዶችን ይገልጻሉ፡፡ • የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች ባሕርያትን ፍችዎች በመስጠት ይገልጻሉ • የቁስ አካላትን (የጠጣር፣ የፈሳሽና የጋዞች) የሁነታ ለውጥ ይገልጻሉ • የብርሃንን ጥቅሞች ይዘረዝራሉ	2.1 ምግብና ጤና 2.2 የምግብ ጠቀሜታ • ዐራቱ የምግብ ምድቦች (ጥራጥሬዎች፣ ሥጋ፣ወተት እና አትክልትና ፍራፍሬዎች) • የምግብ ብክለት መንሥኤዎች 2.3 የግል ንጽሕና አጠባበቅ • ንጽሕናችንን ለምን እንጠብቃለን? • ንጽሕናችንን ባንጠብቅ በሌሎች ላይ ምን ጉዳት ያደርሳል? • በንጽሕና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች • ጤናማና ሕመምተኛ ሰዎችን ማወዳደር • ለታመሙ ሰዎች የምናደርገው ርህራሄና እንክብካቤ 2.4 የቁስ አካል አካላዊ ለውጦች • ጠጣር፣ፈሳሽ እና ጋዞች 2.5 የብርሃን ጠቀሜታ	• መማሪያ መጽሐፍን ማንበብ፣ ውይይት፣ ገለጻ እና ሠርቶ ማሳየትን መጠቀም • በቡድን በመክፈል ጥያቄዎችን መጠየቅ • የሚያውቋቸውን የምግብ ዓይነቶች በወረቀት እንዲዘረዝሩ በማድረግ በዐራቱ ዋና ዋና የምግብ ምድቦች እንዲመድቧቸው ማበረታታት • የምግብ መበከል ዋነኛ መንሥኤዎችን እንዲጠይቁና እንዲወያዩ ማድረግ (ለምሳሌ እጅን በአግባቡ አለመታጠብን እና የአፍ ንጽሕናን አለመጠበቅ) • የጤናና የሕመም ልዩነትን ተወያይተው እንዲረዱ ማድረግ • በቡድን በማደራጀት በጥጥር፣በፈሳሽና በጋዞች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲወያዩ ማድረግ • የብርሃንን ምንጮችና ጠቀሜታ ተወያይተው እንዲዘረዝሩ ቤት ውስጥ ወስደው የሚሠሩት ተግባር መስጠት ለምሳሌ:- ምንጮች (ፀሐይ፣ ኮከብ፣ ጨረቃ፣ ሻማ፣ ባትሪ፣ አምፖል የመሳሰሉት) • የብርሃን ጠቀሜታ (ለማየት፣ዕጽዋት ምግባቸውን እንዲያዘጋጁና ለዕድገታቸው እና ለጉልበት ምንጭነት)	• በጥያቄና መልስ ምግብን በዐራት ዋና ዋና የምግብ ምድቦች እንዲመድቡ ማድረግ • ዋነኛ የምግብ ብክለት መንሥኤዎች ላይ ሲወያዩ ትኩረት ሰጥቶ መከታተል • የተማሪዎችን ውጤት መመዝገብ • መማራቸውን ለማሻሻል ገንቢ አስተያየት መስጠት • የብርሃንን ጠቀሜታ ሲዘረዝሩ ዕውቀታቸውን መመዘን

ምዕራፍ ሦስት ፡- ተፈጥሮአዊ አካባቢ

ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 54

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ፡- • የአየር ሁኔታና የአየር ንብረትን ልዩነቶች መግለጽ • በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ሁኔታዎችን መግለጽ • በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የሙቀት መጠን ልዩነት መገምገም • በክፍለ ከተማቸው የሚኖረውን የዝናብ መጠን ሥርጭት ማወዳደር • በክፍለ ከተማቸው የአየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን (ከፍታ፣ የደን ሽፋንና ከባህር ያለው ርቀት) መለየት • የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት መግለጽ • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን መለየት	3.1 የክፍለ ከተማችን አየር ንብረት • የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ልዩነት • የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች 3.2 የተፈጥሮ ሀብቶች • የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶች ምንነት • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች (ማዕድናት፣ የዱር እንስሳ ት እና የመሳሰሉት) • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅም 3.3 የተፈጥሮ ሀብቶች ለክፍለ ከተማቸው ህልውናና ዕድገት ያለው ፋይዳ	• ስለ አየር ሁኔታና አየር ንብረት ያላቸውን መረዳት መጠየቅ • የክፍለ ከተማቸውን አጠቃላይ የአየር ንብረት ሁኔታ እንዲገልጹ መጠየቅ • የዝናብ መጠንን የሚያሳይ ካርታን በመጠቀም የክፍለ ከተማቸውን ደረቅና እርጥበታማ የአየር ንብረት እንዲያሳዩ ማድረግ • የሙቀት መጠንን የሚሳይ ካርታን በመጠቀም የክፍለ ከተማቸውን የሙቀት መጠን ልዩነት እንዲያሳዩ ማድረግ • የክፍለ ከተማቸውን ዋና ዋና የአየር ንብረት ተቆጣጣሪዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ • በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድሩ የተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች አስመልክቶ በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ ውይይቱን መምራት በመጨረሻም እንዲያቀርቡ ማድረግ	• ጥያቄዎችን ሲመልሱ መመልከት • የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ልዩነትን በተሻላ ሁኔታ ሲያብራሩ መከታተል • ተግባሮችን ሰጥቶ መከታተል ለምሳሌ፡ - የሙቀት መጠንን እና የዝናብ ሥርጭት የሚያሳይ ግራፍን የማንበብ ክህሎት • መረጃ በመያዝ ገንቢ ግብረ መልሶችን መስጠት • የተማሪዎችን ሥራ በማየት ገንቢ የሆኑ ግብረ መለሶችን መስጠት • ተከታታይ ምዘና መስጠት • ተማሪዎች በቤታቸው እንዲሠሩ በተሰጣቸው ሥራ ላይ ገንቢ ግብረ መልስ መስጠት

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃቶች	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
• የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም መግለጽ • በክፍለ ከተማቸው የሚስተዋሉ ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንሥኤዎችንና ውጤቶችን መግለጽ • በክፍለ ከተማቸው የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎችን መግለጽ • የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ለቀጣይ ትውልድ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ዋጋ መስጠት • ብክለትን ለመቀነስ የሚያግዙ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማቅረብ • በትምህርት ቤታቸውና በወረዳቸው መልሶና ደጋግሞ የመጠቀም ዘዴዎችን ማዘውተር • ቆሻሻን ያለአግባብ ማስወገድ በአካባቢያቸው ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ መግለጽ • ንጽሕናው የተጠበቀ አካባቢ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሐሳብ መስጠት	• የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነት፣ • በክፍለ ከተማቸው የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንሥኤዎችና ውጤቶች • በክፍለ ከተማቸው የሚዘወተሩ ሀገር በቀልና የተለመዱ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና የእንክብካቤ ዘዴዎች • በክፍለ ከተማቸው የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና መንከባከብ ያለው ጠቀሜታ 3.4 በትምህርት ቤት እና በወረዳቸው የሚስተዋሉ ተገቢ እና ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ዘዴዎች 3.5 ተገቢ ያልሆኑ የቆሻሻ አወጋገድ ተጽዕኖዎች	• የሠሯቸውን ተግባራት በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት • ሳምንታዊ የአየር ሁኔታ በተመለከተ በቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባራትን በመስጠት እንዲገነዘቡና እንዲያደንቁ ማድረግ • የተፈጥሮና የሰው ሠራሽ ሀብቶችን ምንነት መጠየቅ • በቡድን በማደራጀት በክፍለ ከተማቸው ስለሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ተወያይተው እንዲናገሩ ማድረግ (ስለ ማዕድናት፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎችም) • በቡድን በማደራጀት በክፍለ ከተማቸው ስለሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ተወያይተው ጥቅማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ (ስለ ማዕድናት፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎችም) • የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን መጠየቅ	• ውስብስብ/ሰፋ ያሉ ይዘቶችን በውይይት ግልጽ ያደርጋሉ • ውይይት ከመጀመራቸው በፊት ሊያወያዩ የሚችሉ ጥያቄዎችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ለተማሪዎቹ ማንብብ • ሁሉም ተማሪዎች መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎችን በአትኩሮት መከታተል፣በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስና ሁሉም ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማበረታታት • ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን በአንክሮ እንዲከታተሉ ማድረግ • እርስ በእርሳቸው ተግባቦት እንዲኖራቸው ማመቻቸት ለምሳሌ፡- አንዳቸው የሌላቸውን ጥያቄዎች በቀጥታ እንዲመልሱ ማድረግ እና አንዳቸው የሌላቸውን ሐሳብ ሳያቋርጡ በጥሞና እንዲያዳምጡ ማድረግ

ምዕራፍ ዐራት ፡- ማኅበራዊ አካባቢ ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 54

አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ሲያጠናቅቁ • የባህልን ምንነት ይገልጻሉ • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ባህላዊ ልማዶችን ያበራራሉ • በክፍለ ከተማ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅና ለመንከባከብ የሚያግዙ ባህላዊ ልምዶችን ይለያሉ • ባህላዊ ብዝኃነትን በሥነ ጥበብ ያደንቃሉ • የአየር ንብረት በክፍለ ከተማቸው በሚንጸባረቁ በባህሎች ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይገልጻሉ	4.1 የባህል ብዝኃነት • የባህልና ባህላዊ ክዋኔዎች ምንነትና ምሳሌዎች • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተለያዩ ባህሎች (አለባበስ፤ አመጋገብ፤ የግጭት አፈታት ወዘተ) • በክፍለ ከተማቸው ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎች • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች	• ባህል ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎችን መጠየቅና ምሳሌ መስጠት • በክፍለ ከተማቸው የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን አስመልክቶ ታላላቅ ሰዎች / አዛውንቶችን በመጠየቅ እንዲሰበስቡ በማድረግ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡ ማድረግና ማመቻቸት • በክፍለ ከተማቸው ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ የሚረዱ ባህላዊ ክዋኔዎችን አስመልክቶ የአካባቢ አዛውንቶችን በመጋበዝ ለሁሉም ተማሪዎች ገለጻ ማድረግ • በክፍለ ከተማቸው የተፈጥሮ ሀብት በባህል ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ በሚመለከት በቤታቸው ሠርተው እንዲመጡና የሠሩትን ለሁሉም እንዲያቀርቡ ማድረግ • በክፍለ ከተማቸው የሚከናወኑ ዐበይት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲዘረዝሩ ወይንም እንዲጠቅሱ መጠየቅ	• ሰፊና ውስብስብነት ያላቸውን የመወያያ ርዕሶችንና ከውይይቱ የሚጠበቀውን ግልጽ ማድረግ • ከውይይቱ በፊት መሪ ጥያቄዎችን ዝርዝር በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍና ማንበብ • ፊት ለፊት የዓይን ለዓይን ግንኙነት በመፍጠርና በክፍል ውስጥ በመንቀሳቀስና በመዘዋወር እያንዳንዳቸው ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው መንገር (የሁሉንም የቡድን አባላት ተሳትፎ ማረጋገጥ) • ተማሪዎች በያዙት ርዕሰ ጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ • አንዱ ከሌላው ጋር የሚኖረውን ተግባቦት ማመቻቸት- ለምሳሌ፤ አንዱ ለሌሎች ሐሳብ ቀጥተኛ መልስ እንዲሰጡ መጠየቅ፤ አንዱ የሌላውን ሐሳብ ከመንቀፍና ከማቋረጥ ይልቅ በምክንያታዊነት እንዲያዩ ማድረግ) • በውይይቱ የሁሉም ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎና አስተዋጽኦ እንዲኖር ማድረግና ውይይቱ በተወሰኑ ተማሪዎች ተጽዕኖ ሥር እንዳይሆን መቆጣጠር • ተማሪዎች በጉዳዮች ላይ ጥልቅና ከተለያዩ ዕይታዎች አንጻር ለመገንዘብ የሚያስችላቸውን ግልጽና ውስን የሆኑ ጥያቄዎችን በውይይቱ ሂደት ሁሉ ማዘጋጀት

አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
• የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ምንነትን መግለጽ • በክፍለ ከተማቸው የሚከናወኑ ዋና ዋና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ያብራራሉ •ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ ይለያሉ • የገበያ ምንነትን ይገልጻሉ • የተፈጥሮ ሀብትና ምርቶቻቸው በገበያ ላይ የሚኖራቸውን ልምድ ይገልጻሉ • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የመጓጓዣ ዘዴዎችን ያብራራሉ	• በክፍለ ከተማቸው በተፈጥሮ ሀብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚሳድሩ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች • የገበያ ምንነት • በክፍለ ከተማቸው ለገበያነት ሊቀርቡ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶች • በክፍለ ከተማቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት፤ ውጤቶችና የግብይት ክዋኔዎች • ለሰዎችና ለዕቃዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች	• የገበያና የግብይት ምንነትን (ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቀጥታ ግብይትን ጨምሮ) እንዲናገሩ መጠየቅ • ተማሪዎች በክፍለ ከተማቸው ለገበያ የሚውሉ የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸውን አስመልክቶ በቤታቸው እንዲሠሩ ማድረግና የሠሩትን ለሁሉም ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ • ተማሪዎች በክፍለ ከተማቸው ለገበያ የሚውሉ ዐበይት የተፈጥሮ ሀብቶችና ውጤቶቻቸውን አስመልክቶ በቡድን እንዲወያዩና እንዲናገሩ ማድረግ • ተማሪዎች በክፍለ ከተማቸው ለሰውና ለዕቃ መጓጓዣነት የሚያገለግሉ የተለያዩ መጓጓዣ ዘዴዎችን እንዲናገሩ መጠየቅ	• ዋና ዋና ሐሳቦችን በመዘርዘር፤ በመግለጽና በማጠቃለል በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ • ተማሪዎችን ወደ ራስ ሐሳብና አረዳደድ ብቻ እንዲመጡ አለመሞከር፤ የተለያዩ ሐሳቦችንና ዕይታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት • የተማሪዎችን ሐሳቦች በጥንቃቄ በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝና መመዝገብ • ለሁሉም ጥያቄዎችና ለተሰጡ ሐሳቦች ወይንም አሰተያየቶች አክብሮት ማሳየት፤ ለነበራቸው አስተዋጽኦ ተማሪዎችን ማመስገን • ተማሪዎች የመከራከሪያ ሐሳባቸውን በማስረጃ አስደግፈው ለሌሎች ተከራካሪዎቻቸው በመግለጽ እንዲመልሱ መደገፍ • የውይይቱ አቀራረብና አካሂድን በተመለከተ አጭር ማስተዋሻ መያዝና በሌላ ጊዜ ሌላ ውይይት ለማዘጋጀትና ለማቅረብ የተያዙትን ነጥቦች እንደመነሻ መጠቀም • ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ወይንም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ግምት ውስጥ ማስገባት • ተማሪዎች የታላላቅ አዛውንቶችን ዐበይት ሐሳቦችን እንዲመዘግቡ ማድረግ

የሦስተኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ትምህርት መርሐ ትምህርት

ምዕራፍ አምስት ፡- ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች **ለምዕራፉ የተመደበው ክፍለ ጊዜ - 30**

የምዕራፉ አጥጋቢ የመማር ብቃት	የትምህርት ይዘት	የመማር ስልቶች	ምዘና
ተማሪዎች ይህን የትምህርት ይዘት ተምረው ሲያጠናቅቁ ፡- • የትራፊክ ደንቦችን መግለጽና መጠቀም • በኤች አይ ቪ እና ኤድስ ምልክቶችና በመድኃኒቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት	1. የመንገድ ደኅንነት 2. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ	• ተማሪዎችን በመንገድ ላይ በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ አደጋዎችን በቤተሰብና በሕፃናት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መጠየቅ • ተማሪዎች እንደ ትራፊክ ፖሊስ በተሽከርካሪዎች መንገድ ላይ ኪስ የሚጫወቱ ሕፃናትን ሁኔታ በሚና እንዲያሳዩ መጠየቅ • ተማሪዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ. እና ኤድስ አጭር ገለጻ እንዲያቀርቡ ማድረግ	• የተማሪዎችን ጽብረቃ መከታተል • የተማሪዎችን የመረጃ ትንተናና መደምደሚያ መመዘን